2018
ሚያዝያ - ሰኔ

ጥራዝ 102፣ ቁ. 2

የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች
የጎልማሶች ክፍል



# የትንቢት አስፈላጊነት

## የዳንኤልና የዮሐንስ ትንቢታዊ አገልግሎቶች የአሰሳ ጥናት

GENERAL CONFERENCE SABBATH SCHOOL

# የዳንኤልና የዮሐንስ ትንቢታዊ አገልግሎቶች የአሰሳ ጥናት

## የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ፡ የጎልማሶች ክፍል

ጥራዝ 102፣ ቁጥር 2 ፡ ሚያዝያ - ሰኔ፣ 2018

## ማውጫ


1. መግቢያ ስለ ትንቢት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
2. የእግዚአብሔር መልእክተኛ ለነገሥታት . . . . . . . . . . .10
3. የወደፊት መንግሥታት ተገለጡ . . . . . . . . . . . . . . . .15
4. የዳንኤል የመጀመሪያው ራዕይ . . . . . . . . . . .. . . . . . .20
5. የመንግሥታት መተካካት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26
6. ራእዩ ተብራርቷል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .31
7. የታተመው መጽሐፍ እንደገና ተከፈተ . . . . . . . . . . . .36
8. የፍጥሞው ነቢይ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .41
9. ዘንዶው፣ ሴቲቱ እና ቅሬታዎቹ . . . . . . . . . . . . . . . 46
10. አውሬው እና ምልክቱ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 52
11. ሦስቱ መላእክት . . . . . . . . . . . . . . . . .. . . . . . . .57
12. የመጨረሻው ጥሪ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .62
13. መጨረሻው አስቀድሞ ተነግሮአል . . . . . . . . . . . . . 67

# መቅድም

መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መመሪያ መጽሐፍ ሆኖ በመለኮታዊ ጥበቃ ስር ተጠብቆ ቆይቷል። በውስጡ ያሉት ታሪኮች ለግል ሕይወታችን እና ለምንኖርበት ለዚህ ጊዜ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ትምህርቶች ይዘዋል። ይህ እግዚአብሔር በአሕዛብ እና በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ የሰራው ሥራ ያበረታታናል፥ ፍቅሩንም ያረጋግጥልናል። እጅግ ውድ የሆነው ምስክርነቱ እርሱም የየሱስ ሕይወት እና መልእክት በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ያነቃቃል። "እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና" (1ኛ ዮሐንስ 4:19)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት አስደናቂ የአምላካችን ባሕርያቶች አንዱ 'አስቀድሞ ማወቁ' ነው "ከመጀመሪያ መጨረሻውን" ማየት ይችላል (ኢሳይያስ 46:10)። ይህም "እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ።" (ሮሜ 8:28) ለማድረግ ወደር የሌለውን ኃይሉን እንዲጠቀም ያስችለዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ "ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር።" ለሕዝቡ ለመግለጽ ወዷል (ራዕይ 1:1)። ይህም በፍቅሩና በጥበቃው ላይ እንድንተማመን ያደርገናል፤ አልፎም የመጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ መለኮት እንደሆነ አንዱ ማረጋገጫ ነው። ትንቢት በታሪክ ገጾች ውስጥ በተከታታይ መፈጸሙ እና የአሁን ክስተቶች መገለጥ የእግዚአብሔር ቃል ከሰው ፈጠራ የበለጠ መሆኑን ያሳያሉ።

ትንቢት ለእግዚአብሔር ልጆች እጅግ አስፈላጊ ነው። "የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።" (ራዕይ 1:3) ሲል በረከቱ በእነርሱ ላይ እንደሚሆን ገልያአል።

ከነቢያት ጸሐፎች መካከል ሁለቱ የታሪክን ዝርዝር መግለጫዎች እና ስልታዊ ትንበያዎችን በመያዛቸው ጎልተው ይታያሉ። ዳንኤል እና ዮሐንስ እነዚህ ልዩ መልእክቶች ተሰጥቷቸዋል፤ እናም መጽሐፎቻቸው፤ ዳንኤል እና ራዕይ የዚህ ሩብ ዓመት የሰንበት መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እትም ትኩረት ናቸው።

በሚቀጥሉት ሶስት ወራት የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የዳንኤልንና የዮሐንስን ታሪኮች እና የዘገቧቸውን አንዳንድ አስፈላጊ ትንቢቶች ያጠናሉ። እነዚህ የምፅአቱን መልእክት፣ ያለፈውን እና የአሁኑን መንፈሳዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ለመረዳት የሚያስችልን ማዕቀፍ ያስቀምጣሉ።

በዚህ ሩብ ዓመት የሁለቱንም መጻሕፍት እያንዳንዱን ክፍል ለመሸፈን የሚያስችል በቂ ጊዜ ባይኖርም፣ ተማሪዎች ሙሉ ይዘታቸውን እና ከቀሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ጨምሮ በጥልቀት እንዲያጠኑ ይበረታታሉ።

የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎች የእነዚህን ትንቢቶች በዝርዝር ለመረዳት ከሚረዷቸው ምርጥ የመርጃ ምንጮች አንዱ በኡሪያ ስሚዝ የተጻፈው "The thoughts on Daniel and the Revelation" የተሰኘው መጽሐፍ ነው። በዚህ ሩብ ዓመት ውስጥ ለጥናት እንደ አጋዥ እንዲጠቀሙት አጥብቀን እንመክራለን።

በእነዚህ ትንቢቶች ጥናትዎ እንዲባረኩ ጸሎታችን ነው። ምክንያቱም "ዘመኑ ቀርቧል" (ራዕይ 1:3)።

የአጠቃላይ ጉባኤ የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል

## መጋቢት 26፣ 2018

## የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ



# ለጣሊያን ዋና መሥሪያ ቤት

ጣሊያን በሜዲትራኒያን ባህር መሃል ላይ የምትገኝ ውብ፣ በጥንታዊ ታሪኳ፣ በማይነፃፀር ጥበብ፣ በሚያምር የምግብ አሰራር እና በሚያስደምም የመሬት ገጽታዋ በዓለም ሁሉ ታዋቂ አገር ናት። ከዓለም ከፍተኛ የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ ከመሆኗ በተጨማሪ አስፈላጊ የሆነች የኢንዱስትሪ እና የግብርና አምራች ነች። ከ60 ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች ያሏት ጣሊያን በሕገ መንግሥቱ የሃይማኖት ነፃነትን አረጋግጣለች። ሆኖም፣ አብላጫው (74%) የሚሆነው ሕዝብ ካቶሊካዊ እምነተ ተከታይ ሲሆን፣ 9.3% የሚሆኑት ካቶሊክ ያልሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው፣ በቅርብ ጊዜ በተፈጠረው ፍልሰት ምክንያትም እያደገ የመጣ በአሁኑ ጊዜ በ3.6% የእስልምና እምነት አሏት። ከእነዚህም ጋር ሌሎች አናሳ ሃይማኖቶች፣አምላክ የለሽነት እና የግኖስቲዝም እምነት እየጨመሩ ነው።

የSDA የተሃድሶ እንቅስቃሴ መልእክት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰበከው በ1926 በጣሊያን ነበር፤ ነገር ግን የመጀመሪያዎቹ የተሃድሶ አራማጅ ቡድኖች የተደራጁት 1939/40 ነበር። ከ1990ዎቹ ጀምሮ ከደቡብ አሜሪካ፣ ከፖርቱጋል እና ከዚያም ከሮማኒያ የመጡ ሚስዮናውያን በመምጣታቸው፣ ስራው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሌሎች ቡድኖችን በማቋቋም አድጓል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መልእክቱ በጽናት ሲታወጅ ነበር፤ በክልሉም ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተቋቁሟል፤ ዛሬ ላይ በ6 አብያተ ክርስቲያናት የተከፋፈሉ ከ130 በላይ አባላት፣ በሁለት ቡድኖች እና የተለዩ አባላት አሉን። በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ሰሜን ምስራቅ ርቀ በሚገኘው ትሪስቴ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አንድ የቤተክርስቲያን ሕንፃ ብቻ ነው ያለን። ሆኖም ግን፣ ለሕዝባችን የጥንካሬ እና የመንፈሳዊ እድገት ምሰሶ ሆኖ የሚያገለግል የስትራቴጂካዊ ቦታ አስቸኳይ አስፈላጊነትን እናያለን።

ይህ ቦታ የቀጠናው ዋና መሥሪያ ቤት ይሆናል እናም ማዕከላዊ የሆነው የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እንደ የሚሲዮናዊ ስልጠና ሴሚናሮች፣ የሙዚቃ ፕሮግራሞች፣ በጤና ላይ ያተኮሩ ኮንፈረንሶች የሚስዮናዊ ፕሮጀክቶች እና በእፅዋት ላይ የተመሰረቱ የምግብ ማብሰል ትምህርቶች ባሉ የታቀዱ ተግባራት ላይ ብዙ ወንድሞች እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል። ይህ ቦታ በጣሊያን የጌታን ሥራ ለማራመድና ለማስፋት መሰረታዊ እንደሚሆን እናምናለን፣ ስለዚህ በመላው ዓለም ያሉ ወንድሞቻችንን፣ እህቶቻችንን እና ጓደኞቻችንን በስጦታዎቻቸው በልግስና እንዲደግፉ እንጋብዛለን።

በየሱስ ጸጋ እና በእርስዎ ትብብር ይህንን ግብ እናሳካለን፣ በዚህች አገር ወንጌልን እናጠናክራለን፣ የመዳንን መልእክትም ለብዙ ነፍሳት እናደርሳለን። ጌታ ይባርካችሁ፤ በብዙ ዋጋ ይክፈላችሁ!

ወንድሞቻችሁ፡ ከጣሊያን ቀጠና

# ስለ ትንቢት መግቢያ

**የማስታወሻ ጥቅስ፡ “ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ።” (2ኛ ጴጥሮስ 1፡19)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 593–602.

“*ታሪክና ትንቢት የምድር ሁሉ አምላክ የብርሃን ተሸካሚ በሆኑት ምርጦቹ ለዓለም ምሥጢርን እንደሚገልጥ ይመሰክራሉ።*”—Bible Training School, December 1, 1912.

## 1. ውሰን የሌለው አእምሮ እሁድ፡ መጋቢት 20

## ሀ. እግዚአብሔር ብቻ ሊያየው የሚችለው ምንድነው? ኢሳይያስ 46:9፣ 10

“*እኔ ነኝ ማለት ዘላለማዊ መገኘት ነው። ያለፈው፣ የአሁኑ እና የወደፊቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ናቸው። በሩቅ ያለፉትን የታሪክ ክስተቶች እና የወደፊቱን ጊዜ ልክ እኛ በየቀኑ ሲከሰት እንደምናያቸው እርሱ የሚከሰቱትን ነገሮች በግልፅ ያያል*”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 1, p. 1099.

## ለ. ጌታችን በጥበቡ ምን ያደርጋል? ዳንኤል 2:20–22።

“*ከምድር ጥፋት ሁሉ በላይ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጧል፤ ሁሉም ነገር ለመለኮታዊው ቅኝት ክፍት ነው፤ እናም ከታላቁና ከተረጋጋው ዘላለማዊነቱ እርሱ ከሁሉ የተሻለውን ያዛል።*”—The Ministry of Healing pp. 417.

“*በሰው ልጅ ታሪክ ሁሉ የግዛቶች ማደግ፣ የነገሥታት መነሳትና ውድቀት፣ የታሪክ ይዘት፣ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ በሰው ኃይልና ውሳኔ የሚከናወኑ መስለው ይታያሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር መጋረጃውን ገልጦ ሲያሳየን ኃያልና መሐሪ የሆነው አምላክ በጥበቡ የሰውን ልጆች ሸኩቻና የኃይል ትግል ይቆጣጠራል።*—Prophets and Kings, pp. 499, 500.

### ሀ. እግዚአብሔር ፈቃዱን በምድር ላይ ለማድረግ ዝግጁ ሲሆን ምን ያደርጋል? አሞጽ 3:7፤ ራዕይ 1:1

*"በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም" አሞጽ 3:7፣ "ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።"*

*ዘዳግም 29:29 እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሰጥቶናል፤ ትንቢታዊ ቅዱሳት መጻሕፍትን በአክብሮት እና በጸሎት በማጥናት በረከት ይገኛል።"*—The Desire of Ages, p. 234.

### ለ. እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ መልእክቶችን ለምን ይልክልናል? 1ኛ ዮሐንስ 3:1፤ ዮሐንስ 1:12፤ ቆላስይስ 1:25–28

*"መጽሐፍ ቅዱስ ድንቅ መጽሐፍ ነው። ያለፉትን ምዕተ ዓመታት የሚከፍትልን ታሪክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ባይኖር ኖሮ ስላለፉት ዘመናት ክስተቶች ለግምቶችና ለተረቶች እንሰጥ ነበር። የወደፊቱንም የሚገልጥ ትንቢት ነው። የመዳንን እቅድ የሚገልጥልን ሲሆን፣ ዘላለማዊ ሞትን የምናመልጥበትን መንገድም የሚያመለክተን የእግዚአብሔር ቃል ነው።ምንም እንኳ ዋጋ ቢኖራቸውም፤ ዓለምን ካጥለቀለቁት መጻሕፍት ሁሉ ይልቅ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሊደነቅ እና ሊጠና የሚገባው የመጽሐፍት ሁሉ መጽሐፍ ነው። የዚህን ዓለም ታሪክ ብቻ ሳይሆን ስለሚመጣውም ዓለም መግለጫን ይሰጣል። ስለ ዩኒቨርስ ድንቅ የሆኑ ስርአቶችንና መመሪያን ይዟል፣ የሰማያትና የምድርን ባለቤት ባሕርይ እንድንረዳም ይገልጥልናል። ለሰው ልጆችም በውስጡ የእግዚአብሔር መገለጥ አለበት።"*—The Signs of the Times, January 30, 1893.

### ሐ. ልንፈልገው የሚገባን በጣም አስፈላጊው እውቀት ምንድን ነው? ኤርምያስ 9:23፣ 24፤ ዮሐንስ 17:3፤ ኤፌሶን 3:17–19

*"በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሲሆን አእምሮአችን ጥልቅ ለሆኑ ሀሳቦችና ለከፍተኛ ፍላጎት ተገዢ ይሆናል። በእርሱም ከአበውና ከነቢያት ጋር ኅብረት በማድረግ ዘላለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰዎች ውስጥ ሲናገር መስማት እንችላለን። በእርሱ ውስጥ የሰማይ ባለግርማ ስለ እኛ ራሱን ዝቅ በማድረግ የጨለማን ኃይሎች ብቻውን በመቋቋም፤ በእኛ ምትክ ድልን ለማግኘት ዋስትናችን ሲሆን እናያለን። እንደዚህ ባሉ ጭብጦች ላይ በአክብሮት ማሰላሰል ልብን ያለሰልሳል፣ ያጠራል፣ ያበለፅግማል፤ በተመሳሳይ ጊዜም አእምሮን በአዲስ ጥንካሬ እና ጉልበት ማነሳሳት ይችላል።*—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 25.

# 3. ቃሉን መረዳት ማክሰኞ፣ መጋቢት 22

## ሀ. ትንቢትን ጨምሮ ቅዱሳት መፅሃፍትን ለመረዳት የማን እገዛ ያስፈልገናል? ዮሐንስ 16:7–13

እግዚአብሔር በዚህ ምድርም ቢሆን እውነት ሁልጊዜ ለሕዝቡ እንዲገለጥ ይፈልጋል። ይህም እውቀት የሚገኝበት በአንድ መንገድ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት የምንችለው ቃሉ በተሰጠበት በመንፈሱ ብርሃን ብቻ ነው።—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 703.

"መጽሐፍ ቅዱስን በምንም ዓይነት ያለፀሎት ማጥናት የለብንም። ገፆቹን ከመግለጣችንና ከማንበባችን በፊት መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንዲገልጥልንና እንድናስተውል እንዲረዳን ልንጠይቀው ይገባል። እግዚአብሔርም ይገልጥልናል። አንድ ጊዜ ናትናኤል ወደ የሱስ ሲመጣ አዳኛችን ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ «ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ» ናትናኤልም ሲመልስ «ከወዴት ታውቀኛለህ» አለው። የሱስ ሲመልስ «ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ» አለው። (ዮሐ. 1፥ 47-48)። ዛሬም የሱስ የእውነትን ብርሃን ለማግኘት በሰውር ሆነን ወደእርሱ ስንፀልይ እያንዳንዳችንን ያየናል። ቅዱሳን መላዕክት እራሳቸውን ዝቅ አድርገው በትህትና የእግዚአብሔርን አመራር ከሚሹ ሁሉ ጋር ይሆናሉ።"—Steps to Christ, p. 91.

## ለ. ትንቢትን ስናጠና የራሳችንን አመለካከት አለመከተል ለምን ይጠቅማል? 2ኛ ጴጥሮስ 1:19–21

"በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ከዚህ በፊት በአእምሮአችሁ ይዛችሁት የነበረውን ግምትም ሆነ በውርስና በሂደት ያዳበራችሁትን አሳብ በምርምር በር ላይ አስቀምጡት። መጽሐፍ ቅዱስን ለራሳችሁ አሳብ ድጋፍ እንዲሆን የምታጠኑ ከሆነ በፍጹም እውነትን ማግኘት አትችሉም። እነዚህን አሳቦች በበር ላይ ተውና ዝቅ ባለ ልብ ጌታ የሚላችሁን ለመስማት ሂዱ። ትሁት የሆነ የእውነት ፈላጊ በክርስቶስ እግር ሥር ቁጭ ብሎ ከእርሱ ሲማር ቃሉ ማስተዋልን ይሰጠዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት በራሳቸው ማስተዋል እጅግ ጠቢባን ለሆኑ ክርስቶስ እንዲህ ይላል፡- ለደህንነት ጠቢባን መሆን ከፈለጋችሁ በልባችሁ ትሁታንና የዋሃን ሁኑ።

"ቃሉን ከዚህ በፊት በነበራችሁ አስተሳሰብ አታንብቡ። ነገር ግን አስቀድሞ ከመወሰን ነፃ በሆነ አእምሮ በጥንቃቄ በጸሎት መርምሩ። ስታነቡ ሳለ ለአእምሮአችሁ የሚያሳምን አሳብ ከመጣላችሁና ከዚህ በፊት ይዛችሁ የኖራችሁት አሳብ ከቃሉ ጋር የማይስማማ ከሆነ ቃሉ ከእናንተ አሳብ ጋር እንዲገጥም ለማድረግ አትሞክሩ። እናንተ የነበራችሁ አስተሳሰብ ከቃሉ ጋር ገጣሚ እንዲሆን አድርጉ። ከዚህ በፊት የምታምኑትም ሆነ ስትለማመዱት የኖራችሁት ነገር ማስተዋላችሁን እንዲቆጣጠር አትፍቀዱ። ከሕጉ ተዓምራትን ለማየት የአእምሮ ዓይኖቻችሁን ክፈቱ። የተጻፈው ምን እንደሆነ አግኙና እግራችሁን በዘላለማዊው ዓለት ላይ አቁሙ።—Messages to Young People, p. 260.

## ሀ. እግዚአብሔር ቃሉን እንዴት ይሰጠናል? እንዴትስ ማጥናት አለብን? ኢሳይያስ 28:9፣ 10

“የእግዚአብሔር ቃል እውነትነት ማስረጃው በራሱ በቃሉ ውስጥ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚፈተቱት ራሳቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ጥልቅ ትርጉም ለአእምሯችን የሚገለጠው በመንፈሱ ነው።” —Testimonies for the Church, vol, 8, p. 157.

“ትምህርቱን በአድናቆት የሚቀበል መንፈስ ያለው ማናቸውም ሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚያነብበት ጊዜ አንዲት ገጽ እንኳ ብትሆን ጠቃሚ ሀሳቦች ሳያገኝ አያልፍም። ነገር ግን ዋናው ጥቅም የሚገኘው አልፎ አልፎ በሚደረግና ባልተያያዘ ጥናት አይደለም። ታላቁ የእውነት ሥርዓት ችኩልና ግዴየለሽ በሆነ አንባቢ አማካይነት የሚሰጥ አይደለም። ብዙዎቹ የወርቅ መዝገቦች ከላይኛው የመሮት ልባስ ሥር በጣም ጠለቅ ብለው ነው የሚገኙት። ሊደርስባቸው የሚችሉትም ትጋት በተሞላበት ምርምርና ባላቋረጠ ጥረት ነው። በታላቁ ጥቅል ውስጥ የሚካተቱ እውነቶች ተፈልገው መሰብሰብ አለባቸው። «ከዚህም ጥቂት ከዝያም ጥቂት።» ኢሳ 28፡10

“እንግዲህ እንዲህ እየተፈለጉ ሲሰበሰቡ አንደኛው ከሌላው ጋር ፍፁምና በትክክል የሚስማማ ይሆናል። እያንዳንዱ ወንጌል የሌሎቹ ደጋፊ፣ እያንዳንዱ ትንቢት የሌላው መግለጫና ማብራሪያ፣ እያንዳንዱ የልማት እውነት ለሌላው ውነት መግለጫ ይሆናል። የአይሁዶች የኢኮኖሚ አያያዝ ዓይነት በወንጌል ውስጥ ተብራርቷል። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እያንዳንዱ መሠታዊ ሀሳብ የራሷ ቦታ አላት። እያንዳንዱ እውቀትም የራሷ የሆነ ፍሬ አላት። በንድፍና በአፈፃፀም ላይ ያለው የተሟላ ቅርጽ ባለቤት ለሆነው ደራሲ ምስክርነት ይሰጣሉ። እንዲህ ዓይነቱን ግሩም ድንቅ ቅርጽ ፈልፍሎ ሊያንጸው የሚችለው የሰው አእምሮ ሳይሆን ሊያስበው የሚችለው ወሰን የሌለበት አምላክ ብቻ ነው።”—Education, pp. 123, 124.

## ለ. ሁሉም የመፅሃፍ ቅዱስ አንቀፆች አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው? ማቴዎስ 4፥4፣ ሉቃስ 24፥27

“የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በተመለከተ ማንም ሰው የሚለንን ተከትለን መሄድ የለብንም። የእግዚአብሔርን ቃል በግላችን ልናጠናው ይገባል። . . . አዕምሮአችን እየበሰለ የሚሄደው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በተመለከተ አንድን ጥቅስ ከሌላው ጥቅስ ጋር እያጣቀስን ፣ መንፈሳዊ ነገርን ከመንፈሳዊ ነገር ጋር እያነፃፀርን በምናጠናበት ጊዜ ነው።

“በማስተዋልና በፀሎት ካላጠናነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ እውቀትን ማግኘት አንችልም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግልፅ በመሆናቸው ምንም አያሳስቱም ቢሆንም ትርጉማቸው ሙሉ በሙሉ ግልፅ ያልሆኑ በጥንቃቄ ሊጠኑ የሚገባቸው አንዳንድ ጥቅሶች አሉ። እነዚህን ጥቅሶች ከሌሎች ጥቅሶች ጋር ማነፃፀር ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ መፀለይና በጥንቃቄ መመርመር ግድ ነው። በዚህ መልኩ ከመረመርን ትልቅ ሽልማት እናገኝበታለን። ልክ አንድ ማዕድን ቆፋሪ በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኘውን የከበረ ድንጋይ በጥልቀት ቆፍሮ እንደሚያወጣ፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተደበቁትን እንቁዎች ለማግኘት ተግቶ የሚፈልግ ማንም ሰው ለሕይወቱ እጅግ ጠቃሚ እውነቶችን ያገኛል። ላይ ላዩን ለሚያነብ ሰው ግን እነዚህ እውነቶች አይታዩትም። ወደ ልባችን የምናስገባቸውና የምናስቀምጣቸው የእግዚአብሔር ቃሎች ከሕይወት ፏፏቴ እንደሚፈስ ምንጭ ይሆኑልናል።”—Steps to Christ, pp. 89–91.

## 5. በጥበብ ማጥናት ሐሙስ፣ መጋቢት 24

## ሀ. አመለካከታችን እና ምርጫዎቻችን የትንቢቶቹን ትርጉም የመለየት ችሎታችን ላይ እንዴት ተፅዕኖ ያደርጋሉ? ዳንኤል 12:10፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:1–8

"ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመመርመር የተነሳህበት መንፈስ ከጎንህ የሚቆመውን ረዳት ባሕርይ ይወስናል። ከብርሃን አለም የመጡ መላእክት በትህትና መለኮታዊ መመሪያን ከሚፈልጉ ጋር ይሆናሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ አክብሮት በጎደለዉ ሁኔታ፣ በራስ በመመካት ስሜት፣ ልብ በጭፍን ጥላቻ በተሞላበት ሁኔታ ከተከፈተ፣ ሰይጣን ከጎንህ ይሆናል፣ እናም የእግዚአብሔርን ቃል ጠማማ በሆነ መንገድ በፊታችን ያስቀምጣል።"—Testimonies to Ministers, p. 108.

"ሰይጣን ዳንኤልንና የዮሐንስ ራዕይን ማስተዋል አይቻልም ብሎ ብዙ አማኞችን አሳምኖአቸዋል። ነገር ግን እነዚህን ትንቢቶች በማጥናት ስለሚገኘው በረከት የተሰጠው ተስፋ ግልጽ ነው።"—Prophets and Kings, p. 547.

## ለ. እውነትን በግል የመተግበር አስፈላጊነትን አብራራ። ራዕይ 22:7፤ ማቴዎስ 7:24–27፤ ዮሐንስ 7:17

"ትሑታን ለመማር ፈቃደኛ ስለሆኑ በጌታ ይመራሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና ለማድረግ ልባዊ ፍላጎት አላቸው። የአዳኙ ቃል ኪዳን "ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል።" ይላል። ዮሐንስ 7:17። በሐዋርያው ያዕቆብም "ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።" ብሎ አውጇል። ያዕቆብ 1:5። ነገር ግን የተስፋ ቃሉ ጌታን ሙሉ በሙሉ ለመከተል ፈቃደኛ ለሆኑት ብቻ ነው።"—Patriarchs and Prophets, p. 384.

"የእግዚአብሔርን ምሥጢር ማወቅ ከፈለክ፣ በምንም አይነት ሁኔታ የእውነትን ግልጽ ቃል መከተል አለብህ። ታዛዥነትን እንደ መርህ አድርገህ መቀበልና በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን ነገር መፈለግ አለብህ።—Fundamentals of Christian Education, p. 125.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ መጋቢት 25

1. በእውቀት ረገድ እግዚአብሔር ራሱን ከሌሎች ሁሉ የሚለየው እንዴት ነው?
2. እግዚአብሔር በነቢያት ጽሑፎች ውስጥ ምን ይገልጥልናል፤ ለምን?
3. የእግዚአብሔርን ቃል ስንከፍት ምን ዓይነት እርዳታ ለማግኘት መጸለይ አለብን?
4. በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ምን ዓይነት ጥረት ማድረግ አለብኝ?
5. በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያገኘሁትን እውነት ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝን?

# ሰንበት፣ ሚያዝያ 03፣ 2018 — 2ኛ ትምህርት

## ለነገሥታት የተላከ የእግዚአብሔር መልእክተኛ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “ለእነዚህም ለአራቱ ብላቴኖች እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ እውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው፤ ዳንኤልም በራእይና በሕልም ሁሉ አስተዋይ ነበረ።” ዳንኤል 1፡ 17**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Prophets and Kings, pp. 479–490.

*“የዳንኤልና የጓደኞቹ ሕይወት እግዚአብሔር ፈቃዳቸውን ለእርሱ ፈቃድ ለሚያስገዙ ሁሉ የሚያደርገውን ታላቅ ድርጊት ያሳያል።”*—Prophets and Kings, p. 490.

### 1. ወደ ባቢሎን የተወሰዱ ምርኮኞች — እሁድ፣ መጋቢት 27

### ሀ. ዳንኤል ወደ ባቢሎን እንዴት ሄደ? ዳንኤል 1፡1–7

### ለ. ዳንኤል ከንጉሡ ማዕድ ስለመብላት ባደረገው ውሳኔ ምን ውጤት ተገኘ? ዳንኤል 1፡8–16

*“በንጉሡ ማዕድ የቀረበው ምግብ ለጣዖታት መስዋዕት ሆኖ የተረፈና ለጣዖታት መስዋእት ሆኖ የቀረበ ነበር። ያን ምግብ መብላት የባቢሎንን አማልክት እንደማምለክ ይቆጠር ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው ዕምነት ዳንኤልንና ጓደኞቹን ምግቡን እንዲበሉ አልፈቀደላቸውም። . . .*

*ምቾት የአካላቸውን፣ የአእምሮአቸውንና መንፈሳዊ እድገታቸውን እንዲያደኩርባቸው አልፈለጉም።”*—Prophets and Kings, pp. 481, 482.

*“ዳንኤልና ባልደረቦቹ ፈተና ሲመጣ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በጽድቅና በእውነት ጎን አደረጉ። በብልሃት እንጂ በስሜታዊነት አልተንቀሳቀሱም ነበር። ቀድሞውኑ ሥጋ የምግባቸው አካል እንዳልነበረ ሁሉ ወደፊትም ወደ ምግባቸው እንደማይገባ ወሰኑ። እናም በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ ለሚሳተፉ ሁሉ የወይን ጠጅ መጠቀም የተከለከለ ስለነበር ከዚህ መጠጥ ላለመውሰድ ወሰኑ።”*—In Heavenly Places, p. 261.

### ሐ. ሙከራውን (ፈተናውን) እና የንጉሡን ምርመራ ግለፅ። ዳንኤል 1:17–21።

## 2. በእሳት መፈተን ሰኞ፣ መጋቢት 28

## ሀ. በሞት ፍርሃት ስር፤ ዕብራውያን ለሁለተኛው ትእዛዝ ባላቸው ታማኝነት ረገድ እንዴት ነበር የተፈተኑት? ዳንኤል 3:1–15

"ሁሉም ጉልበታቸውን ለወርቁ ምስል አላንበረከኩም። ከዚያ ሁሉ ሕዝብ መካከል የሰማይን አምላክ ፈቃድ ላለመጣስ የወሰኑ ሦስት ሰዎች ነበሩ። አምላካቸው የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ ነው። ለሌላ ለማንም ላለመስገድ ወስነው ነበር።"—Prophets and Kings, p. 506.

## ለ. እምነታቸውንና ታዛዥነታቸውን እንዴት መጠበቅ ቻሉ? ዳንኤል 3:16–18፤ ኢሳይያስ 43:1፣ 2

"የንጉሡ ዛቻ ከንቱ ነበር። ሰዎቹ በዩኒቨርስ አምላክ እንዳያምኑ ማድረግ አልቻለም። ከአባቶቻቸው ታሪክ እንደተማሩት፣ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ውርደት ሞትና ጥፋት እንደሚያስከትል ያውቃሉ። እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው። የእውነተኛ ብልጽግና መሠረት ነው። በተረጋጋ መንፈስ ,ከእሳቱ አጠገብ ሆነው "ናቡከደነጾር ሆይ፣ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። ነገር ግን የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነናል። ንጉሥ ሆይ" ንግግራቸውን ሲቀጥሉ እነርሱን በማዳን የእግዚአብሔር ክብር እንደሚገለጥ በማወቅ፣ እግዚአብሔር እንደሚታደጋቸው በመገንዘቡ ንግግራቸውን በመቀጠል "ነገር ግን ንጉሥ ሆይ እርሱ ባያድነን አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቅ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት"።"—Ibid., pp. 507, 508.

## ሐ. እግዚአብሔር እነርሱን በማዳኑ እንዴት ተከበረ? ዳንኤል 3:19፣ 20፣ 24–28

"ንጉሡ ከንጉሣዊ ዙፋኑ ላይ ሆኖ የተቃወሙትን ሰዎች ሙሉ በሙሉ ሲጠፉ ለማየት ይጠብቅ ነበር። ነገር ግን የድል ስሜቱ በድንገት ተለወጠ። . . . ንጉሡ በእሳት መካከል አራተኛ የእግዚአብሔርን ልጅ አስተዋለው።...

"አሁንም ታላቅነቱና ክብሩ ተረስቶ፣ ናቡከደነፆር ከዙፋኑ ወረደ. . . ።

"ከዚያም ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ምንም እንዳልተጎዱ እራሳቸውን እያሳዩ ወደ ሕዝቡ ፊት ወጡ። . . . . እንደዛ ሲከበር የነበረው ታላቁ የወርቅ ምስል ተረሳ። በሕያው እግዚአብሔር ፊት ሰዎች ፈሩ ተንቀጠቀጡም።—Ibid., pp. 509, 510.

## 3. ኩራት እና ትሕትና ማክሰኞ፣ መጋቢት 29

## ሀ. እግዚአብሔር ከንጉሡ ናቡከደነፆር ጋር እንዴት ተነጋገረ? ዳንኤል 4:4–7

*"ይህ ታላቅ ንጉሥ፣ በኩራትና በትዕቢት ልቡ አብጦ የእውነተኛ ታላቅነት ከሆነው ከትህትና መንፈስ መራቁ አያስገርምም። . . . እግዚአብሔር በምሕረቱ ናቡከደነጾርን ለማስጠንቀቅ ሌላ ሕልም አሳየው።"*—Prophets and Kings, p. 515.

## ለ. ዳንኤል በመጨረሻ ሕልሙን እንዲተረጉም ሲጠራ ለንጉሱ የሰጠው ምክር ምን ነበር? ዳንኤል 4:20–27

*"ለዳንኤል ግን ፍቺው ግልጽ ነበር። የሕልሙ ግን ከባድነት አስደነገጠው። . . . በኩራቱና በማን አለብኝ ስሜቱ ምክንያት በናቡከደነጾር ላይ የሚወርደውን ቅጣት የመናገር ከባድ ኃላፊነት እንደተጣለበት ዳንኤል ተገነዘበ።"*—Ibid., p. 517.

*"ዳንኤል ሕልሙን በታማኝነት ከተረጎመ በኋላ፣ ኩሩው ንጉሥ ትክክል የሆነውን በማድረግ የተጋረጠውን ጥፋት እንዲያስወግድ ንስሐ እንዲገባና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አሳሰበው።"*—Ibid., p. 518.

## ሐ. በከባድና በውርደት በተሞሉ ተሞክሮዎች ለመማር የተገደደው ንጉሡ በዳንኤል አገልግሎት እግዚአብሔርን እንዴት አከበረው? ዳንኤል 4:34–37።

*"ለሰባት ዓመታት ናቡከደነጾር መተረቻ ሆነ። ለሰባት ዓመታት በዓለም ሁሉ ፊት ተዋረደ። ከዚያ በኋላ አእምሮ ተመለሰለት። በትህትና ወደ እግዚአብሔር ወደ ላይ እያየ ቅጣቱ የእግዚአብሔር እጅ እንደነበረበት ተገነዘበ። በአደባባይ ጥፋቱን ተናዝዞ እግዚአብሔር በምሕረቱ ከወደቀበት እንዳነሳው መሰከረ። . . .*

*"ኩሩ የነበረው ንጉሥ ትሁት የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ። ጨቋኝና ጨካኝ የነበረው አምባ ገነን ንጉሥ ጠቢብና ሩህሩህ ገዥ ሆነ። የሰማይን አምላክ ይሳደብ የነበረው አሁን የቅዱሳን ቅዱስን ኃይል ተገነዘበ። ከልቡ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ለማስፋፋትና የሕዝቡን ደስታ ለማብዛት ተሰለፈ።. . ."*

*"በዓለም ላይ ታላቅ የነበረው መንግሥት እርሱን እንዲያከብር የነበረው የእግዚአብሔር እቅድ ተፈጸመ። ስለ ናቡከደነጾር በታሪክ የተመዘገበው የመጨረሻ ዘገባ በአደባባይ (በይፋ) ስለ እግዚአብሔር ቸርነትና ኃይል የሰጠው ምስክርነት ነበር።"*—Ibid., pp. 520, 521.

## 4. በግድግዳው ላይ የተጻፈው ጽሑፍ    ረቡዕ፣ መጋቢት 30

### ሀ. የናቡከደነፆር ዘር የሆነው ብልጣሶርን በሰማይ አምላክ ላይ የንቀትን ተግባር በፈጸመ ጊዜ በድንገት ያስቆመው አስደናቂ ክስተት ምንድን ነው? ዳንኤል 5:1–6

"በወጣትነቱ የንጉስነቱን ዙፋን ለመጋራት ችሎ የነበረው ብልጣሶር በስልጣኑ በመመካት ልቡ በሰማይ አምላክ ላይ ታበየ። የአምላክን ፈቃድ ለማወቅና ይህንን አምላክ ለመታዘዝ ያለበትን ሃላፊነት ለመረዳት ብዙ እድሎች ገጥመውት ነበር። አያቱ ንጉስ ናቡከደነጾር በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የደረሰበትን ቅጣት ከማህበረሰቡ፣ ከራሱ ከንጉስ ናቡከደነጾር ንግግርና በተዓምራዊ መንገድ ወደ መንግስቱ መመለስ ስለመቻሉ ሰምቶ ስለነበር በሚገባ ያውቅ ነበር። ነገር ግን ብልጣሶር ምቾትና የራስ ክብር ፈጽሞ ሊረሳ የማይገባውን ትምህርት እንዲያጠፋበት ፈቀደ።"—Prophets and Kings, pp. 522, 523.

### ለ. ዳንኤል የእግዚአብሔርን መልእክት ለአረማዊ ንጉሥ ለማድረስ እንደገና እንዴት ተወሰደ? ዳንኤል 5:8–16

"ነቢዩ በመጀመሪያ ብልጣሶር ሊያተርፈው ይችል የነበረውን ነገር ግን የትህትና ትምህርቶችን ያልተማረባቸውን የሚያውቃቸውን ጉዳዮች አስታወሰው። የናቡከደነጾርን ሐጢአትና ውድቀት እንዲሁም ጌታ ምን እንዳደረገበት ነገረው። ግዛትና ክብር ተሰጥቶት እንደነበር፤ ኋላም የመለኮት ፍርድ በኩራቱ ምክንያት እንደደረሰበትና ለእስራኤል አምላክ ሐይልና ምህረት የሰጠውን እውቅና ከነገረው በኋላ በድፍረትና በግልጽ ቃላት ብልጣሶርን ስለታላቅ ድክመቱ ወቀሰው።"—Ibid., p. 529.

### ሐ. የዳንኤል ትርጓሜ በዚያች ሌሊት እንዴት ተፈጸመ? ዳንኤል 5:17፣ 25–31

"በግብዣው አዳራሽ ሳሉ በነዚያ ጥፋት የታተመባቸው ሰዎች ተከቦ ሳለ ንጉሱ "ከተማው እንደሚወሰድ" በመልዕክተኛው ተነገረው። እነዚህ ጥፋት የታተመባቸው ሰዎች በተከበቡበት የግብዣ አዳራሽ ውስጥ ንጉሱ አስተማማኝ መሳሪያ እንዳለው እየተሰማው ባለበት "ከተማዋ በጠላት እንደተወሰደች" . . . በመልዕክተኛው ተነገረው። እርሱና ባለሟሎቹ በተቀደሱት የያህዌ እቃዎች እየጠጡና ከብርና ከወርቅ የተሰሩ አማልዕክቶቻቸውን እያመለኩ ሳለ ሜዶናውያንና ፋርሶች የኤፍራጥስን ወንዝ አቅጣጫ በማስቀየር ጥበቃ ወደሌላት ከተማ እያመሩ ነበር። የቂሮስ ሰራዊት አሁን በቤተመንግስቱ ግድግዳዎች ስር ቆመዋል፤ ከተማዋ "እንደአንበጣ" (ኤር 51፡14) በጠላት ወታደሮች ተሞልታለች። የድል አድራጊነት ጩኸታቸውም በአስገራሚ ሁኔታ ሲፈነጥዙ ከነበሩትና አሁን ግን ከሚያለቅሱት ድምጽ በላይ ከፍ ብሎ ይሰማ ነበር።"—Ibid., p. 531.

## 5. በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ሐሙስ፣ ሚያዝያ 01

## ሀ. ዳንኤል ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት ለምን መከራን አስከተለ? ዳንኤል 6:1–5

"ለዳንኤል የተሰጠው ክብር የመንግሥቱን መሪዎች ቅናት ቀሰቀሰ፣ እርሱንም የሚከሱበትን ምክንያት መፈለግ ጀመሩ..

"የዳንኤል ነቀፋ የሌለበት ባህርይ የጠላቶቹን ቅናት የበለጠ አነሳሳ። . .

"ከዚያም መሪዎቹና መሳፍንቱ አንድ ላይ በመመካከር፣ ነቢዩን እናጠፋለን ብለው ተሰፋ ያደርጉበትን እቅድ አወጡ።" —Prophets and Kings, pp. 539, 540.

## ለ. ዳንኤል ለማቅማማት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምን ተከሰተ? ዳንኤል 6:11–17።

"ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆኑ የሚያስከትለውን ውጤት በሚገባ ቢያውቅም፣ መንፈሱ ግን አላቅማማም። እርሱን ለማጥፋት እያሴሩ በነበሩ ሰዎች ፊት፣ ከሰማይ ጋር ያለው ግንኙነት እንደተቋረጠ መስሎ እንዲታይ እንኳን አልፈቀደም። ንጉሡ የማዘዝ መብት ባለው ጉዳይ ሁሉ ዳንኤል ይታዘዝ ነበር፤ ነገር ግን ንጉሡም ሆነ ትዕዛዙ ከነገሥታት ንጉሥ ለሆነው ካለው ታማኝነት እንዲያፈነግጥ ሊያደርጉት አልቻሉም።"—Ibid., p. 542.

## ሐ. እግዚአብሔር በባሪያው በኩል እንደገና እንዴት ከበረ? ዳንኤል 6:19–23፣ 27

"እግዚአብሔር የዳንኤል እርሱን ጠላቶች ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንዳይጥሉት አልከለከላቸውም፤ ክፉ መላእክትና ክፉ ሰዎች እስከዚያ ድረስ ዓላማቸውን እንዲያሳኩ ፈቅዷል፤ ነገር ግን ይህን ያደረገው የባሪያውን መዳን የበለጠ ግልጽ ለማድረግና የእውነትና የጽድቅ ጠላቶችን ሽንፈት የበለጠ እንዲጎላ ለማድረግ ነበር። 'የሰው ቁጣ እንኳ ለክብርህ ይሆናል' (መዝሙር 76:10) ሲል መዝሙረኛው መስክሯል። 'ከፖሊሲ ይልቅ ትክክል የሆነውን ለመከተል በመረጠው በዚህ አንድ ሰው ድፍረት ምክንያት ሰይጣን እንዲሸነፍና የእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ ብሎ እንዲከበር ተደርጓል።'"—Ibid., pp. 543, 544.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሚያዝያ 02

1. ዛሬ የአራቱን ዕብራውያን ጥበብ የተሞላባቸው ምርጫ እንዴት አርአያ ልናደርገው እንችላለን?
2. በፈተናዎች ውስጥ ማለፍ እንዴት ጠንካራ ሊያደርገንና ለዓለም ምስክርነት በር ሊከፍትልን ይችላል?
3. ንጉሥ ናቡከደነፆር እንዲመለስ ያደረገውን ምን ትምህርት ተማረ?
4. የዛሬዎቹ መሪዎች ከብልጣሶር የመጨረሻዋ የባቢሎን ምሽት ምን ሊማሩ ይችላሉ?
5. የዳንኤል ታሪክ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስደትን እንዲጋፈጡት እንዴት ሊያበረታታው ይችላል?

# የወደፊት ግዛቶች ተገለጡ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ "ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል፤ ነገሥታትን ያፈልሳል፥ ነገሥታትንም ያስነሣል፤ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል።" (ዳንኤል 2፡21)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** Prophets and Kings, pp. 491–502.

*"የሕዝብም ሆነ የግለሰቦች ጥንካሬ፣ ጠንካራ በሚመስሉ እድሎች ወይም በታላቅነታቸው ዝና ውስጥ አይገኝም። የሚለካውም የእግዚአብሔርን ዓላማን በታማኝነት በመፈፀም ነው።"*—Prophets and Kings p. 502።

## 1. አስደናቂ ሕልም እሁድ፣ ሚያዝያ 04

**ሀ. ንጉሥ ናቡከደነፆር ከሚያስጨንቅ ሕልም አይቶ ከተነሳ በኋላ ምን አዘዘ? ዳንኤል 2፡1፣ 2**

**ለ. የንጉሡ አማካሪዎች ላልተለመደው የንጉሱ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት እንዴት ነበር? ዳንኤል 2:3–7።**

*"ንጉሡም ትርጓሜውን በትክክል መናገር ከቻሉ ሕልሙንም መናገር እንደሚችሉ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር ይህንን ሕልም በሰጠው ጊዜ የባቢሎንን ጠቢባን አስመሳይነት ለማጋለጥ ሲል አስፈሪው ትውስታ በአእምሮው ውስጥ ሲቀር ዝርዝር ነገሩን እንዲረሳ አድረገው።"*—The Sanctified Life, p. 34.

**ሐ. ከመንፈስ ዓለም እና ከሞት በኋላ ካለው ሕይወት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ቢናገሩም፤ እነዚህ የባቢሎን ጠቢባን ሰዎች ምን አምነው ተቀበሉ? ዳንኤል 2:8–11**

*"አስማተኞቹ ሕልሙን አለመተርጎማቸው የሚያስከተለውን መዘዝ በመፍራት ለንጉሡ፣ ጥያቄው ምክንያታዊ እንዳልሆነ እና ፈተናው ከማንኛውም ሰው ከሚጠበቀው በላይ መሆኑን ለማሳየት ሞከሩ።"*—Prophets and Kings, p. 492.

## ሀ. ንጉሡ ጠቢባኑ ሕልሙን ለመናገር እና ለመተርጎም ባለመቻላቸው ምን ምላሽ ሰጠ፤ ዳንኤልስ እንዴት ተሳተፈ? ዳንኤል 2:12–16

*"የንጉሡን አዋጅ ድንጋጌዎች ለመፈጸም ሲዘጋጁ በነበሩት መኮንኖች ይፈለጉ ከነበሩት መካከል ዳንኤልና ጓደኞቹ ይገኙበታል። መሞት እንዳለባቸው ሲነገራቸው ዳንኤልም በትዕዛዙ መሠረት በጥበብ የንጉሡን የክብር ዘበኛ አለቃ አርዮክን 'የንጉሡ አዋጅ ለምን እንዲህ ቸኮለ?' ሲል ጠየቀው። አርዮክም ንጉሡ አስደናቂ ሕልሙን በተመለከተ ግራ ስለተጋባና፤ እስካሁን ድረስ ሙሉ እምነት ከጣለባቸው ሰዎች እርዳታ ለማግኘት ያለመቻሉን ታሪክ ነገረው። ዳንኤልም ይህን ሲሰማ በሕይወቱ ሀላፊነትን ወስዶ ወደ ንጉሡ ፊት ገባና ሕልሙንና ፍቺውን እንዲያሳየው አምላኩን እንዲለምን ጊዜ እንዲሰጠው ለመነው።*

*"ንጉሱም በዚህ ጥያቄ ተስማማ። ዳንኤልም ወደ ቤቱ ሄደና ነገሩን ለባልንጀሮቹ ለአናንያ፣ ለሚሳኤልና ለአዛርያ አስታወቀ።" አብረው ከብርሃንና ከእውቀት ምንጭ ጥበብን ፈለጉ። አሁን ባሉበት ቦታ ያስቀመጣቸው እግዚአብሔር እንደሆነ፤ ሥራውን እየሠሩ እና ሀላፊነታቸውን እየተወጡ ስለመሆናቸውን እምነታቸው ጠንካራ ነበር።"*—Prophets and Kings, p. 493.

## ለ. ዳንኤል እና ጓደኞቹ በዚህ አጋጣሚ ከፀለዩት ፀሎት ምን እንማራለን? ዳንኤል 2:17–23።

*"ዳንኤል እና ጓደኞቹ ግራ በመጋባትና በአደጋ ጊዜ ሁልጊዜ መመሪያና ጥበቃ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ይሄዱ ነበር፤ እርሱም ሁልጊዜም እርዳታ እንደሚሰጣቸው አረጋግጦላቸዋል። አሁን በተሰበረ ልብ ለምድር ዳኛ እንደገና ራሳቸውን አስገዙ፤ በዚህ ልዩ እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ ነፃ እንዲያወጣቸው ለመኑ። ልመናቸውም ከንቱ አልነበረም። ያከበሩት አምላክ አሁን አከበራቸው። የእግዚአብሔር መንፈስ በእነሱ ላይ አረፈ፤ ለዳንኤልም 'በሌሊት ራእይ' የንጉሡ ሕልምና ፍቺው ተገለጠለት።"*—Ibid., pp. 493, 494.

*"[አራቱ ዕብራውያን] የእግዚአብሔርን ምሕረት እንደተራ ነገር አላዩም። ይልቁንም ዳንኤል ጓደኞቹን ጠርቶ ጸሎታቸው ስለተሰማና ስለተመለሰ እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ለዩኒቨርሱ ገዥ ለእግዚአብሔርም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያለው የውዳሴና የምስጋናን መሥዋዕት አቀረቡ። (ዳንኤል 2:20–22) ዳንኤልና ባልደረቦቹ የምስጋና ስብሰባ አደረጉ፤ እናም ዩኒቨርሱ ሁሉ በምስጋና ከእነርሱ ጋር ተባበረ።"*—The Youth's Instructor, November 22, 1894.

## ሀ. ዳንኤል ናቡከደነፆርን ስለ ሕልሙ መግለጥ እንዴት አነጋገረው? ዳንኤል 2:24–30

*"እነሆ የተረጋጋውና ራሱን የገዛው አይሁዳዊው ምርኮኛ በዓለም ላይ እጅግ ኃያል በሆነው ንጉሥ ፊት ቀረበ። በመጀመሪያዎቹ ንግግሩ ለራሱ ክብርን ሳይወስድ እግዚአብሔርን የጥበብ ሁሉ ምንጭ አድርጎ ከፍ አደረገው። ንጉሡ "ያየሁትን ሕልምና ፍቺውን ልታሳየኝ ትችላለህን?" ብሎ በጭንቀት ሲጠይቀው "ንጉሡ የጠየቀውን ምስጢር ጠቢባን፣ ኮከብ ቆጣሪዎች፣ አስማተኞችና ጠንቋዮች ለንጉሡ ሊያሳዩት አይችሉም፤ ነገር ግን በሰማይ ምስጢርን የሚገልጥ አምላክ አለ እናም በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር ያሳውቃል።" ሲል መለሰ።*—Prophets and Kings, pp. 494–497.

*"የአይሁዳዊው ምርኮኛ ከፀሐይ በታች እጅግ ኃያል በሆነው ንጉሥ ፊት ቀሞ ነበር። ናቡከደነፆር ምንም ባለጠጋና የተከበረ ቢሆንም እንኳ አእምሮው በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ነበረ። ነገር ግን ወጣቱ ምርኮኛ በአምላኩ የተረጋጋና ደስተኛ ነበር። ከዚያም ዳንኤል ራሱን፣ ጥበቡንና መንፈሳዊነቱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ምቹ አጋጣሚ ያገኘ ቢሆንም የመጀመሪያ ጥረቱ ለራሱ ክብርን ባለመውሰድ እግዚአብሔርን የጥበብ ምንጭ አድርጎ ከፍ ከፍ ማድረግ ነበር።"*—The Youth's Instructor, September 1, 1903.

## ለ. ንጉሡ በሕልሙ ያየውን ምስል አብራራ። ዳንኤል 2:31–33

*"ንጉሱ በሕልሙ አይቶት የነበረውን እያንዳንዱ ነገር ሲደገምለት በታላቅ ትኩረት ይሰማ ነበር፤ ይህንንም ሲሰማ ሲያስጨንቀው የነበረውን ሕልም አስታወሰ፤ የሕልሙንም ትርጉም ለመቀበል ተዘጋጅቶ ነበር።"*—Ibid.

*"የነገሥታቱ ንጉሥ ለባቢሎን ንጉሥ ታላቅ እውነት ሊያስተላልፍ ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር በዓለም መንግሥታት ላይ ሥልጣን እንዳለው፤ ነገሥታትን የመሾምና የማውረድ ኃይል እንዳለው ገለጠለት። የናቡከደነፆር አእምሮ የሰማይ ኃላፊነት እንዳለበት እስኪገባው ደረሰ መንቃት ነበረበት። እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የሚደርሱት የወደፊቱ ክስተቶች በፊቱ ይገለጡ ነበር።"*—Prophets and Kings, p. 498.

## ሐ. ንጉሡ ምስሉን ሲመለከት ምን ሆነ? ዳንኤል 2:34፣ 35

## ሀ. የወርቁ ራስ ትርጉሙ ምንድን ነው? ዳንኤል 2:36–38

*“በንጉሥ ናቡከደነፆር ዘመን፣ ባቢሎን በምድር ላይ እጅግ ባለጸጋና ኃያል መንግሥት ነበረች። ሀብቷና ግርማዋ በመፅሐፍ ቅዱስ በጥቂቱ ተገልጸዋል።”*—The Youth’s Instructor, September 29, 1903.

## ለ. በሚከተሉት ማእድናት የተገለጹት የትኞቹ መንግሥታት ናቸው? ዳንኤል 2:39፣ 40

*“ትንቢት የዓለም ታላላቅ መንግስታትን ፡ ባቢሎን፣ ሜዶ-ፋርስ፣ ግሪክ እና ሮም መነሳትና መተካካትን አብራርቷል።”*—Prophets and Kings, p. 535.

*“ዳንኤል... መንግሥቱ በሌላ እንደሚተካ ለናቡከደነፆር አሳወቀ። ለናቡከደነፆር በእግዚአብሔር ዓለም ውስጥ ያለው ታላቅነቱና ኃይሉ የሚያበቃበት የራሱ ዘመን አለው፣ ሁለተኛ የሚመጣው መንግሥትም የራሱ የሆነ የፈተና ጊዜ አለው። ፈተናውም ብቸኛውንና እውነተኛውን አምላክ ከፍ ከፍ ያደርጋል ወይስ አያደርግም በሚለው ነው። ይህን ባያደርግ፤ ክብሩ ይጠፋል፤ ሦስተኛውም መንግሥት ቦታውን ይይዛል። መታዘዙ ወይም አለመታዘዙ ከታየ በኋላ ይህም መንግስት ደግሞ ያልፋል፤ እንደ ብረትም ጠንካራ የሆነው አራተኛው መንግሥት ዓለምን ይገዛል። እነዚህ በትንቢት እና በታሪክ ገጾች ላይ የተመዘገቡት የዘላለማዊው አምላክ ትንቢቶች፤ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ጉዳዮች ላይ ገዥ መሆኑን ለማሳየት የተሰጡ ናቸው። እርሱ የራሱን ዓላማ ለማሳካት፤ ጊዜንና ዘመናትን ይለውጣል፣ ነገሥታትን ያስወግዳል፣ ነገሥታትንም ያስቀምጣል።”*—The Youth’s Instructor, September 29, 1903.

*“ባቢሎን በብልጽግናዋ እግዚአብሔርን ስለረሳችና የሠው ሥራ ውጤት እንደሆነ በመቁጠር ክብርን ለሠው ስለሰጠች አልፋለች*

*“የሜዶ-ፋርስ መንግሥትም በዘመኑ የእግዚአብሔር ሕግ ከእግር ጫማ በታች ተረግጦ ስለነበር በሰማይ ቁጣ ተጎብኝቷል። እግዚአብሔርን መፍራት በሕዝቡ ልብ ውስጥ ቦታ አልነበረውም። በሜዶ-ፋርስ ጊዜ የነበሩት ዋና ዋና ተግባራት ክፋት፣ ጭካኔ፣ ስድብ እና እርኩሰት ነበሩ።*

*“ከዚያ በኋላም የተከተሉት መንግሥታት የበለጠ ወራዳና ብልሹ ነበሩ። ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ስለተዉ እየተበላሹ ሄደዋል። እርሱን በረሱት መጠን፣ በሞራልና በሥነ ምግባር ሚዛን እየዘቀጡ ወድቀዋል።”*—Ibid., September 22, 1903.

## ሐ. በእግሮችና በጣቶች የተወከሉት መንግሥታት ከሌሎች የሚለዩት እንዴት ነበር? ዳንኤል 2:41–43

*“በናቡከደነፆር ምስል ውስጥ አሁን ያለንበት ጊዜ በጣቶቹ በተከፋፈለ ሁኔታ፣ አንድ ላይ መቆም የማይችልና በሚፈርስ ቁሳቁስ በተወከለበት መንግሥታት ነው።”*—Testimonies for the Church, vol. 1, p. 361.

## ሀ. የዓለምን ኃያላን ሥርዓት የሚያጠፋው የትኛው መንግሥት ነው? ዳንኤል 2:44፣ 45

*"ለናቡከደነፆር እስከ ዘመን ፍጻሜ ድረስ የታየው የታላቁ ምስል ሕልም የተሰጠው በዓለም ታሪክ ውስጥ እርሱ የሚጫወተውን ሚና እና የእርሱ መንግስት ከሰማዩ መንግሥት ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግንኙነት እንዲረዳ ነው። በሕልሙ ትርጓሜ፤ ስለ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት መቋቋም በግልጽ ተነግሮታል።"—*Prophets and Kings, p. 503.

## ለ. የእግዚአብሔር የክብር መንግሥት መቼ ይጀምራል? ዮሐንስ 18:36፤ ማቴዎስ 25:31-34፤ 26:64፤ ራዕይ 6:15–17

*"የእኛ መንግሥታችን ከዚህ ዓለም አይደለም። ጌታችን ከሰማይ ወደ ምድር እንኪመጣ፤ ሥልጣንንና ኃይልን ሁሉ አውርዶ የዘላለም መንግሥቱን እስኪያቋቁም ድረስ እየጠበቅን ነው። . . . ትንቢት የእግዚአብሔር ታላቁ ቀን እንደደረሰ ያሳየናል። እጅግ ፈጥኖም ይመጣል።"—*Testimonies for the Church, vol. 1, pp. 360, 361.

## ሐ. ንጉሡ፣ ዳንኤል ሕልሙን በተሳካ ሁኔታ በመግለጡ ምላሽ የሰጠው እንዴት ነበር? ዳንኤል 2:46-49

*"ዳንኤል ይህን ሕልም በመግለጡ ንጉሡ ለእሱና ለባልንጀሮቹ ክብርና ሥፍራ እንዲሰጥ ምክንያት ሆኗል። . . . የዳንኤል ሦስቱ ጓደኞች በምድሪቱ ላይ አማካሪዎች፣ ፈራጆች እና ገዥዎች ተደረጉ። እነዚህ ሰዎች በከንቱ አልተኩራሩም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ከምድራዊ ገዥዎች ሁሉ በላይ መታወቁን እና መንግሥቱም ከምድራዊ መንግሥታት ሁሉ በላይ መከበሩን አይተው ተደሰቱ።"—*The Youth's Instructor, September 8, 1903.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሚያዝያ 09

1. ንጉሥ ናቡከደነፆር ያምንባቸው ስለነበሩት ጠቢባኑ ምን ተረዳ?
2. የዳንኤል የልመና ጸሎት ሳይሆን የምስጋና ጸሎቱ መመዝገቡ ምን ትርጉም አለው?
3. ዳንኤል በባቢሎን ውስጥ እጅግ ጥበበኛ ሰው ቢሆንም፣ ምን ዓይነት ባሕርይ ነበረው?
4. በተለያዩ ማእድናት የተወከሉትን መንግሥታት ባህሪያት ግለጽ።
5. የድንጋዩ የሕልም ክፍል መቼ ይፈጸማል?

# የዳንኤል የመጀመሪያው ራዕይ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “እነሆም፥ ያ ቀንድ ከቅዱሳን ጋር ሲዋጋ አየሁ፥ በዘመናት የሸመገለው እስኪመጣ ድረስ፥ ፍርድም ለልዑሉ ቅዱሳን እስኪሰጥ ድረስ፥ ቅዱሳኑም መንግሥቱን የሚወስዱበት ዘመን እስኪመጣ ድረስ አሸነፋቸውም።” (ዳንኤል 7፡21፣ 22)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 479–491; Early Writings, pp. 54–56.

*“የዚህ ዓለም ታሪክ ወደ ፍጻሜ እየተቃረብን ስንመጣ፣ በዳንኤል የተመዘገቡት ትንቢቶች እኛ ከምንኖርበት ዘመን ጋር ስለሚዛመዱ ልዩ ትኩረታችንን ይጠይቃሉ።”*—Prophets and Kings, p. 547.

## 1. አራቱ ነፋሳት፣ አራቱ አራዊት እሁድ፣ ሚያዝያ 11

**ሀ. ዳንኤል የመጀመሪያውን ትንቢታዊ ራእዩን መቼ ተቀበለ? ስለእሱስ ምን ምላሽ ሰጠ? ዳንኤል 7:1፣ 15፣ 16 (የመጀመሪያው ክፍል)**

*“ከባቢሎን ውድቀት ጥቂት ቀደም ብሎ፣ ዳንኤል በእነዚህ ትንቢቶች ላይ ሲያሰላስል እና ዘመኑን ለመረዳት እግዚአብሔርን ሲፈልግ፤ ስለ መንግሥታት መነሳትና ውድቀት ተከታታይ ራእዮች ተሰጠው። በዳንኤል መጽሐፍ በሰባተኛ ምዕራፍ ላይ እንደተመዘገበው የመጀመሪያው ራዕይ ትርጓሜ ተሰጥቶታል። ነገር ግን ሁሉም ለነቢዩ ግልጽ አልነበረም።”*—Prophets and Kings, p. 553.

**ለ. የታዩት የተፈጥሮ አካላት ምን ይወክላሉ? ዳንኤል 7:2፤ ራዕይ 17:15፤ ኤርሚያስ 25:31–33።**

**ሐ. መልአኩ የተነሱትን አራት ታላላቅ አራዊት ትርጉም እንዴት አስረዳ? ዳንኤል 7:3፣ 16 (የመጨረሻው ክፍል)፣ 17።**

*“ዓለምን የገዙት ታላላቅ መንግሥታት ለነቢዩ ዳንኤል በአዳኝ አውሬዎች ተመስለው ቀርበዋል።”*—The Great Controversy, pp. 439, 440.

# 2. የተከታተሉ መንግሥታት ሰኞ፣ ሚያዝያ 12

## ሀ. ከአራቱ አውሬዎች የመጀመሪያው ምን ነበር? የትኛውንስ መንግስት ይወክላል? ዳንኤል 7:4፤ ኤርሚያስ 50:17፤ ዕንባቆም 1:6–8

[ባቢሎን] የእግዚአብሔርን ዓላማ አላሟላም፤ ጊዜውም በደረሰ ጊዜ፣ ይህ በጠቢባን ሰዎች የሚተዳደር፤ የትዕቢትና የሥልጣን መንግሥት ተሰበረ፤ አቅመ ቢስ ሆነ። ክርስቶስ ‘ያለ እኔ ምንም ማድረግ አትችሉም’ ብሏል። የባቢሎን ታዋቂ ገዥዎች ራሳቸውን በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ እንደሆኑ አድርገው አላሰቡም። ሁሉንም ግርማቸውንና ክብራቸውን እራሳቸው እንደፈጠሩ አስበው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሲናገር እንደ ጠወለገ ሣር፣ እንደሚጠፋም አበባ ሆኑ። የእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ብቻ ለዘላለም ይኖራል።”—The Youth’s Instructor, September 29, 1903.

## ለ. ሁለተኛው አውሬ እንዴት ነበር የተገለፀው፤ የትኛውንስ መንግሥት ይወክላል? ዳንኤል 7:5

“እያንዳንዱ ሕዝብ ወይም ወደ መደረክ የመጣ ብሔረ በምድር ላይ የራሱን ቦታ እንዲይዝና «ቅዱስ የሆነውን ጠባቂ» ዓላማዎች አሟልቶ ይፈጽም እነደሆነ ይታይ ዘንድ ለራሱ ዕድል ተፈቅዶለታል። ትንቢት በዓለም ላይ የነበሩ ትልልቅ ግዛት የነበራቸው ኃያላን መንግሥታት ውድቀት የባቢሎንን የሜዶንና የፋርስን፣ የግሪክ የሮም አነሳስና ውድቀት ተከታትሎ ተመልክቷል። በእነዚህም እንደ ሆነ ሁሉ ከነዚህ ባነሱ ደካማ መንግሥታትም ጭምር እንደዚሁ ታሪክ አንድ ነገር ደጋግሞ አሳይቷል። እያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሙከራ ጊዜ ነበራቸው። ሁሉም በየተራቸው ወደቁ። ክብራቸውም ተገፈፈ። ኃይላቸው ተለያቸው። በቦታቸውም ሌላው ተተካ።

“ሕዝቦት የእግዚአብሔርን መርሆች ሲቃወሙ ይህ ተቃውሞአቸውም በራሳቸው ላይ ጥፋታቸውን ሲያፋጥን በዚያው ጊዜ ውስጥ የሚገለጠው የመለኮት የበላይ ገዥነት ዓላማዎች በእንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ ሁሉ ይሠራ እንደ ነበረ ነው።”—Education, pp. 176, 177.

## ሐ. የግሪክን ግዛት የሚወክለውን ሦስተኛውን አውሬ ከሌሎች የሚለዩት ምን ልዩ ነገሮች ናቸው? ዳንኤል 7:6

“እነዚህ በርካታ መንግሥታት ሁልጊዜ በፊታቸው ፈሪሃ እግዚአብሔርን ጠብቀው ቢሆን ኖሮ፤ አንድ ላይ የሚያስተሳስራቸውና ጠንካራ የሚያደርጋቸው ጥበብና ኃይል ይሰጣቸው ነበር። ነገር ግን የዓለም መንግሥታት ገዥዎች እግዚአብሔርን ኃይላቸው የሚያደረጉት ሲጨነቁና ግራ ሲጋቡ ብቻ ነው።… እነርሱ ለመረዳት ያልቻሏቸውን ምስጢሮች ማብራሪያ ለማግኘት አእምሮአቸው በሰማያዊ ብርሃን የበራላቸውን ሰዎች እንዲጠይቁ ይገደዳሉ።”—The Youth’s Instructor, September 29, 1903.

## 3. ሮም፤ አራተኛዋ መንግስት ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 13

## ሀ. አራተኛውን አውሬ በተፈጥሮ አነጋገር ለመግለጽ አስቸጋሪ ያደረገው ምንድን ነው? ዳንኤል 7:7

*"መንፈስ ቅዱስ ዓለማዊ መንግሥታትን የሚወክለው በጨካኝ የአራዊት አምሳያ ነው፤ ነገር ግን ክርስቶስ 'የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው።" ዮሐንስ 1:29። በመንግሥቱ ዕቅድ ውስጥ ሕሊናን ለማስገደድ የሚደረግ ምንም ዓይነት የጭካኔ ሥራ የለም።"*—Christ's Object Lessons, p. 77.

*"መስቀሉ ከሮም ኃይል ጋር የተያያዘ ነው። እጅግ የጭካኔና የውርደት ሞት መሣሪያ ነበር። እጅግ ክፉ ወንጀለኞች መስቀሉን ወደ መሰቀያው ቦታ እንዲሸከሙ ይደረጉ ነበር፤ ብዙውን ጊዜ በትከሻቸው ላይ ስለሚሸከሙት ሲደርግባቸው ላለመሸከም ይንፈራጋጣሉ፤ በግድ መስቀሉ ከትከሻቸው ጋር እስኪታሰርባቸው ድረስ ያምጹ ነበር።"*—The Desire of Ages, pp. 416, 417.

## ለ. በአራተኛው አውሬ ቀንዶች መካከል ምን ታየ? ዳንኤል 7:8

*"በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጳጳሳዊው ሥርዓት በጠንካራ መሰረት ላይ ቆመ። መቀመጫውን የንጉሡ ነገሥታዊቷ ከተማ ተድርጎ የሮም ጳጳስ የጠቅላላዋ ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደሆነ ታወጀ። ጣዖት አምላኪነት ለጳጳሳዊ ሥርዓት ቦታ ለቀቀ። ዘንዶው "ሃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ስልጣን" ለአውሬው ሰጠው [ራዕ 13÷2፤ በመግለጫ ስር ማስታወሻ 2ን ይመልከቱ]። በዚህ ጊዜ በዳንኤልና በራዕይ የተነገሩት የ1260 የጳጳሳዊው ሥርዓት የጭቀና ዓመታት ጀመሩ። [ዳን 7÷25፤ ራዕይ 13÷5-7]። ታማኝነታቸውን ሰውተው የጳጳሳዊ አምልኮና ሥርዓት መቀበልን አለበለዚያ በወህኒ ቤት መማቀቅን፤ እጅና እግር ተወጥሮ ታስሮ (ግራ እጅና እግር በአንድ በኩል ቀኝ እጅና እግር በሌላ በኩል ታስሮ በመመንጨቅ) ተሰቃይቶ መሞትን፤ መቃጠልንና አንገትን በፋስ መቀላትን ይመርጡ ዘንድ ክርስቲያኖች ተገደዱ። አሁን የየሱስ ቃላት ተፈጸሙ፦ "ወላጆችም ስንኳ ወንድሞችም ዘመዶችም ወዳጆችም አሳልፈው ይሰጡአችኋል ከእናንተም አንዳንዱን ይገድላሉ። በሁሉም ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።" [ሉቃ 21÷16፣17]። ከምንጊዜውም በላይ በበለጠ ቁጣ አማኞችን ማሳደድ ተጀመረ፤ ዓለም ሰፊ የጦርነት ቀጠና ሆነች። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በመገለልና ከእይታ ውጪ በመሆን ውስጥ መጠጊያ (ደህንነት) አግኝታ ለብዙ መቶ ዓመታት ኖረች። ስለዚህም ነብዩ ይላል፦ "ሴቲቱም ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሃ ሸሸች።" [ራዕይ 12÷6]።*—The Great Controversy, pp. 54, 55.

## ሐ. ዳንኤል ራእዩን ካየ በኋላ ምን ማወቅ ፈለገ? ዳንኤል 7:19፣ 20

## 4. ትንሹ ቀንድ                    ረቡዕ፣ ሚያዝያ 14

## ሀ. መልአኩ የሮም መንግሥትን የሚወክለውን አስፈሪውን አራተኛ አውሬ በተመለከተ ምን አስረዳ? ዳንኤል 7:23።

## ለ. ስለ ትንሹ ቀንድ ምን ተገለጠ? ዳንኤል 7:24።

*"ሰፊው የሮም ግዛት ፈራረሰ፤ እናም ኃያሏ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከፍርስራሹ ወጣች። ይህች ቤተክርስቲያን በማየሳሳትና ከትውልድ ትውልድ ተሸጋጋሪ በሆነው ሃይማኖቷ ትመካለች። ነገር ግን ይህ ሃይማኖት የኃጥያት ምስጢርን ለሚያውቁ ሁሉ እጅግ አስፈሪ ነው። የዚህች ቤተክርስቲያን ካህናት ሕዝቡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለፀውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳያውቁ በማድረግ ከፍታቸውን (ክብራቸውን) ያስጠብቃሉ።"*—The Youth's Instructor, September 22, 1903.

## ሐ. የትንሹ ቀንድ ኃይል ቁጣ በማን ላይ ይቃጣ ይሆን? ዳንኤል 7:21፣ 25

*"የሮም ቤተ ክርስቲያን ስልጣን ላይ መውጣት የጨለማው ዘመን መባቻ ነበር። ኃይልዋ እየጨመረ ሲሄድ ጽልመቱም ጥልቅ እየሆነ ሄደ። እምነት፣ ትክክለኛ መሰረት ከሆነው ከክርስቶስ ወደ ሮማው ሊቀ-ጳጳስ ተላለፈ። ለኃጢአት ይቅርታና ለዘላለማዊ ድነት በእግዚአብሔር ልጅ በማመን ፈንታ ሰዎች ወደ ሊቀ-ጳጳሱና እርሱ ወደ ሾማቸው ቀሳውስትና የኃይማኖት መሪዎች ተመለከቱ። ምድራዊ አማላጃቸው ሊቀ-ጳጳሱ እንደሆነና በእርሱ በኩል ካልሆነ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደማይቻል ተማሩ። በተጨማሪም፣ ለእነርሱ፣ በእግዚአብሔር ቦታ የተቀመጠ ከመሆኑ የተነሳ በፍጹም መታዘዝ እንዲከተሉት ተማሩ። ከእርሱ መስፈርቶች ዝንፍ ማለት በአመጸኞች አካልና ሕይወት ላይ ከፍተኛውን አሰቃቂ ቅጣት ለማስከተል በቂ ምክንያት ነበር። በመሆኑም የሰዎች አእምሮ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ፣ ስህተት መፈጸም ወደሚቀናቸው፣ ጥፋት ወደሚሰሩና ወደ ጨካኝ ሰዎች፣ እንዲያውም ሃይሉን በእነዚህ ሰዎች አማካኝነት ተግባራዊ ወደሚያደርገው ወደ ጨለማው ልዑል እንዲዞር ተደረገ። ኃጢአት በማሳሳቻ የቅድስና ካባ ተደበቀ። መጽሐፍ ቅዱስ ሲጨቆንና ሰው የሁሉ በላይ እንደሆነ አድርጎ ራሱን ሲቆጥር፣ ልናይ የምንችለው አጭበርባሪነትን አታላይነትንና የሚያዋርድ ኃጢአትን ብቻ ነው። የሰው ሕግጋትና ባህሎች ከፍ ከፍ ሲደረጉ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ወደ ጎን የመገፍተር የምንጊዜም ውጤት የሆነው ብልሹነት ተንጸባረቀ።*

*እነዚያ ዘመናት ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በጣም አደገኛ ነበሩ። የክርስትናን ደረጃ የጠበቁ አማኞች እጅግ ጥቂቶች ነበሩ። እውነት ያለ ምስክሮች የቀረ ባይሆንም አንዳንድ ጊዜ ስህተትና መላምት ሙሉ በሙሉ የሚያሸንፍ፣ እውነተኛ ኃይማኖትም ከምድር የሚጠፋ ይመስል ነበር። ወንጌሉ ከእይታ ውጭ ሆነ፣ ኃይማኖታዊ ስነ-ስርዓቶች ተበራከቱ፤ ዝንፍ በማያስብሉ ሐይማኖታዊ ጭነቶች ሕዝቡ ጎበጠ።"*—The Great Controversy, p. 55.

## 5. ፍርዱ ሐሙስ፣ ሚያዝያ 15

## ሀ. የትንሹ ቀንድ ኃይል እንዲያበቃ ምን ይሆናል? ዳንኤል 7:26

"አርባ ሁለቱ [የራዕይ 13:5] ወራት በዳንኤል 7 ላይ ካሉት ሶስት ዓመት ተኩል ወይም 1260 ቀናት "እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም" ከተባሉት ጋራ እኩል ናቸው። ይህም ጊዜ የጳጳሳዊው ስልጣን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጨቁንበት ዘመን ነበር። ይህ ጊዜ በቀደሙት ምዕራፎች እንደተገለጸው፣ ጳጳሳዊው ሥርዓት በ538 ዓ .ም ሲቋቋም የጀመረ ሲሆን በ1798 ዓ .ም አብቅቷል። በዚያን ጊዜ ጳጳሳዊው ስርዓቱ ተገርስሶ ሊቀ ጳጳሱም በፈረንሳይ ጦር እስረኛ ሲሆን ጳጳሳዊው ኃይል የሞቱ ቁስል ደረሰበት፤ እናም ሊማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል የሚለው ትንቢት ተፈፀመበት።"—The Great Controversy, p. 439.

## ለ. የፍርዱ ሁኔታ እንዴት ይገለጻል? ዳንኤል 7:9፣ 10፣ 13

"እዚህ ላይ የተገለጸው የክርስቶስ መምጣት ሁለተኛው ወደ ምድር መምጣት አይደለም። በሰማይ በዘመናት ወደ ሸመገለው ሥልጣንና ክብር እንዲሁም መንግሥት ለመቀበል ይመጣል፤ ይህም የመካከለኛነት ሥራውን ሲያጠናቅቅ ይሰጠዋል።"—Ibid., p. 480.

## ሐ. የፍርዱ ውጤት ምን ይሆናል? ዳንኤል 7:11፣ 14፣ 18፣ 22፣ 26፣ 27

"ታላቁ የመቤዠት ዕቅድ ዓለምን ሙሉ በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ቸርነት መልሶ ያመጣል። በኃጢአት የጠፋው ሁሉ ይመለሳል። ሰው ብቻ ሳይሆን ምድርም የታዛዦች ዘላለማዊ መኖሪያ እንድትሆን ትቤዠለች። ለስድስት ሺህ ዓመታት ሰይጣን ምድርን ለመያዝ ሲታገል ቆይቷል። ያኔ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ የነበረው የመጀመሪያ ዓላማው ይፈፀማል። 'የታላቁ ልዑል ቅዱሳን መንግሥትን ይወስዳሉ፤ መንግሥቱንም ለዘዓለም ዓለም ይወርሳሉ።' ዳንኤል 7:18"—Patriarchs and Prophets, p. 342.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሚያዝያ 16

1. ዳንኤል ከባሕር ሲወጡ ያያቸውን አራት እንስሳትን ግለጽ።
2. አራዊቱ የተወከሉባቸውን መንግስታት እና ባህሪያቸው እንዴት እንደተሟላ ጥቀስ።
3. የትንሹን ቀንድ ኃይል ከሌሎች ኃይሎች የተለየ ያደረገው ምንድን ነው?
4. የትንሹ ቀንድ ኃይል "ታላላቅ" ቃላት ምን ነበሩ?
5. በፍርዱ የምድር ገዥነት የሚሰጠው ለማን ነው? መቼ ነው?

## ሚያዝያ 24፣ 2018



# የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ

## ለዓለም ሚሲዮኖች

በ24ኛው አጠቃላይ የልዑካን ጉባኤ ላይ፤ በቅርቡ የተከፈቱ ብዙ አዳዲስ ሚሽኖች ተወክለው ነበር። በዚህ እድገት ከልብ ደስተኞች ነን፣ እናም በእርግጥ መላው ዓለም በእግዚአብሔር ክብር መገለጥ እንዲሞላ የእንደዚህ ያሉ ብዙ የሆኑ ማእከሎችን መከፈት እንጠባበቃለን።

በአዲስ በሆኑ ቦታዎች ላይ በዚህ አስደናቂ የነፍስ ማዳን ሥራ ለመተባበር ከአንድ በላይ መንገዶች አሉ። "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?" (ሮሜ 10:13–15)። ሠራተኞቹም ሆኑ ሥራውን የሚደግፉት የጠፉትን በጎች ለማዳን ሲሉ በተለያዩ መንገዶች ራሳቸውን ይከዳሉ።

"ሁሉም አካላት ባለፉት ዓመታት በአሁኑ ጊዜ ወሳኝ በሆኑት ማዕከላት ይህን ስራ ማቋቋም ምን ያህል ከባድ እንደነበር ቢያውቁ ኖሮ፤ ተስፋ ሰጪ ያልሆኑ ሁኔታዎችን መጋፈጥ እና እጆቻቸውን ወደ ሰማይ በማንሳት "አንወድቅም ተስፋም አንቆርጥም" ማለት ምን ያህል ድፍረት እንደሚፈልግ ይገነዘቡ ነበር። በአዲስና አስቸጋሪ በሆኑ መስኮች ላይ መሰረትን ያልሰሩ ሰዎች የመጀመርያዎቹን ፈርቀዳጆች ሥራ ከባድነት አያስተውሉም። የእግዚአብሔርን ሥራ መረዳት ቢችሉ ኖሮ ቀድሞ በተሠራው ስራ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም በሞሰራው ሥራ ጊዜ ለመደሰት ምክንያት ያገኙ ነበር።

"ወንድሞቼ፤ ተስፋ ለመቁረጥ ምንም ምክንያት የለም። መልካሙ ዘር እየተዘራ ነው። እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፤ እንዲበቅልና የተትረፈረፈ ምርት እንዲያገኝም ያደርጋል። ብዙዎቹ ለነፍስ ማዳን የተቀቋቋሙ ድርጅቶች በመጀመሪያ በታላቅ ችግር ውስጥ እነዳለፉ አስታውስ።"—Testimonies for the Church, vol. 7, p. 242.

"ያለን እያንዳንዱ ብር የጌታ ነው።" አላስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ገንዘብ ከማውጣት ይልቅ፣ የሚስዮናዊ ሥራ ጥሪዎችን ለመመለስ ኢንቨስት ማድረግ አለብን። "አዳዲስ መስኮች እየተከፈቱ በሄዱ ቁጥር የአቅርቦት ጥሪዎች ያለማቋረጥ ይጨምራሉ።"—Historical Sketches, p. 293.

ስለዚህ የዛሬው የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ የሚሰበሰበው ለዓለም ሚሲዮኖች ነው፤ ይህም በአሁኑ ጊዜ በጣም አስፈላጊ የሆነ መዋጮ ነው። ጌታ እያንዳንዱ ሰጪ ራሱን በመካድ፣ በእምነትና በደስታ እንዲሰጥ ይርዳ በምላሹምእያንዳንዱን ይባርክ።

ወንድሞቻችሁ ከጠቅላላው ጉባኤ

# የመንግሥታት መተካካት

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ "የተነገረውም የማታውና የጥዋቱ ራእይ እውነተኛ ነው፤ ነገር ግን ከብዙ ዘመን በኋላ ስለሚሆን ራእዩን ዝጋ።" (ዳንኤል 8፡26)።**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 423–432.

*"እያንዳንዱ መንግሥት… የፈተና ጊዜውን አሳልፏል፤ ሁሉም ወድቀዋል፤ ክብራቸውም ደብዝዞአል፤ ኃይላቸውም ጠፍቶአል።"* —Prophets and Kings, p. 535.

## 1. አውራው በግ ታላቅ ሆነ — እሁድ፣ ሚያዝያ 18

**ሀ. የባቢሎን ታላቅነት ሊያበቃ ሲቃረብ ዳንኤል ምን አየ? ዳንኤል 8፡1፣ 2**

**ለ. ወደ ትዕይንቱ የመጣውን የመጀመሪያውንና ታላቅ የሆነውን አውሬ ባህርይ ግለጽ። ዳንኤል 8፡34**

**ሐ. ዳንኤል ያየውን አውራ በግ መልአኩ እንዴት ተረጎመው? ዳንኤል 8:19፣ 20**

*"በነቢዩ ራእይ ውስጥ እግዚአብሔር አንዱን ኃያል ገዥ ሲጥልና ሌላውን ሲያስነሣ ታይቷል። የዘላለም መንግሥቱን የሚያቋቁም፤ ለዘመናት የሸመገለ፣ ሕያው አምላክ፣ የጥበብ ሁሉ ምንጭ፣ የአሁኑ ገዥ፣ የወደፊቱን የሚገልጥ የዩኒቨርስ ንጉሥ ሆኖ ተገልጧል።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 4, p. 1166

*"በዳንኤልና በራዕይ መጻሕፍት ውስጥ ከተገለጸው የመንግሥታት መነሳትና መውደቅ፤ ውጫዊና ዓለማዊ ክብር ምን ያህል ከንቱ እንደሆነ መማር አለብን። ዓለማችን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይታው የማታውቀው ለዚያ ዘመን ሰዎች በጣም የተረጋጋችና ዘላቂ የመሰለችው የባቢሎን ኃይሏና ግርማዋ ሁሉ እንዴት ሙሉ በሙሉ እንደ 'ሣር አበባ' ተደመሰሰ! ድራሹ ጠፍቷል። የሜዶ-ፋርስ መንግሥት፣ የግሪክና የሮም መንግሥታትም እንዲሁ ጠፉ። እግዚአብሔርን መሰረታቸው የማያደርጉ ሁሉም እንዲሁ ይጠፋሉ።"*—Prophets and Kings, p. 548.

## 2. “እጅግ ታላቁ” ፍየል                ሰኞ፣ ሚያዝያ 19

## ሀ. ሜዶ ፋርስን ለመቃወም የመጣው አዲስ ኃይል ምንድን ነው? ዳንኤል 8:5፣ 21

## ለ. የዚህን አዲስ ግዛት ንጉሥ የድል አድራጊነት ኃይል ግለጽ። ዳንኤል 8:6፣ 7

“በዚህ ምድር ላይ በእያንዳንዱ ገዥ እጅ የተሠራበት ስልጣን ሁሉ ከሰማይ ተከፍሎ የተሰጠ ነው። የእያንዳንዱ ሰው ውጤት የሚመሠረተው በተሰጠው ስልጣንና በስልጣን አጠቃቀሙ ላይ ነው። በእያንዳንዱ ሰው የመለኮታዊ ጠባቂ ኃይል ቃል «አንተ ግን አላወቅኸኝም።» ይላል ኢሳ 45፡5 ጥንት ለናቡከደነጾር የተነገሩ ቃላት ለእያንዳንዱ ሰው ትምህርት ናቸው። «የደህንነትህ ዘመን ይረዝም እንደ ሆነ ምክሬ ደስ ያሰኝህ ኃጢአትህንም በጽድቅ፣ በደልህንም በድሆች በመመጽወት አስቀር። » ዳን 4፡27 “እነኝህ ነገሮች ለማስተዋል «ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች። » እንዲሁ «ዙፋን በጽድቅ ይፀናልና» «በቸርነትም ይበረታል።» ምሳ 14፡34 ምዕ 16፡12 ምዕ 20፡28 እነኝህን መሠረተ ሐሳቦች ለማስተዋል፡ በርሱ ኃይል ውስጥ ሲገለጡ ሥራቸውን ለመገንዘብ «ነገስታትን ያፈልሳል ነገሥታትን ያስነሳል።» ዳን 2፡21 ይህ ኃይል ያለው በእርሱ ነው የታሪክን ፍልስፍና ማስተዋል የሚቻለው። “ይህ በግልጽ ተብራርቶ የተቀመጠው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብቻ ነው፡ ፡ በዚህ ውስጥ የሕዝቦችና የግለሰብ ብርታት በአጋጣሚ ዕድሎች ወይም ባላቸው ሀብት ንብረት መሣሪያና ምቾት የመነጨ እንዳልሆነ ወይም በጉራ እንደሚናገሩት ታላቅነታቸው ከራሳቸው ኃይል የሚመነጭ እንዳልሆነ ያሳያል። የእግዚአብሔርን ሐሳብ አሟልተው ለማሳካት በፈፀሙት መጠን የሚሠፈር ነው።”—Education, pp. 174, 175.

## ሐ. የግሪክ መንግሥት በታላቁ አሌክሳንደር ግዛት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በነበረበት ጊዜ ምን ተፈጠረ? ዳንኤል 8:8፣ 22

““ትዕግስተኛ ሰው” ይላል ጠቢቡ ሰው፣ “ከኃያል ሰው ይሻላል፤ በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማን ከሚወስድ ሰው ይሻላል።” ስሜታቸውን ላለመግዛት ሲፈተኑ የአዕምሮን ሚዛን የሚጠብቁ ወንዶችና ሴቶች የጦር ሠራዊትን ለጦር እና ድል ለመንሳት ከሚመራ የጦር መሪ ይልቅ በእግዚአብሔር እና በሰማይ መልዓክት ፊት ከፍ ተደርገው ይታያሉ። አንድ የተከበረ ንጉስ ነገስት በአልጋው ላይ በሞት አፋፍ ሳለ እንዲህ ሲል ተናገረ፣ “ድል ካደረግኋቸው መካከል አንድ አሁን መጽናናትን የሚሰጠኝ ነገር አለ፣ እርሱም አስቸጋሪ ስሜቴ ላይ ያገኘሁት ድል ነው።” አሌክሰንደር እና ቄሳር ራሳቸውን ድል ከመንሳት ይልቅ ዓለምን ድል መንሳት ቀሏቸው አግኝተዋል። ከአንዱ አገር ሌላውን አገር ድል ከነሱ በኋላ — አንዳቸው “መሻትን ያለመግዛት፣ ሌለኛው ለምኞት እብደት ሰለባ” በመሆን ወድቀዋል።”—Child Guidance, pp. 95, 96.

## 3. "እጅግ የበለጠ ታላቅ" ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 20

## ሀ. የተከፋፈለውን የግሪክ ግዛት እንደተቆጣጠረ የተገለጸው አዲስ ኃይል የትኛው ነው? ዳንኤል 8:9፣ 23

## ለ. ዳንኤል በራዕይ ያየውን የአረማዊና የጳጳሳዊ ሮምን ድርጊቶች ግለጽ። ዳንኤል 8:10–12፣ 24

*"ጳጳሳዊው ስልጣን ዓለምን በማን አለብኝነት የሚያስተዳድር ጨቋኝ ገዥ ሆኖ ነበር። የዓለም ነገሥታትና ንጉሠ ነገሥታት ሁሉ ለሮም ጳጳስ አዋጅ (ሕግ) ይንበረከኩ ነበር። የሰዎች የጊዜያዊና የዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ በርሱ ቁጥጥር ስር ያለ መሰለ።.... የጳጳሳዊ ሥርዓት ቀትር የዓለም የግብረ ገብነት ውድቅት ነበር።...' ለብዙ መቶ ዓመታት አውሮፓ በትምህርት፣ በስነ-ጥበብም ሆነ በስልጣኔ ምንም አይነት ዕመርታ አላሳየችም ነበር። የስነ-ምግባርና የአእምሮ ሽባነት በክርስትናው ዓለም ላይ ወድቆ ነበር።"*—The Great Controversy, p. 60.

*"በትንቢት አስቀድሞ እንደተነገረው ጳጳሳዊ ስልጣን እውነትን ወደ ታች፣ ወደ ትቢያ ጣለው። የሰዎች ባህልና ወግ ከፍ ከፍ ሲል የእግዚአብሔር ሕግ ግን አቧራ ላይ ይረጋገጥ ነበር። በጳጳሳዊ ሥርዓት አገዛዝ ስር የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት አስቀድሞ እሁድን በቅዱስ ቀንነት እንዲያከብሩ ተገደው ነበር። በተንሰራፋው ስህተትና መላምት ተወናብደው ብዙዎች፣ የእግዚአብሔር ታማኝ ባርያዎች እንኳ ሳይቀር፣ እውነተኛውን ሰንበት እያከበሩ ሳለ በእሁድ ቀን ሥራ ከመሥራት ተቆጥበው ነበር። ይህ ግን ጳጳሳዊ መሪዎቹን አላረካቸውም። እሁድ እንዲቀደስ ብቻ ሳይሆን ሰንበት[ቅዳሜ] እንዲረክስ ጭምር ጠየቁ። ቋንቋቸው ውስጥ ማግኘት በቻሉት ከባድ ቃልም የሚያከብሩትን አወገዙ። የእግዚአብሔርን ሕግ በሰላም ለመታዘዝ የነበረው ብቸኛው አማራጭ ከሮም ስልጣን መሸሽ ነበር።"*—Ibid., p. 65.

## ሐ. ተንኮል የተሞላበት ዘዴ ቢኖረውም፤ ይህ ኃይል እንዴት ወደ ፍጻሜው ይመጣል? ዳንኤል 8:25።

*"በጳጳሳዊ ሥርዓት የበላይነት ረጅም ዘመን፣ በምድር ላይ ሰፍኖ በነበረው ጽልመት መኃል የእውነትን የብርሐን ጮራ ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት አልተቻለም ነበር። የዘመናቱ እግዚአብሔር ምስክሮች ነበሩት። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ብቸኛው አስታራቂ ክርስቶስ የመሆኑን እምነት የያዙ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የሕይወት መመሪያ መሆኑን የተቀበሉና ትክክለኛውን ሰንበት በቅድስና የጠበቁ ሰዎች እግዚአብሔር ነበሩት። ዓለም ለእነዚህ ሰዎች ምን ያህል ባለ ዕዳ እንደሆነ ትውልድ ፈጽሞ ሊያውቀው አይችልም። ሃሳባቸውና ምክንያታቸው እየተተቸ፣ ባህርያቸው በተንኮልና በግፍ እየተበረዘ፣ ጽሁፎቻቸው እንዳይሰራጩ እየተገደቡ፣ ያልሆነ ስም እየተሰጣቸውና እየተበጫጨቁ፣ የመናፍቅነት ስያሜ ይሰጣቸው ነበር። ሆኖም ንቅንቅ ሳይሉ ከዘመን ዘመን የእምነታቸውን ንጽህና ጠብቀው በቅዱስ ቅርስነት ለቀጣዩ ትውልድ እንዲቆይ በቀራጥነት ቆመዋል።"*— Ibid., p. 61.

## 4. የ2300ዎቹ ቀናት ረቡዕ፣ ሚያዝያ 21

## ሀ. ዳንኤል በራእዩ ያሉት ክስተቶች የሚወስዱትን የጊዜ ርዝመት በተመለከተና፤ በጊዜው መጨረሻ ላይ ምን እንደሚከሰት ምን ሰማ? ዳንኤል 8:13፣ 14

## ለ. በሜዳዊ ሕጎች ላይ እንደተገለጸው እና በዳንኤል ራእይ እንደተተነበየው፤ የመቅደሱ መንጻት የምን ዓይነት ክስተት ተምሳሌት ነበር? ዘሌዋውያን 23:27–32፤ 16:33፣ 34

*“በምሳሌያዊው (በብሉይ ኪዳኑ) ሥርዓት - የክርስቶስን መስዋዕትነትና ካህንነት የሚወክለው ጥላ - በሊቀ ካህኑ ከሚከናወኑ አመታዊ አገልግሎቶች ውስጥ የመቅደሱ መንፃት አገልግሎት የመጨረሻው ክፍል ነበር። የመጨረሻ የሆነው የመንፃት ሥራ የሚከናወንበት፣ ኃጢአት ከእሥራኤል ዘንድ የሚወገድበት ወይም የሚጣልበት የስርዓቱ መደምደሚያ ነበር። ይህም አስቀድሞ የገለጸው በሰማያዊ መዛግብት ሰፍረው ያሉትን የሕዝቦቹን መተላለፎች ያስወግድ ወይም ይፍቅ ዘንድ በሰማይ ያለው ሊቀ ካህናችን የሚያከናውነው የመጨረሻ አገልግሎቱን ነበር።”*—The Great Controversy, p. 352.

*“በጥንት ጊዜ እንደሚደረገው፣ የሕዝብ ኃጢአት በእምነት የኃጢአት መስዋዕቱ ላይ እንደሚጫን፣ በምሳሌም በደሙ በኩል ወደ ምድራዊው መቅደስ እንደሚተላለፍ፣ የአዲሱ ቃል ኪዳንም፣ ንስሐ የሚገቡ ሁሉ ኃጢአት በክርስቶስ ላይ ተጭኖ [በምሳሌ ሳይሆን] በትክክል ወደ ሰማያዊው መቅደስ ይተላለፋል። የምድራዊውም ምሳሌያዊ ማንፃት የተበከለበትን ኃጢአት በማስወገድ እንደሚከናወን ሁሉ፣ እውነተኛው የሰማያዊ መንፃትም እዚያ ተመዝግበው ያሉትን ኃጢአቶች በማስወገድ ወይም በመደምሰስ ይከናወናል። ይህ ከመፈፀሙ በፊት ግን ኃጢአትን በመናዘዝ፣ በክርስቶስ እምነት በኩል እነማን የዚህ ስርየት ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባቸው ለመወሰን የመዝገብ መጻሕፍት መመርመር አለባቸው። ስለዚህ የመቅደሱ መንፃት የምርመራ ሥራ፣ የፍርድ ሥራ ያካተተ ነው። ይህ ሥራ ክርስቶስ ሕዝቦቹን ነጻ ለማውጣት ከመምጣቱ*

*በፊት መከናወን ያለበት ተግባር ነው፤ ምክንያቱም በሚመጣበት ጊዜ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይከፍለው ዘንድ ዋጋው ከእርሱ ጋር ይሆናልና። [ራእይ 22÷12]።”*—Ibid., pp. 421, 422.

## ሐ. መልአኩ ስለ 2300ው ቀናት ትንቢት ምን አለ? ዳንኤል 8:26 (ከቁጥር 14፣ ንጽጽር ጋር አወዳድር)።

## 5. በከፊል የተረዳው ራዕይ ሐሙስ፣ ሚያዝያ 22

### ሀ. መልአኩ ገብርኤል ለዳንኤል ምን እንዲያደርግ ተልኮ ነበር? ዳንኤል 8:15–18

"መለኮታዊውን መልዕክት ወደ ዳንኤል ያመጣው ከእግዚአብሔር ልጅ ቀጥሎ የነበረው መልአክ ገብርኤል ነበር። ክርስቶስ ለተወደደው ዮሐንስ የወደፊቱን ለመግለጥ የላከው 'መልአኩ' ገብርኤልን ነበር። የትንቢቱን ቃል ለሚያነቡና ለሚሰሙ እንዲሁም በውስጡ የተጻፈውን ለሚጠብቁ በረከት ተነግሯል። ራዕይ 1:3—The Desire of Ages, p. 234.

### ለ. ዳንኤል ስለ ሌሎች በርካታ ዝርዝሮች ጥልቅ ማብራሪያ ቢሰጠውም፣ የ2300ውን ቀናት የጊዜ ትንቢት ከሰማ በኋላ ምን ምላሽ ሰጠ? ዳንኤል 8:27

"በሌላ ራእይ ወደፊት በሚከሰቱ ክስተቶች ላይ ተጨማሪ ብርሃን ፈነጠቀ፤ እናም በዚህ ራእይ መጨረሻ ላይ ዳንኤል "አንድ ቅዱስ ሲናገር ሰማ፤ ሌላው ቅዱስ ለተናገረው ቅዱስ ራእዩ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?" አለው። ዳንኤል 8:13 የተሰጠውም "እስከ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ማታና ጥዋት ድረስ ነው፤ ከዚያም በኋላ መቅደሱ ይነጻል።" (ቁጥር 14) የሚለው መልስ ግራ በመጋባት ሞላው። የራእዩን ትርጉም አጥብቆ ፈለገ። ዳንኤል በኤርምያስ በኩል በተተነበየው የሰባው ዓመት የምርኮ ጊዜና በራእይ ሰማያዊው ፍጥረት የእግዚአብሔር መቅደስ ከመንጻቱ በፊት እንደሚያልፍ ሲናገር በሰማው ሁለት ሺ ሦስት መቶው ዓመት መሀከል ያለውን ግንኙነት መረዳት አልቻለም። መልአኩ ገብርኤል በከፊል ትርጓሜን ሰጠው፤ ነገር ግን ነቢዩ "ራእዩ . . . ለብዙ ቀናት ይቆያል" የሚለውን ቃል በሰማ ጊዜ ሃይሉ ከዳው። እንዲህም ሲል በጊዜው የተሰማውን ስሜት ዘግቧል "እኔም ዳንኤል ተኛሁ፥ አያሌም ቀን ታመምሁ፤ ከዚያም በኋላ ተነሥቼ የንጉሡን ሥራ እሠራ ነበር፤ ስለ ራእዩም አደንቅ ነበር፥ የሚያስተውለው ግን አልነበረም።" ቁጥር 26፣ 27።"—Prophets and Kings, p. 554.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሚያዝያ 23

1. አብዛኛውን ጊዜ የምድር ነገስታት ሌሎችን ሕዝቦች ለመውረር የሚያነሳሳቸው የውስጥ ፍላጎቶች ምንድን ናቸው?
2. የፍየሉ ቀንድ እንዲሰበር ያደረገው ያልተስተካከለው የባህርይ ጉድለት ምንድን ነው?
3. የሮም አረማዊና የጳጳሳት ወቅቶች እርስ በርስ እንዴት ተመሳሳይ ነበሩ?
4. በ2,300ዎቹ ቀናት መጨረሻ ላይ ምን ይከሰታል?
5. ዳንኤል ጉልበቱ በከዳው ጊዜ አሁንም ምስጢር የሆነበት የራእዩ ክፍል የትኛው ነው?

# ራእዩ ተብራራ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “ስለዚህ እወቅ አስተውልም፤ እየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሢሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል፤ እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች።” (ዳንኤል 9፡25)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy pp. 409–422

“*መልአኩ ወደ ዳንኤል የተላከው በስምንተኛው ምዕራፍ ራዕይ ውስጥ ከጊዜ ጋር በተያያዘ ያለውን አገላለጽ ለመረዳት ያልቻለውን ነጥብ ለማብራራት ግልጽ ዓላማ ይዞ ነበር።*”—The Great Controversy, p. 326.

## 1. ለመረዳት ማንበብ እሁድ፣ ሚያዝያ 25

### ሀ. ባቢሎን በሜዶናውያንና በፋርሳውያን ድል ልትደረግ በነበረበት ወቅት ዳንኤል ምን እያጠና ነበር? ዳንኤል 9:1፣ 2.

“*በባቢሎን ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የቆዩት እግዚአብሔርን ሲፈልጉና ነፃነታቸውን የሚተነብዩ ትንቢቶችን ሲያጠኑ፤ እግዚአብሔር ደግሞ ለሕዝቡ በፊታቸው ሞገስ እንዲያገኝ የነገሥታትን ልብ እያዘጋጀ ነበር።*”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 4, p. 1172.

### ለ. ዳንኤል ያነብበው የነበረው ትንቢት ምን ትርጉም እንዳለው አብራራ። ኤርምያስ 25:8–14።

### ሐ. የኤርምያስ ትንቢት የእግዚአብሔር ሕዝብ ምን እንዲያደርጉ ያሳስባል? ኤርምያስ 29:10–14

“*ኤርምያስ በሚጽፍበት ጊዜ እስራኤል በግዞት ውስጥ ነበሩ፤ ከባቢሎን ከመመለሳቸውም በፊት በዚያ የሚቆዩበት ጊዜ በግልጽ ተቀምጧል። ለይሁዳ ቅሬታዎች ልባዊ ጸሎት፣ እግዚአብሔር በሞገስ ምላሽን ይሰጣቸዋል።*”—Prophets and Kings, p. 552.

## ሀ. ዳንኤል ላነበበው ነገር ምን ምላሽ ሰጠ? ዳንኤል 9:3

*"ዳንኤል እርግጥ በሆነው የትንቢት ቃል ላይ በተመሠረተ እምነት፣ እነዚህ ተስፋዎች በፍጥነት እንዲፈጸሙና የእግዚአብሔር ክብር እንዲጠበቅ ለመነ። በጸሎቱ ውስጥ ኃጢአታቸውን እንደ ገዛ ኃጢአቱ አድርጎ በመናዘዝ ከመለኮታዊ ዓላማ ከጎደሉት ጋር ሙሉ በሙሉ ራሱን መደበ።"*—Prophets and Kings, pp. 554, 555.

## ለ. የዳንኤልን ጸሎት ካነበብክ በኋላ፤ ምን ያህል ራሱን እንዳዋረደ እና ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደጸለየ ስታይ ምን አስተዋልክ? ዳንኤል 9:4–19

*"ዳንኤል ለረጅም ጊዜ እግዚአብሔርን ሲያገለግል የቆየ እና በሰማይ 'እጅግ የተወደደ' ተብሎ የተነገረለት ቢሆንም፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ኃጢአተኛ ታየ፤ የሚወዳቸውን ሰዎች ትልቅ ፍላጎት አሳሰበ።"*—Ibid., p. 555.

## ሐ. ዳንኤል በተለየ ያሳሰበው ነገር ምንድን ነበር? ዳንኤል 9:16፣ 17

*"እስራኤል ለሰባ ዓመታት ያህል በግዞት ቆይታለች። እግዚአብሔር ለራሱ የመረጣት ምድር ለአሕዛብ እጅ ተላልፋ ተሰጥታለች። የተወደደች፣ የሰማይ ብርሃንን የምትቀበል፣ የምድር ሁሉ ደስታ የነበረችው ከተማ አሁን የተናቀችና የተዋረደች ሆናለች። የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦትና የስርየት መክደኛውን የሚሸፍኑትን የክብር ኪሩቤሎች የያዘው ቤተ መቅደስ አሁን ፍርስራሽ ሆኖ ነበር። ቦታውም ባልተቀደሱ እግሮች ረክሶ ነበር። የቀደመውን ክብር የሚያውቁ ታማኝ ሰዎች እስራኤልን በእግዚአብሔር እንደተመረጡ ሕዝብ አድርጎ የለየው ቅዱስ ቤት በመጥፋቱ በጥልቅ ሃዘን ተሞልተው ነበር። እነዚህ ሰዎች በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔርን ፍርድ ምስክሮች ነበሩ። የዚህ ቃል ፍጻሜ ምስክሮች ነበሩ። እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ብትመለስና በፊቱ በጥንቃቄ ብትሄድ የእርሱን ሞገስ ታገኛለች ለሚለውም የተሰፋ ቃል ምስክሮች ነበሩ። አረጋውያንና ሽበት ያወጡ ሽማግሌ ተጓዦች በፍርስራሾቿ መካከል ለመጸለይ ወደ እየሩሳሌም ወጡ። እግዚአብሔር ጽዮንን እንዲምርላቸውና በጽድቁ ክብር እንዲሸፍናት ድንጋይቿን እየሳሙና በእንባቸው እያራሱ ለመኑት። ዳንኤል የእስራኤል ምርኮ የተመደበው ጊዜ ሊያበቃ እንደተቃረበ አውቆ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው ቃል ስለገባላቸው ብቻ እነሱ ራሳቸው ሣይሰሩ እጃቸውን አጣምረው መቀመጥ እንዳለባቸው አልተሰማውም። በጾምና በንስሐ እግዚአብሔርን ፈለገ፤ የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት ተናዘዘ።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 4, p. 1172.

## ሀ. በዳንኤል ጸሎት የተቋረጠው እንዴት ነበር? ዳንኤል 9:20፣ 21

"ሰማይ የነቢዩን ከልብ የሆነ ልመና ለመስማት ዝቅ ብሎ ነበር። የይቅርታና የመታደስ ልመናውን እንኳ ከመጨረሱ በፊት ኃያሉ ገብርኤል እንደገና ተገለጠለት።"—Prophets and Kings, p. 556.

"ወደ ዳንኤል መለኮታዊ መልዕክትን ይዞ የመጣው ከእግዚአብሔር ልጅ ቀጥሎ ያለው መልአክ ገብርኤል ነበር። . . . እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሰጥቶናል፤ በረከቱም የትንቢት መጻሕፍትን በአክብሮትና በጸሎት በማጥናት ይገኛል።"—The Desire of Ages, p. 234.

## ለ. የገብርኤል ጉብኝት ዓላማ ምንድን ነበር እናም በምዕራፍ 8 ካለው ራዕይ ጋር እንዴት የተገናኘ ነው? ዳንኤል 9:22፣ 23.

"[ገብርኤል] የዳንኤልን ትኩረት ከባቢሎን ውድቀትና ከብልጣሶር ሞት በፊት ወደ ተመለከተው ራዕይ መለሰ።"—Prophets and Kings, p. 556.

"እግዚአብሔር መልዕክተኛውን አዘዘ፣ "ራዕዩን ለዚህ ሰው አስታውቀው" [ዳን 8÷16]፤ ተልዕኮው መፈፀም አለበት። ትዕዛዙን ተቀብሎ መልአኩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ዳንኤል ተመልሶ "ጥበብና ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ"፤ "አሁንም ነገሩን መርምር፣ ራዕዩንም አስተውል" [ዳን 9÷22-23፣ 25-27]። በምዕራፍ ስምንት ራዕይ ውስጥ ሳይብራራ የቀረ ነጥብ አንድ ብቻ ነበር። እርሱም ጊዜን በተመለከተ ማለትም የ2300 ቀናት ክፍለ-ጊዜ ጉዳይ ነበር፤ ስለዚህም መልአኩ ማብራራቱን በመቀጠል በጊዜ ጉዳይ ብቻ አተኮረ።"—The Great Controversy, p. 325.

## ሐ. ለአይሁድ ሕዝብ ምን ዓይነት ጊዜ መመደብ ነበረበት እናም በዚያስ ጊዜ ምን ይከናወናል? ዳንኤል 9:24

"የክርስቶስ ስብከት ሸክም 'ዘመኑ ተፈጸሟል፣ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሐ ግቡ፣ በወንጌልም እመኑ' የሚል ነበር። ስለዚህ በአዳኙ በራሱ የተሰጠው የወንጌል መልእክት በትንቢቶቹ ላይ የተመሠረተ ነበር። እሱ እንደሚፈጸም የተናገረው 'ጊዜ' መልአኩ ገብርኤል ለዳንኤል የገለጸለት ጊዜ ነው። . . . በትንቢት ውስጥ አንድ ቀን እንደ አንድ ዓመት ይረዝማል። . . . ዘኍልቍ 14:34፤ ሕዝቅኤል 4:6ን ተመልከቱ። ሰባዎቹ ሳምንታት ወይም አራት መቶ ዘጠናዎቹ ቀናት አራት መቶ ዘጠና ዓመታትን ይወክላሉ።"—The Desire of Ages, p. 233.

## 4. ጅማሬው ተገለጠ                    ረቡዕ፣ ሚያዝያ 28

### ሀ. የሰባው ሳምንታትን መጀመር የሚያመለክተው ጉልህ የሆነው የንጉሣዊ ትእዛዝ የትኛው ነው? ዳንኤል 9:25

“በአርጤክስስ ሎንጊማነስ ትእዛዝ እየሩሳሌም መታደስና መገንባት በ457 ዓ.ም. የመከር ወራት ተጠናቀቀ። (ዕዝራ 6:14፤ 7:1, 9) ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ 27 ዓ.ም. የመኸር ወራት አራት መቶ ሰማንያ ሦስት ዓመታትን ዘልቋል።”—The Desire of Ages, p. 233.

### ለ. የዚህ ትንቢት ፍፃሜ በሆነው ድንጋጌ ውስጥ የተደረጉትን አቅርቦቶች አብራራ። ዕዝራ 7:11–13 21–27

“ጌታ… የንጉሡ ልብ ላይ እንዲነሳሳ አድርጎ ዕዝራ በእርሱ ዘንድ ሞገስን አገኘ። ንጉሡ ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ብዙ መሳሪያዎችን በእጁ ሰጥቶ አይሁዶች እንዲመለሱ ፈቀደ።”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 3, p. 1134.

### ሐ. በተጨማሪም ትንቢቱ ስለ መሲሑ አገልግሎት ምን ተንብይዋል? ዳንኤል 9:26 (የመጀመሪያው ክፍል)፣ 27 (የመጀመሪያው ክፍል)

“በትንቢቱ መሠረት ይህ ጊዜ እስከ የተቀባው መሲሕ ድረስ ነበር። በ27 ዓ.ም. የሱስ በተጠመቀ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ተቀበለ፣ እና ብዙም ሳይቆይ አገልግሎቱን ጀመረ። ከዚያም ‘ዘመኑ ተፈጽሟል’ የሚለው መልእክት ታወጀ።

“ከዚያም መልአኩ፣ ‘ከብዙዎች ጋር ለአንድ ሳምንት [ለሰባት ዓመታት] ቃል ኪዳኑን ያጸናል’ ብሏል።

አዳኙ አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ ለሰባት ዓመታት ወንጌል ይሰበካል ፤ በተለይም ለአይሁድ። የመጀመርያውን ለሦስት ዓመት ተኩል በክርስቶስ በራሱ ከዚያም በኋላ ደግሞ በሐዋርያት። ‘በሳምንቱ መካከል መሥዋዕቱንና መባውን ያስቀማል።’ ዳንኤል 9:27። በ31 ዓ.ም. የጸደይ ወራት እውነተኛ መሥዋዕት የሆነው ክርስቶስ በቀራንዮ ላይ ተሰዋ። ከዚያም የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ፣ ይህም የመሥዋዕቱ አገልግሎት አስፈላጊነት እንደተወገደ ያሳያል። ምድራዊው መሥዋዕቶችና መንጻቶች የሚቀሙበት ጊዜ ደረሰ።

አንዱ ሳምንት (ሰባቱ ዓመታት) በ34 ዓ.ም. አብቅቷል። ከዚያም በእስጢፋኖስ መወገር አይሁድ ወንጌልን አለመቀበላቸውን አረጋገጡ፤ በስደት የተበተኑትም ደቀ መዛሙርት ‘ቃሉን በየቦታው እየሰበኩ ዞሩ’ (የሐዋርያት ሥራ 8:4)።”—The Desire of Ages, p. 233.

## 5. ሰባዎቹ ሳምንታት ተጠናቀቁ ሐሙስ፣ ሚያዝያ 29

## ሀ. 490ዎቹ ዓመታት ካለቁ በኋላ ምን አሳዛኝ ሁኔታ ይከሰታል? ዳንኤል 9:26 (የመጨረሻው ክፍል)፣ 27(የመጨረሻው ክፍል)፤ ሉቃስ 21:20

"እግዚአብሔር ለየሩሳሌም ያሳየው ትዕግስት ያረጋገጠው ነገር ቢኖር የአይሁድን በአመጽ የመቀጠል ግትርነት ነበር። በጭፍንና በስድብ አዘል አይን ያወጣ ስተሳሰባቸው [መሪዎቻቸው]፣ የዚህ አሰቃቂ ሥራ አነሳሽዎች፣ የሩሳሌም የእግዚአብሔር የራሱ ከተማ ስለሆነች ትጠፋለች የሚል ምንም አይነት ፍርሃት እንደሌለባቸው በአደባባይ ይለፈልፉ ነበር። ስልጣናቸውን የበለጠ ለማደላደል ሲሉ፣ የሮማ ክፍለ ጦር መቅደሱን እየከበበ ባለበት ሰዓት እንኳ ለሐሰተኛ ነብያት ጉቦ ከፍለው ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ማዳን ዝም ብሎ መጠበቅ እንዳለበት ያስለፍፉ ነበር። ጠላቶቻቸውን ያሸንፉ ዘንድ ታላቁ ንጉሥ (አምላክ) ጣልቃ እንደሚገባ ብዙዎች እስከመጨረሻዋ ሰዓት እምነት ጥለው ነበር። እሥራኤል ግን መለኮታዊ ጥበቃን አሻፈረኝ ብላለችና አሁን የሚያድናት የለም። ደስታ-ቢስዋ የሩሳሌም! የሰው አገር ሰራዊት ቅጥሮችዋን ሲደረማምሱና የጦር ሰዎችን ሲያርዱ ሳለ፣ በውስጥ አለመግባባት ተከፋፍላ፣ ልጆችዋ እርስ በርስ ተገዳድለው በጃቸው ጎዳናዎችዋን በደም ያቀልሙት ነበር።!"—The Great Controversy, pp. 28, 29.

## ለ. የዚህን የቀኖቹ የመጀመሪያ ክፍል ከተረዳን በኋላ፣ አሁን ምንን ማስተዋል እንችላለን? ዳንኤል 8:14፤ 9:24

"እስከዚህ ድረስ እያንዳንዱ ትንቢት በሚያስገርም ሁኔታ ተፈጽሞአል፤ የሰባው ሳምንታት መጀመሪያም ጥያቄ በማያስነሳ ሁኔታ ከክ. ል . በፊት 457 ዓ .ዓ ማብቂያውም በ34 ዓ .ም እንደሆነ ተረጋግጧል። ከዚህ መረጃ በመነሳት 2300 ቀናት የሚያልቁበትን ዘመን ማወቅ ከባድ አይደለም። ሰባ ሳምንታቱ ማለትም 490ዎቹ ቀናት ከ2300 ቀናት ተቀንሰው የሚቀረው 1810 ቀናት ነበሩ። 490 ቀናቱ ካለቁ በኋላ 1810 ቀናቱ ገና ፍፃሜ ማግኘት ያለባቸው ዘመናት ነበሩ። ከ34 ዓ.ም ጀምሮ 1810 ዓመታት ሲጨመሩ ወደ 1844 ዓ.ም ያመጣናል። በመሆኑም የዳንኤል 8÷14ቶቹ 2300 ቀናት በ1844 ያበቃሉ። ከዚህ ታላቅ ትንቢታዊ ዘመን ማለቅ በኋላ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ምስክርነት "መቅደሱ ይነፃል"፤ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው፣ በዳግም ምፅዓት ጊዜ የሚከናወነው የመቅደሱ መንፃት ዘመን መቼ እንደሆነ ታወቀ።"—Ibid., p. 328.

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሚያዝያ 30

1. ዳንኤል ራሱ ነቢይ ቢሆንም፣ ምን ለመረዳት ጓጉቶ ነበር?
2. ዳንኤል ስለ እስራኤል ያለፈ ኃጢአት በንስሐ ጸሎቶች ውስጥ ራሱን ለምን አካተተ?
3. ዳንኤል 9 የዳንኤል 8ን ምስጢር እንደሚፈታ በእርግጠኝነት እንዴት እናውቃለን?
4. የ490 ዓመት ትንቢት መጀመሪያን የሚያሳየውን ክስተት አብራራ።
5. በዳንኤል እና በየሱስ እንደተነበየው የእሩሳሌምን ጥፋት ይግለጽ።

# የታተመው (የተዘጋው) መጽሐፍ እንደገና ተከፈተ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “ወደ መልአኩም ሄጄ፡- ታናሺቱን መጽሐፍ ስጠኝ አልሁት። እርሱም፡- ውሰድና ብላት፥ ሆድህንም መራራ ታደርገዋለች በአፍህ ግን እንደ ማር ትጣፍጣለች አለኝ።” (ራዕይ 10፡9)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 391–408.

“ዮሐንስን ያስተማረው ኃያል መልአክ በእርግጥ የሱስ ክርስቶስ ነበረ።”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 971.

## 1. ጥበበኞች ያበራሉ እሁድ፣ ግንቦት 02

**ሀ. በዳንኤል የመጨረሻ ራእይ መጨረሻ ላይ የተገለጠውን ፈተናና ድል ግለጽ። ዳንኤል 12፡1፣ 2**

**ለ. በዚያ ቀን ጥበበኞች ከክፉዎች ጋር ሲነጻጸሩ እንዴት ይታዩ ነበር? ዳንኤል 12:3፤ ማቴዎስ 13:41-43**

“የተለወጠ ነፍስ በክርስቶስ ይኖራል። ጨለማው ያልፋል፣ አዲስና የሰማይ ብርሃንም ወደ ነፍሱ ያበራል። ‘ነፍሳትን የሚያተርፍ ወይም የሚያሸንፍ እርሱ ጥበበኛ ነው።’ ‘ጥበበኞች እንደ ሰማይ ብርሃን ያበራሉ፤ ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱም እንደ ከዋክብት ለዘላለም ያበራሉ።’ በሰዎችና ከእግዚአብሔር ትብብር የሚሰራው ሥራ የማይጠፋ ነገር ግን ለዘላለም የሚጸና ነው። እግዚአብሔርን ጥበቡ ያደርገ፣ በክርስቶስ የሱስ ወደ ሙሉ ሰውነት የሚያድግ እርሱ በነገሥታት ፊት፣ በዓለም ታላላቅ ሰዎች ተብለው በሚጠሩት ፊት ቆሞ ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራውን የእርሱን ምስጋና ያሳያል። ስለእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የከበረው ወንጌል ወደ ጨለማው የሰው አእምሮ ሊያመጣ የሚችለውን ብርሃን ሳይንስና ሥነ ጽሑፍ ማምጣት አይችሉም። ለነፍስ ብርሃንን የማብራትን ታላቅ ሥራ መሥራት የሚችለው የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ነው። ጳውሎስ “በክርስቶስ ወንጌል አላፍርምና. . .የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው” ሲል መናገሩ ምንም አያስደንቅም። የክርስቶስ ወንጌል በሚያምኑት ውስጥ ማንነታቸው ይሆናል፤ እናም በሰዎች ሁሉ ዘንድ የሚታወቁ እና የሚነበቡ ሕያው መልእክቶች ያደርጋቸዋል።”—Fundamentals of Christian Education, pp. 199, 200.

## 2. መጽሐፉ ተዘጋ ሰኞ፣ ግንቦት 03

### ሀ. ዳንኤል አሁን ምን እንዲያደርግ ታዘዘ? ዳንኤል 12:4 (የመጀመሪያው ክፍል)፣ 8፣ 9 (የመጀመሪያው ክፍል)

"የመንግሥት ኃላፊነት ባላቸው ሰዎች እና ዓለም አቀፋዊ ሥልጣን ባላቸው የመንግሥታት ምስጢር ጠባቂዎች የተከበረው ዳንኤል በእግዚአብሔርም እንደ አምባሳደር ክብር ተሰጥቶታል፤ ስለሚመጡት ዘመናት ምስጢሮች ብዙ መገለጦችን አግኝቷል። በስሙ በተሰየመው መጽሐፍ ከምዕራፍ 7 እስከ 12 ላይ የተመዘገቡት ድንቅ ትንቢቶች ነቢዩ ራሱ እንኳን ሙሉ በሙሉ አልተረዱቸውም ነበር፤ ነገር ግን ሕይወቱ ከማለፉ በፊት "በዘመኑ መጨረሻ" በዚህ ዓለም ታሪክ የመጨረሻ ዘመን እንደገና በዕጣ ፈንታው እና በቦታው እንዲቆም እንደሚፈቀድለት የተባረከ ማረጋገጫ ተሰጥቶታል። እግዚአብሔር ስለ መለኮታዊ ዓላማው የገለጸውን ሁሉ እንዲረዳ አልተሰጠውም። . . .

"ወደዚህ ዓለም ታሪክ ፍጻሜ እየተቃረብን ስንሄድ፣ በዳንኤል የተመዘገቡት ትንቢቶች እኛ ከምንኖርበት ዘመን ጋር ስለሚዛመዱ ልዩ ትኩረት እንድንሰጣቸው ይጠይቃሉ።" የአዲሱ ኪዳን የቅዱሳት መጻሕፍት የመጨረሻ መጽሐፍ ትምህርቶችም ከእነርሱ ጋር መያያዝ አለባቸው።—Prophets and Kings, p. 547.

### ለ. የመልአኩ ቃላት የ2300 ቀናትን ምስጢር እንደሚያመለክቱ የሚያሳየው ምንድን ነው፤ ያ ምስጢርስ መቼ ይገለጣል? ዳንኤል 8:17፤ 12:4፣ 9 (የመጨረሻው ክፍል)

"ትንቢታ ቱ የሚያቀርቡት፣ ወደ ፍርዱ መከፈት የሚያመሩ ተከታታይነት ያላቸውን ክስተቶች ነው። የዳንኤልን መጽሐፍ በተመለከተ ይህ በተለይ እውነት ነው። ነገር ግን ከመጨረሻዎቹ ቀናት ጋር የሚዛመደውን የእርሱን ትንቢት ክፍል እስከ "ፍፃሜ ዘመን ድረስ" እንዲዘጋና እንዲያትም ዳንኤል ተነግሮታል። በእነዚህ ትንቢታት አፈፃፀም መሰረት ወደዚህ ጊዜ እስክንደርስ ድረስ ፍርዱን በተመለከተ የተሠጠው መልእክት አይታወጅም። ሆኖም "በመጨረሻው ዘመን" አለ ነብዩ፣ "ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ፤ እውቀትም ይበዛል" [ዳን 12÷4]። . .

"ከ1798 ዓ.ም ጀምሮ የዳንኤል መጽሐፍ ማህተም ስለተከፈተ፣ የትንቢታቱ እውቀት ጨምሯል፤ ክቡር የሆነውን የፍርድ ጊዜ መልእክትም በማወጅ ጊዜው እንደቀረበ ብዙዎች መስክረዋል።

"በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደነበረው ታላቅ ተሐድሶ ሁሉ የአድቬንት (የዳግም ምጽዓቱ) እንቅስቃሴ በተለያዩ የክርስቲያን ሃገራት በተመሳሳይ ጊዜ ብቅ ብቅ ማለት ጀመረ። በአውሮፓና በአሜሪካ የነበሩ የእምነትና የፀሎት ሰዎች ትንቢታቱን እንዲያጠኑ ተመሩ። በመንፈስ የተፃፈውን መዝገብ ዱካ በመከተልም የሁሉም ነገር ፍጻሜ በደጅ እንደቀረበ አሳማኝ መረጃ አስተዋሉ። በተለያዩ ስፍራዎች፣ ለየብቻቸው የነበሩ የክርስቲያን ስብስቦች መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ብቻ የአዳኙ ምፅዓት እንደቀረበ አመኑ።።"—The Great Controversy, pp. 356, 357.

## ሀ. ዳንኤል ሲመለከትና ሲያዳምጥ፣ ፍጻሜውን ዘመን መጀመር የሚለየው የትኛው ከባድ አዋጅ ነው? ዳንኤል 12:5–7

## ለ. ሌሎች ክፍሎችን በማጣቀስ፣ የዚህን ትንቢታዊ ጊዜ ለይ። ዳንኤል 7:25፤ ራዕይ 11:2፣ 3፤ 12:6፣ 14፤ 13:5

*"በእርሱ ዘመን የሚከናወን ነው ብላ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን መገለጥ እንዳትጠብቅ ሐዋርያው ጳውሎስ አስጠንቅቋታል። [ያ ቀን ደርሷል ብላችሁ... እንዳትናወጡ] ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና "የኃጢአት ሰው" እርሱም "የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ" ይላል ጳውሎስ "አይደርስምና" [2ኛ ተሰሎ 2÷3]። ከታላቁ ክህደት፣ ከ"ኃጢአት ሰው" የረጅም ዘመን ግዛት በፊት የጌታችን መገለጥ አይጠበቅም። "የአመፅ ምስጢር"፣ "የጥፋት ልጅ" እንዲሁም "ያ ክፉ" ተብሎ በተጨማሪ የተገለፀው [2ኛ ተሰሎ 2÷3፤ 7፣8] ያ "የኃጢአት ሰው" ጳጳሳዊው ሥርዓት ሲሆን በትንቢት አስቀድሞ እንደተነገረውም የበላይነቱን አስጠብቆ ለ1260 ዓመታት የሚቀይ ነበር። ይህ ዘመን በ1798 ዓ.ም አብቅቷል። የክርስቶስ መገለጥ ከዚያ ጊዜ በፊት ሊሆን አይችልም። ጳውሎስ እስከ 1798 ዓ .ም ድረስ ያለውን የክርስቲያን ዘመን በሙሉ በማስጠንቀቂያው አካቶታል። የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት መልእክት የሚታወጀውም ከዚያን ጊዜ በኋላ ባለው ነው።"*—The Great Controversy, p. 356.

## ሐ. የ1260ዎቹ ዓመታት ዘመን በመልአኩ የተገለጸው እንዴት ነበር? ዳንኤል 12:10 (የመጀመሪያው ክፍል)

*"በአሥራ ሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሁሉም የጳጳሳዊ መሳሪያዎች የሚበልጠው፣ እጅግ አሰቃቂ የሆነው ችሎት (the Inquisition) ተቋቋመ። የጨለማው ልዑል በጳጳሳዊ ስልጣን እርከን ውስጥ ካሉ መሪዎች ጋር ይሰራ ነበር። ምስጢራዊ ስብሰባቸውን ሲያካሂዱ፣ የእግዚአብሔር መልአክ በመካከላቸው ቆሞ በኃጢአት የተሞሉትን አዋጆቻቸውን፣ በፍጡር አይን ተገልጦ ለመታየት እጅግ ዘግናኝ የሆነውን የሥራቸውን ታሪክ፣ በአስፈሪው መዝገብ ላይ ሲጽፍ ሳለ፣ ሰይጣንና መላዕክቱ የክፉ ሰዎችን አእምሮ ይቆጣጠሩ ነበር። ። "ታላቋ ባቢሎን" "በየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ" [ራዕይ 17÷6] ነበር። አካላቸው የተቆራረጠው፣ በሚሊዮን የሚቀጠረው የሰማዕታት ግዝም፣ በዚያ ከሃዲ ኃይል ላይ የበቀል እርምጃ ይወሰድ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ይጮህ ነበር። . . .*

*"በሮም ስልጣን ስር የነበረው ዓለም በነቢዩ ሆሴዕ የተነገረውን አስፈሪና ከባድ ትንቢት ፍጻሜ ይወክል ነበር፦ . . . "እውቀትና ምሕረት እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድር ስለሌለ፣ እርግማንና ሐሰት፣ ግዳይና ስርቆት ምንዝርም ወጥተዋል፤ ደምም ወደ ደም ደርሶአል።" [ሆሴዕ 4÷6፣1፣3]። የእግዚአብሔርን ቃል ማጥፋት ውጤቱ ይህን ይመስል ነበር።*—Ibid., pp. 59, 60.

## ሀ. ከዳንኤል 12:7 ጋር ያለውን በማስተያየት ስንመለከት፣ ነቢዩ ዮሐንስ የዳንኤልን የታተመ ራዕይ መፈታት እንዴት አየ? ራእይ 10:1፣ 2፣ 5፣ 6

"ዮሐንስን ያስተማረው ኃያል መልአክ የሱስ ክርስቶስ ነበረ። ቀኝ እግሩን በባህር ላይ ግራውንም በደረቅ ምድር ላይ ማድረጉ ከሰይጣን ጋር በተደረገው ታላቅ ተጋድሎ የመዝጊያ ትዕይንቶች ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ያሳያል። ይህ አቋቋም በምድር ሁሉ ላይ ያለውን ከፍተኛ ኃይል እና ሥልጣኑን ያመለክታል። . . .

"ዮሐንስ ትንሹ መጽሐፍ ሲፈታ ያያል። ከዚያም የዳንኤል ትንቢቶች በመጀመሪያው፣ በሁለተኛው እና በሶስተኛ መላእክት ለዓለም በሚሰጡት መልእክቶች ውስጥ ተገቢ ቦታ አላቸው። የትንሿ መጽሐፍ ማኅተም መፈታት ከጊዜ ጋር የተያያዘ መልእክት ነበር። . . .

"መልአኩ በከባድ መሐላ የሚያውጀው ይህ ጊዜ የዚህ ዓለም ታሪክ ፍጻሜ አይደለም፤ የአማክሮ ጊዜም አይደለም፤ ነገር ግን ከጌታችን ምጻት በፊት መፈጸም ያለበት ትንቢታዊ ጊዜ ነው። ይህ ማለት ለሕዝቡ በተወሰነ (በተቀረጠ) ጊዜ የሚሰጥ ሌላ መልእክት አይኖረውም። ከዚያን ጊዜ በኋላ . . . ከ1844 የመኸር ወቅት በኋላ ግልጽ የሆነ የተወሰነ ጊዜን የሚያሳይ ትንቢት የለም። ረጅሙ የትንቢት ዘመን 1844 ዓ.ም ያበቃል።

"የመልአኩ አንድ እግር በባህር ላይ፣ ሌላኛው ደግሞ በምድር ላይ ሆኖ መቆሙ የመልእክቱን የተደራሽነት ስፋት ያመለክታል። ባሕርን አቋርጦ በሌሎች አገሮች፣ እስከ ዓለም ሁሉ ድረስ ይታወጃል።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 971.

## ለ. ዮሐንስ በራእይ ትንሹን መጽሐፍ በበላ ጊዜ የነበረው ተሞክሮ ከ1840ዎቹ የአድቬንቲስት እንቅስቃሴ ተሞክሮ ጋር እንዴት ተመሳሳይ እንደነበር አብራራ። ራዕይ 10:9–11።

"ትንሿን መጽሐፍ መብላት፡ እውነትን የመረዳትና መልእክቱን በደስታ የመቀበል ምልክት ነው። ስለ ጌታችን ምጻት ጊዜ ያለው እውነት ለነፍሳችን ውድ መልእክት ነው።"—Ibid.

"የተጠበቀው ጊዜ አለፈ፤ ሕዝቦቹን ይታደግ ዘንድ ክርስቶስ አልመጣም። በእውነተኛ እምነትና ፍቅር አዳኛቸውን የጠበቁ እነርሱ መሪር ቅሬታ ደረሰባቸው። ሆኖም የእግዚአብሔር አላማዎች እየተፈፀሙ ነበር። መገለጡን እየጠበቅን ነው ብለው የመሰከሩትን የእነርሱንልብ እየፈተነ ነበር። . . .

"የሱስና የሰማይ ሰራዊት ግን የተፈተኑትን፣ ታማኝም የሆኑትን፣ ሆኖም ቅሬታ የገጠማቸውን ሕዝቦች በፍቅርና በርኅራኄ ተመለከቷቸው። የሚታየውን ዓለም ከማይታየው የሚለየው መጋረጃ ቢገለጥ መላእክት ወደነዚህ የማይነቃነቁ ነፍሳት ሲቀርቡ፣ ከሰይጣን ፍላጻምሲከልሏቸው ይታዩ ነበር።"—The Great Controversy, p. 374.

## 5. ከጠቢባን መካከል ሐሙስ፣ ግንቦት 06

### ሀ. በዳንኤል ዘመን ከነበሩት አንዱ የሆነው ሕዝቅኤል ዳንኤልን እንዴት ገልጾታል? ሕዝቅኤል 14:14

### ለ. እንደ ዳንኤል ከጠቢባን መካከል እንዴት መሆን እንችላለን? ዳንኤል 12:10 (የመጨረሻው ክፍል)፤ ምሳሌ 9:10፤ ማቴዎስ 7:24፣ 25

*"'እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን" በቅርቡ በፊታችን ይከፈታል፤ አሁን የሌለንና ያገኙትም ዘንድ ብዙዎች እጅግ ሰነፎች የሆኑበት፣ ልምምድ የሚያስፈልገን ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ መከራ፣ በተግባር ከሚሆነው ይልቅ ሲያስቡት የበለጠ የገዘፈ ነው። ይህ* [አገላለጽ] *ግን በፊታችን ላለው ችግር ትክክል አይደለም። እጅግ እውነት አስመስሎ የሚያቀርብ ተወዳዳሪ የሌለው ገለፃ እንኳ የአበሳውን ዲካ ሊነካው አይችልም። በዚያ የመከራ ጊዜ፣ እያንዳንዱ ነፍስ በእግዚአብሔር ፊት ለራሱ መቆም ይኖርበታል። "*[*ኖህ፣ ዳንኤልና እዮብ በምድሪቱ ቢኖሩም*] *እኔ ሕያው ነኝና በጽድቃቸው ነፍሳቸውን ብቻ ያድናሉ እንጂ ወንዶችንና ሴቶችን ልጆቻቸውን አያድኑም ይላል ጌታ እግዚአብሔር"* [*ሕዝ* 14÷20]*።*

*አሁን፣ ሊቀ ካህናችን ስርየት እያደረገልን ሳለ በክርስቶስ ፍፁማን እንሆን ዘንድ መጣር ይገባናል። አዳኛችን በአንዲት ሃሳብ እንኳ ለፈተና ኃይል እጅ እንዲሰጥ መደረግ አልቻለም። በሰው ልብ ውስጥ ሰይጣን የሚንጠላጠልበት፣ እግሩን ማሳረፊያ አንዳች ነጥብ ያገኛል፤ የሆነ የኃጢአት ፍላጎት ይበረታታል፤ በዚህም አማካኝነት ፈተናዎቹ ኃይላቸውን ይገልጣሉ። ክርስቶስ ግን ስለራሱ ሲናገር፦ "የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና፤ በእኔ ላይም አንዳች የለውም"* [*ዮሐ* 14÷30] *ይላል። ድል ይቀዳጅበት ዘንድ ሰይጣን በእግዚአብሔር ልጅ ዘንድ ማግኘት የቻለው አንዳች ነገር አልነበረም። የአባቱን ትዕዛዛት ጠብቋል፤ ሰይጣን ለራሱ ጥቅም ሊያውለው የሚችል ኃጢአት በእርሱ ዘንድ አልነበረም። በመከራ ዘመን የሚቆሙ እነርሱ ሊገኙበት የሚገባቸው ሁኔታ ይህ ነው።"*—The Great Controversy, pp. 622, 623.

### ሐ. መልአኩ ዳንኤልን በመጨረሻ እንዴት ተሰናበተው? ዳንኤል 12:13.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ግንቦት 07

1. *የዳንኤል* 12:2*ቱ ትንሣኤ መቼ ይሆናል*?
2. *የዳንኤል ትንቢት እንዲፈታ ያደረገው ክስተት ምንድን ነው*?
3. *የፍጻሜው ዘመን መጀመርን ያመለከተው ክስተት ምንድነው*?
4. *የዳንኤል መጽሐፍ መከፈቱን የገለጸው የትኛው ትንቢት ነው*?
5. *ከጠቢባኑ መካከል እንደሆንኩ እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ*?

# የፍጥሞው ነቢይ

## የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “የሱስም ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በየሱስ ደረት ላይ ተጠጋ።” (ዮሐንስ 13፡23)

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Acts of the Apostles, pp. 539–556.

“ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ፣ ዮሐንስ ለመምህሩ ታማኝና ትጉ ሠራተኛ ሆኖ በጽናት ቆመ።”—The Acts of the Apostles, p. 546.

## 1. የሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር እሁድ፣ ግንቦት 09

### ሀ. ደቀ መዛሙሩ ዮሐንስ ከየሱስ ጋር ያለውን ቅርበት የሚያሳዩት የትኞቹ ምሳሌዎች ናቸው? ማቴዎስ 17፡1፤ ማርቆስ 14፡33፤ ሉቃስ 8፡51

“ዮሐንስ በከፍተኛ ደረጃ የክርስቶስን ወዳጅነት ያገኘ ይመስላል፤ በዚህም አዳኙ ለእርሱ ያለውን እምነትና ፍቅር የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶችንም ተቀብሏል። በመገለጥ ተራራ ላይ የሆነውን የክርስቶስን ክብርና በጌቴሴማኒ የነበረውን ጣር እንዲመሰክሩ ከተፈቀደላቸው ሦስት ሰዎች አንዱ ነበር። ጌታችንም በመስቀል ላይ ሳለ በእነዚያ የመጨረሻ የጭንቀት ሰዓታት ውስጥ እናቱን እንድንከባከባት አምኖት የሰጠው ለእርሱ ነበር።”—The Acts of the Apostles, p. 539.

### ለ. ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የሚለየው እንዴት ነበር? ዮሐንስ 13:23፤ 21:20፣ 24

“ዮሐንስና ያዕቀብ፣ እንድርያስና ጴጥሮስ፣ ከፊልጶስ፣ ናትናኤልና ማቴዎስ ጋር፣ ከሌሎቹ ይልቅ ከእርሱ ጋር በጣም የተቀራኙ ነበሩ፣ እና ብዙ ተአምራቱን አይተዋል። ጴጥሮስ፣ ያዕቀብና ዮሐንስም ከእርሱ ጋር የበለጠ የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው። ሁልጊዜ ማለት በሚያስችል መልኩ ተአምራቱን እያዩ እና ቃሉንም እየሰሙ ከእርሱ ጋር ነበሩ። ዮሐንስ ከየሱስ ጋር ከሁሉም የበለጠ የቀረበ ቅርርብ ፈጥሯል፣ ስለዚህም የሱስ የሚወደው ሰው እንደሆነ ተገልጿል። አዳኙ ሁሉንም ይወዳቸዋል፣ ነገር ግን ዮሐንስ በጣም ተቀባይ መንፈስ ነበረው። ከሌሎቹ በዕድሜ ታናሽ ነበር፣ እናም ልክ ልጆች እንደሚያምኑት ልቡን ለየሱስ ሰጠ እናም በእርሱ በኩል የአዳኙ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊ ትምህርቶች ለሕዝቡ ተላልፈዋል።”—The Desire of Ages, p. 292.

## ሀ. የሱስ ለዮሐንስና ለወንድሙ ለያዕቆብ የሰጠው ስም ትርጉም ምንድን ነው? ማርቆስ 3:17

"ዮሐንስ በኋለኛው ተሞክሮው የተገለጠው የሚወድደው ባህርይው በተፈጥሮው አልነበረውም። በተፈጥሮው ከባድ ጉድለቶች ነበሩበት። ኩሩ፣ ራሱን የሚያስከብር፣ ለክብር የሚጓጓ ብቻ ሳይሆን ችኩል እና ተጎዳሁ ብሎ ሲያስብ ቂም የሚይዝ ነበር። በተወደዱት ደቀ መዛሙርት መካከል ሳሉ እሱና ወንድሙ 'የነጎድጓድ ልጆች' ተብለው ይጠሩ ነበር። ክፉ ቁጣ፣ የበቀል ፍላጎት፣ የትችት መንፈስ ሁሉ ነበረባቸው። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በታች የተሸፈነውን መልካም፣ ቅንና አፍቃሪ ልብን መለኮታዊው መምህር አይቶ ነበር። የሱስ ራስ ወዳድነቱን ገሠጸ፣ ምኞቱን ነቀፈ፣ እምነቱን ፈተነ። ከዚያም ነፍሱ የምትናፍቀውን የቅድስና ውበት፣ የፍቅርን የመለወጥ ኃይል ገለጠለት።"—The Acts of the Apostles, p. 540.

## ለ. ዮሐንስ ከሌሎች ጋር አዲስ ግንኙነት የመፍጠርን መንገድ እንዴት ተማረ? ዮሐንስ 13:34፤ 1ኛ ዮሐንስ 4:7፣ 8።

በጸጋ ለማደግ እና ለሥራው ብቁ ለመሆን ታማኝነት፣ ትሕትና እና ፍቅር አስፈላጊ መሆናቸውን የሚገለፁት የክርስቶስ ትምህርቶች ለዮሐንስ ከፍተኛ ዋጋ ነበራቸው። እያንዳንዱን ትምህርት ዋጋ ሰጥቶ ይመለከት ነበር፣ እናም ሕይወቱን ከመለኮታዊ እቅድ ጋር ለማስማማት ዘወትር ይፈልግ ነበር። ዮሐንስ ተስፋ ያደርገው የነበረውን ዓለማዊ ክብር እና ኃይል ሳይሆን፣ የክርስቶስን ክብር ማስተዋል ጀመረ ፡ ከዚያም 'አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን'። ዮሐንስ 1:14" —Ibid., p. 544.

## ሐ. ለባልንጀሮቻችን የምናሳየው በፍቅር የተሞላ ልብ ውጤቶችን ግለጽ። 1ኛ ዮሐንስ 3:10፣ 11፤ ዮሐንስ 13:35።

"ዮሐንስለጌታው ያሳየው ጥልቅ ፍቅር ክርስቶስ እርሱን ስለወደደው ብቻ ሳይሆን የዚያ የታላቁ ፍቅር ውጤት ነበር። ዮሐንስ የሱስን ለመምሰል ይፈልግ ነበር፣ እናም በክርስቶስ፣ በሚቀይር ፍቅር ተጽዕኖ ስር ቅንና ትሑት ሆነ። ማንነቱ በየሱስ ውስጥ ተሰወረ። ደግሞም ከሁሉም ጓደኞቹ በላይ ዮሐንስ ለዚያ አስደናቂ ሕይወት ኃይል ራሱን አሳልፎ ሰጠ። . . . ዮሐንስ አዳኙን በተግባራዊ እውቀት ያውቅ ነበር። የጌታው ትምህርቶች በነፍሱ ላይ ተቀርጸዋል። ስለ አዳኙ ጸጋ ሲመሰክር፣ ቀላል ቋንቋዎቹ በመላው ማንነቱ ውስጥ ከተንሰራፋው ፍቅር የተቀዱ ነበሩ።"—Ibid., pp. 544, 545.

## ሀ. የዮሐንስን ሕይወት ለማጥፋት የተደረጉ ሙከራዎች ሳይሳኩ ሲቀሩ በመጨረሻ ወደ የት ተላከ? ራዕይ 1:9

*"ዮሐንስ... ስለ እምነቱ እንድፈረድበት ወደ ሮም ተጠራ። እዚያ በባለሥልጣናት ፊት የሐዋርያው ትምህርቶች በተሳሳተ መልኩ ቀረቡ። የሐሰት ምስክሮች ዓመፅን እንደሚያስተምር አደድርገው ከሰሱት። ጠላቶቹ በእነዚህ ክሶች ውጤት የደቀ መዛሙሩን ሞት ተስፋ አድርገው ነበር።*

*"ዮሐንስ ደግሞ ግልጽና አሳማኝ በሆነ መንገድ መልስ ሰጠ፣ ምንም እንኳ በጣም ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ቢናገርም ቃላቶቹ ኃይለኛ ውጤት አስገኝተዋል። አድማጮቹ በጥበቡና በአንደበተ ርቱዕ ንግግሩ ተደነቁ። ነገር ግን ምስክርነቱ አሳማኝ በሆነ ቁጥር የተቃዋሚዎቹ ጥላቻ የበለጠ እየጨመረ ሄደ። . . .*

*"ዮሐንስ በባልዲ በፈላ ዘይት ውስጥ ተጣለ፤ ጌታ ግን ልክ ሦስቱን ዕብራውያን ከእሳት እቶን ውስጥ እንዳዳናቸው ሁሉ የታማኙን ባሪያውን ሕይወት አተረፈ። "በዚያ አታላይ፣ በናዝሬቱ የሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ እንዲሁ ይጠፋሉ" በሚባልበት በዚያ ጊዜ፤ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፣ "ጌታዬ ሰይጣንና መላእክቱ ሊያዋርዱትና ሊያሰቃዩት የቻሉትን ሁሉ ሲያደርጉ በትዕግስት ዓለምን ለማዳን ሕይወቱን ሰጥቷል። ስለ እርሱ መከራ እንድቀበል ስለተፈቀደልኝ ክብር ይሰማኛል።". . . .*

*"እነዚህ ቃላት ተጽዕኖ አሳድረዋል፤ ዮሐንስንም ባልዲው ውስጥ የጣሉት ሰዎች ራሳቸው እንደገና አወጡት። . . . . "በንጉሠ ነገሥቱ ትዛዝ ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተጋዘ። . . .*

*"ጠላቶቹ በእዚህ የዮሐንስ ተጽዕኖው ከእንግዲህ እንደማይሰማ፣ በመጨረሻም በችግርና በጭንቀት እንደሚሞት አሰበው ነበር።"*—The Acts of the Apostles, pp. 569, 570.

## ለ. ወደ ፍጥሞ መጋዙ ምን ውድ ዕድል አስገኝቶለታል? ራዕይ 1:1–3፣ 10፣ 11

*"ፍጥሞ በኤጂያን ባሕር ውስጥ ያለች ባዶና ድንጋያማ ደሴት ስትሆን በሮማውያን መንግሥት ለወንጀለኞች የግዞት ቦታ ሆና ተመርጣ ነበር፤ ለእግዚአብሔር አገልጋይ ግን ይህ ጨለማ መኖሪያ ቦታ የሰማይ በር ሆነለት። እዚህ፣ ከሕይወት የመባዘን ትዕይንቶች እና ከቀደሙት ዓመታት ድካሞች ተገልሎ፤ የእግዚአብሔር፣ የክርስቶስና የሰማያዊ መላእክት ወዳጅ ሆኖ ነበር።*

*ከእነርሱም ለወደፊት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን የሆነን መመሪያ ተቀበለ። በዚህች ምድር ታሪክ የመጨረሻ ትዕይንቶች ውስጥ የሚከናወኑት ክስተቶች በፊቱ ተዘርዘሩ፤ እናም እነዚያን ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን ራእዮች ጻፈ።"*—Ibid., pp. 570, 571.

## 4. መለኮታዊ ጉብኝት ከክርስቶስ ጋር ረቡዕ፣ ግንቦት 12

### ሀ. ክርስቶስ በፍጥሞ በራእይ ለዮሐንስ እንዴት ተገለጠለት? ራዕይ 1:12–16

*"የተወደደው ደቀ መዝሙር ጌታውን ፊቱ በደም ጠብታዎች ሲሞላ፣ በጌቴሴማኒ አይቶታል፤ "ፊቱ ከሰው ልጆች ይልቅ፣ መልኩም ከሰዎች ልጆች ይልቅ የተጎሳቀለ ነበር።' ኢሳይያስ 52:14። በሮማውያን ወታደሮች እጅ ውስጥ አሮጌ ሐምራዊ ልብስ ለብሶ የእሾህ አክሊል ተጭኖበት አይቶታል። በቀራንዮ የጭካኔ ፌዝና ስድብ መሳርያ በሆነው መስቀል ላይ ተሰቅሎ አይቶታል። አሁን ዮሐንስ ጌታውን እንደገና እንዲያይ ተፈቅዶለታል።*

*"ነገር ግን መልኩ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተለውጧል! ከእንግዲህ በሰዎች የተናቀ እና የተዋረደ ሰው አይደለም። የሰማያዊ ብርሃን ልብስ ተጎናፅፏል። . . . ፍጥሞ ከሞት በተነሣው ጌታ ክብር ደመቀች።"*—The Acts of the Apostles, p. 582.

### ለ. የዮሐንስ ምላሽ ምን ነበር፣ እናም የሱስ ለእሱ ምን ተልእኮ ሰጥቶት ነበር? ራዕይ 1:17–19

*"ዮሐንስ በከበረው ጌታ ፊት ለመኖር ብርታት አገኘ። ከዚያም በአስደናቂው ራእዩ ውስጥ የሰማይ ክብር ተገለጠ። የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲያይ ተፈቀደለት፤ ከምድር ተጋድሎዎች ባሻገርም ነጭ ልብስ የለበሱትን የተቤዣቸውን ሰዎች ተመለከተ። የሰማይ መላእክትን ዜማና በበጉ ደምና በምስክርነታቸው ቃል ድል ያደረጉትን ሰዎች የድል ዝማሬ ሰማ። ለእርሱ በተሰጠው ራዕይ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የሚገጥሟቸውን አስደናቂ ነገሮች እና እስከ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተራ በተራ ተተነበየ። ለዮሐንስ ይመዘግባቸው ዘንድ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች በምሳሌዎችና በምልክቶች ቀርበውለታል፤ ይህም በእርሱ ዘመንና በሚመጣው ዘመን የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከፊታቸው ስላሉት አደጋዎችና ተጋድሎዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ነው።"*—Ibid., pp. 582, 583.

### ሐ. የራዕይ መጽሐፍ ለእኛ በግል መልእክት የሚሆነው እንዴት ነው? ራዕይ 1:4–6፤ 3:22

*"ይህ ራዕይ የተሰጠው በክርስትና ዘመን ሁሉ ለቤተክርስቲያን መመሪያና መፅናናት እንዲሆን ነው። ሆኖም የሃይማኖት አስተማሪዎች የታተመ መጽሐፍ እንደሆነና ምስጢሩም ሊገለጽ እንደማይችል ይናገራሉ። ስለዚህ ብዙዎች ከትንቢታዊ መፅሀፍት ዘወር በማለት፤ ጊዜያቸውን ሰጥተው ምስጢራቸውን ለማጥናት ፈቃደኛ አይደሉም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡ መጽሐፉን በዚህ መንገድ እንዲያዩት አይፈልግም።"*—Ibid., p. 583.

## 5. የክርስቶስ መገኘት መረጋገጥ ሐሙስ፣ ግንቦት 13

## ሀ. በራእዩ ውስጥ የክርስቶስ በሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል መሆን ምንን ያመለክታል? ራእይ 1:20

"ክርስቶስ በወርቃማ መቅረዞች መካከል እንደሚራመድ ተነግሯል። ይህ ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያል። እርሱ ከሕዝቡ ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት አለው። በእውነት ያሉበትን ሁኔታቸውን ያውቃል። ሥርዓታቸውን፣ ቅድስናቸውንና ታማኝነታቸውን ይመለከታል። በሰማያዊው መቅደስ ሊቀ ካህናት እና አስታራቂ ቢሆንም፤ በምድር ላይ ባሉ አብያተ ክርስቲያናቱ መካከል እንደሚመላለስ ተደርጎ ተገልጿል። በማያቋርጥ ንቃት የማንኛው ጠባቂዎቹ ብርሃን እየደከመ ወይም እየጠፋ መሆኑን ይመለከታል። መቅረዞቹ ለሰው እንክብካቤ ተትተው ቢሆን ኖሮ፣ የሚንበለበለው እሳት ይዳከምና ይጠፋል፤ ነገር ግን እርሱ በጌታ ቤት ውስጥና መቅደሱ አደባባይ እውነተኛ ጠባቂ ነው። የእርሱ ቀጣይነት ያለው እንክብካቤ እና ዘላቂ ጸጋ የሕይወትና የብርሃን ምንጭ ናቸው።"—The Acts of the Apostles, p. 586.

## ለ. በራእይ ምዕራፍ 2 እና 3 ውስጥ እግዚአብሔር በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ለተወከሉት ለአጠቃላዩ ቤተክርስቲያን የላካቸውን መልእክቶች ዓላማ ግለጽ።

"የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ስሞች በተለያዩ ጊዜያት የነበሩትን የቤተክርስቲያንን ዘመን የሚወክሉ ናቸው። 7 ቁጥር ፍፁምነትን ያመለክታል፤ እናም መልዕክቶቹ እስከ ዘመን ፍጻሜ ድረስ የሚዘልቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ምሳሌያዊ ሲሆን፤ ጥቅም ላይ የዋሉት ምልክቶቹ ደግሞ በዓለም ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የነበረውን የቤተክርስቲያንን ሁኔታ ያሳያሉ።"—Ibid., p. 585.

"ቤተክርስቲያኒቱ ጉድለት ነበረባት ፡ ከባድ ተግሣጽ እና ቅጣት ያስፈልጋት ነበር፣ እናም ዮሐንስ የወንጌልን መሠረታዊ መርሆዎች ችላ ብለው የመዳን ተስፋቸውን አደጋ ላይ ለጣሉ የማስጠንቀቂያ፣ የተግሣጽ እና የልመና መልዕክቶችን ለመጻፍ ተነሳስቶ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚልካቸው የተግሣጽ ቃላት የሚነገሩት በርኅራኄ ፍቅር እና ለእያንዳንዱ ንስሐ ለሚገባ አማኝ በሚሆን በሰላም ተስፋ ነው።"—Ibid., p. 587.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ግንቦት 14

1. የሱስ የሚመርጠው ባይኖረውም፤ ዮሐንስ የተወደደው ደቀ መዝሙር ተብሎ የተጠራው ለምንድን ነው?
2. በዮሐንስ ሕይወትና ባሕርይ ላይ ለውጥ የፈጠረው ምንድን ነው?
3. እግዚአብሔር ዮሐንስን ለማጥፋት የሞከሩትን ክፉ ሰዎች ዓላማ እንዴት አስወገደው?
4. ብዙ ጊዜ በስህተት፣ የታተመ (ምስጥር) መጽሐፍ ተብሎ ቢጠራም፤ ራዕይ ለእኛ ምን ማለት ነው?
5. እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ የተግሣጽ መልዕክቶችን በመላክ ረገድ ያለውን ዓላማ ግለፅ።

## ሰንበት፣ ግንቦት 22፣ 2018 — 9ኛ ትምህርት

# ዘንዶው፣ ሴቲቱ እና ቅሬታዎች

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ።” (ራዕይ 12፡17)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 582–592.

“ብዙ መስዋዕትነት ያስከፈለው የእምነት ነፃነት ከእንግዲህ አይከበርም። በቅርቡ በሚመጣው ግጭት በነቢዩ ተነገሩት ቃላት እውን ሲሆኑ እናያለን።”—The Great Controversy, p. 592.

## 1. ቤተክርስቲያን ተገለጠች — እሁድ፣ ግንቦት 16

### ሀ. በዮሐንስ አራተኛ ራዕይ መጀመሪያ ላይ የሚታየው ምንድን ነው? ራዕይ 12፡1

### ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌያዊ አሰጣጥ፤ ሴት ምንን ተወክላለች? 2ኛ ቆሮንቶስ 11:2፤ ሕዝቅኤል 23:2–4፤ ራእይ 17:3–6

“በራዕይ 17 ባቢሎን በሴት ተመስላ ቀርባለች፤ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ተደርጎ የተቀመጠ ሲሆን መልካም ባህርይ ያላት ሴት ንጽህት ቤተ ክርስቲያንን ስትወክል፣ ምግባረ ብልሹዋ ሴት ደግሞ ከሃዲዋን ቤተ ክርስቲያን ትወክላለች።

“በመጽሐፍ ቅዱስ፣ የተቀደሰውና ዘላቂ የሆነ ባህርይ ያለው በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል የሚኖረው ግንኙነት በጋብቻ ጥምረት ምሳሌ የተወከለ ነው። በእውነተኛ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ከራሱ ጋር አቀራኝቷቸዋል፤ እርሱ አምላካቸው ሊሆን ቃል ገብቶ፣ እነርሱም የእርሱና የእርሱ ብቻ ሊሆኑ ቃል ገብተዋል። እንዲህ ይላል፦ “ለእኔም ለዘላለም አጭሻለሁ በጽድቅና በፍርድ በምሕረትና በርኅራኄም አጭሻለሁ” [ሆሴ 2÷19]። እንደገናም “እኔ ባላችሁ ነኝ” [ኤር 3÷14] ይላል። ጳውሎስም ተመሳሳዩን ተምሳሌት በአዲስ ኪዳን እንዲህ ሲል ይጠቀመዋል፣ “እንደ ንጽህት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና።” [2ኛ ቆሮ 11÷2]።”—The Great Controversy, p. 381.

## ሀ. ቤተ ክርስቲያን የሕፃኑን መሲሕ መምጣት እንዴት ባለ መጠባበቅ ጠበቀች? ራዕይ 12:2፤ ኢሳይያስ 9:6፤ ሉቃስ 2:25–32

*“የያዕቆብ የመጨረሻ ቃላት [በአይሁድ መካከል ያሉትን ታማኝ ሰዎች] ተስፋ ሞልቶባቸው ነበር። “በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፥ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፥ ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፤ የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል።” ዘፍጥረት* 49:10 *የእስራኤል ኃይል እየጠፋ መምጣቱ የመሲሑ መምጣት እንደቀረበ መስክሯል። የዳንኤል ትንቢት የምድራዊ መንግሥታትን ሁሉ የሚተካውን መንግሥት የአገዛዝ ክብር አመልክቷል፤ “ለዘላለምም ትቆማለች” ብሏል። ዳንኤል* 2:44 *የክርስቶስን ተልዕኮ ባህሪ የተረዱት ጥቂቶች ቢሆኑም፤ በስፋት መንግሥቱን በእስራኤል የሚያቋቁምና ለሕዝቡ አዳኝ ሆኖ የሚመጣ ኃያል ልዑል ይጠባበቁ ነበር።*

*“የዘመኑ ፍጻሜ ደርሶአል።” የሰው ልጅ ለዘመናት በዘለቀው ኃጢአቱ እየተበላሸ በመምጣቱ፤ የቤዛውን መምጣት አስፈልጓል።”*—The Desire of Ages, p. 34.

## ለ. በታላቁ ቀይ ዘንዶ የተወከለው የትኛው ገዢ ኃይል ነው? ራዕይ 12:3

*“በታላቅ ቀይ ዘንዶ፣ በነብር መሰል አውሬ እና የበግ ቀንድ ባለው አውሬ ምልክቶች፤ የእግዚአብሔርን ሕግ በመርገጥ እና ሕዝቡን በማሳደድ የሚሳተፉት ምድራዊ መንግሥታት ለዮሐንስ ተገልጠዋል።”*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 972.

## ሐ. በዚህ ዘንዶ መሰል ኃይል ምክንያት ቤተክርስቲያን እና መሲሑ ምን አደጋ ገጠማቸው? ራዕይ 12:4

*“ሰይጣን በምድርና በሰማይ መካከል ያለውን ገደል ጥልቅና ሊታለፍ የማይችል ለማድረግ ሲሰራ ቀይቷል። በውሸቶቹ ሰዎችን በኃጢአት አበረታቷቸዋል። የእግዚአብሔርን ትዕግስት መጨረስ እና ለሰው ያለውን ፍቅር በማጥፋት፤ ዓለምን ለሰይጣን ስልጣን አሳልፎ እነዲሰጣት ማድረግ ዓላማው ነበር።”*—The Desire of Ages, pp. 34, 35.

*“በሰማይ የነበረው ሰይጣን ክርስቶስን በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ስላለው ቦታ ጠልቶት ነበር። ከዙፋኑ ሲወርድ ደግሞ የበለጠ ጠላው። የኃጢአተኞችን ዘር ለመዋጀት ራሱን አሳልፎ የሰጠውን ጠላው። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ሰይጣን ገዢ እንደሆነባት ወደሚቀጥራት ዓለም ልጁን እንደ ሰው የሚደክምና እንደ አቅመ ቢስ ሕፃን ሆኖ እንዲመጣ አደረገው። እያንዳንዱ የሰው ልጅ በውድቀት እና በዘላለም ጥፋት አደጋ መሀል የሕይወትን ፈተናዎች መጋፈጥ እንዳለበት ሁሉ እርሱም ከእያንዳንዱ የሰው ነፍስ ጋር አብሮ የሕይወትን ፈተናዎች እንዲጋፈጥና እንዲዋጋ ተወው።*—Ibid., p. 49.

## ሀ. ለዮሐንስ ስላለፈውን ጊዜ ምን ግንዛቤ ተገለጠለት፣ ይህስ ምን ማለት ነው? ራዕይ 12:79

"የእግዚአብሔርን ሕግ መቃወም የተጀመረው በሰማይ፤ በሚጋርደው ኪሩብ በሉሲፈር ነው። ሰይጣን በሰማይ ጉባኤዎች ውስጥ የመጀመሪያው ለመሆን እና ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ለመሆን ፈለገ።

በእሱ ትዕዛዝ ስር ባሉት መላእክት ያለመርካትንና የአመፅን መንፈስን በመካከላቸው ለማሰራጨት በመፈለግ የአመፅ ሥራውን ጀመረ። እናም ዓላማው ሙሉ በሙሉ ከመታወቁ በፊት ብዙ መላእክት በታማኝነት እስኪሸነፋለት ድረስ እጅግ አታላይ በሆነ መንገድ ሠራ። ታማኝ የነበሩት መላእክት እንኳን ባህሪውን ሙሉ በሙሉ ሊረዱት ወይም ስራው ወደየት እያመራ እንዳለ ማየት አልቻሉም። ሰይጣን ብዙ መላእክትን ከጎኑ እንዲቆሙ በማሸነፉ ሲሳካለት፤ ክርስቶስ የያዘውን ቦታ እንዲይዝ የመላእክት ፍላጎት መሆኑን በመግለጽ ጉዳዩን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ።

"ያለመርካቱ መንፈስ ወደ ብርቱ አመፅ እስኪለወጥ ድረስ ክፋት መሥራቱን ቀጠለ። ከዚያም በሰማይ ጦርነት ሆነ፤ ሰይጣንም ከእርሱ ጋር ከነበሩት ሁሉ ጋር ተባረረ።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, pp. 972, 973.

## ለ. በራዕይ 12:10፣ 11 ላይ የተገለጸው ሀሳብ በየሱስ አገልግሎት ወቅት የሰይጣን መጣሉን እንዴት ያመለክታል?

"ክርስቶስ በትንቢታዊ ዓይን በመጨረሻው ታላቅ ተጋደሎ ውስጥ የሚከናወኑ ሁነቶችን ተመልክቷል። 'ተፈጸመ' ብሎ ሲጮህ ሰማያት ሁሉ ድል እንደሚያደርጉ ያውቅ ነበር። ጆሮው የሩቅ ከሰማያዊው አደባባይ ውስጥ የሙዚቃ እና የድል ጩኸቶችን ሰምቶ ነበር። የሰይጣን ግዛት ኃይል የማብቂያ ደውል ድምፅ እንደሚሰማ እና የክርስቶስ ስም ከአለም እስከ ዓለም በመላው ዩኒቨርስ እንደሚታወጅ ያውቅ ነበር።"—The Desire of Ages, p. 679.

"የመዳን ዕቅድ ከሰው ልጅ መዳን የበለጠ ሰፊ እና ጥልቅ ዓላማ ነበረው። ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ለዚህ ብቻ አልነበረም፤ የዚህች ትንሽ ዓለም ነዋሪዎች የእግዚአብሔርን ሕግ መታየት እንደሚገባው አድርገው እንዲመለከቱት ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ባሕርይ በአጽናፈ ዓለም ፊት ለማጽደቅ ነበር። ክርስቶስ ለሰው ልጅ መዳን ሲል የመሞቱ ተግባር ሰማይን ለሰዎች ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ፣ በመላው አጽናፈ ዓለም ፊት እግዚአብሔርና ልጁ ከሰይጣን ዓመፅ ጋር ባላቸው ግንኙነት ራሳቸውን ያጸድቃሉ። የእግዚአብሔርን ሕግ ዘላቂነት ያረጋግጣል፣ እናም የኃጢአትን ባህሪይና ውጤት ይገልጣል።"—Patriarchs and Prophets, pp. 68, 69.

## ሀ. አሁን ለቤተክርስቲያን ምን ተጨማሪ አደጋ ይመጣል? ራዕይ 12:12፣ 13

"ሰይጣን፣ የወረሰው ግዛት በመጨረሻ ከእሱ እንደሚነጠቅ ስለሚያውቅ፣ እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረውን ፍጥረታት ሁሉ ለማጥፋት ያለውን ሃይል ምንም ሳይቆጥብ እየሰራ ነው። ክርስቶስ እንዲህ ዓይነቱን ይቅር ባይ ፍቅርና ርኅራኄ ለሰው ስላሳየ ሰይጣን ሰውን ጠልቶታል፤ እናም አሁን ሊያጠፋው የሚችልበትን ማንኛውንም ዓይነት የማታለል ዘዴ በእርሱ ላይ ለመተግበር ተዘጋጅቷል፤ ሰይጣን በራሱ ተስፋ ቢስ ሁኔታ ውስጥ ስላለ የማታለል ሥራውን በሃይል እየገፋበት ነው።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, pp. 973, 974.

"መጨረሻው እየቀረበ ሲሔድ በመልካምና በክፋት መካከል ያለው ተቃርኖ(ተጋድሎ) በእጅጉ እየጨመረ ይሄዳል። የሰይጣን ቁጣ በዘመናት ሁሉ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሲገለጽ ኖሯል። የክፋትን ኃይል መቋቋም ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ ፀጋውንና መንፈሱን ሲለግስ ቆይቷል። የክርቶስ ሐዋርያት ወንጌሉን ተሸክመው ለዓለም ሊያደርሱ፣ ለወደፊት ዘመናትም ሊመዘግቡት በነበረበት ጊዜ፣ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ስጦታ በተለየ ሁኔታ ተበርክቶላቸው ነበር። ቤተ ክርስቲያን ወደ መጨረሻው ነጻ የምትወጣበት ጊዜ ስትቃረብ ግን ሰይጣን በታላቅ ኃይል ሥራውን ይሰራል። . . . ይህ ለዘመናት በዘለቀው ትንቅንቅ የካበተው ዲያቢሎሳዊ ጥበብና ብልጠት በሙሉ፣ የተሳለው አረመኔያዊነት ሁሉ በመጨረሻው ፍልሚያ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመውጋት የሚጠቀምበት ይሆናል። በዚህ የጥፋት ጊዜ "ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ" [2ኛ ጴጥ 3÷14] በፊቱ የሚቆም ሕዝብ ይዘጋጅ ዘንድ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የጌታን ዳግም ምፅዓት ማስጠንቀቂያ ለዓለም ያውጁ ዘንድ አላቸው። በዚህ ዘመን ያለው የመለኮታዊ ጸጋና ኃይል ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስፈላጊነት በሐዋርያት ዘመን ከነበረው ያነሰ አይደለም።"—The Great Controversy, pp. ix, x.

## ለ. በ1,260 ዓመታት የጭቆናና የስደት ዘመን የቤተክርስቲያንን ተሞክሮ ይግለጹ። ራዕይ 12:6፣ 14

## ሐ. ዘንዶው በታማኞች ላይ ሊጠቀምበት ያሰበውን የሰብዓዊ ወኪሎች ጥቃት ለማደናቀፍ ምን እርዳታ መጣ? ራዕይ 12:15፣ 16

"እያንዳንዱ ሰው የራሱን ድካም ፍሬ ሊደሰትበትና የህሊናውን እምነት ሊታዘዝበት የሚችልበት ዜና በአውሮፓ አገሮች ምድር ሲሰራጭ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ አዲሱ ዓለም ዳርቻ ተጉዘዋል።"—Ibid., p. 296.

## 5. ቅሬታዎቹ　　　　　　　　　　ሐሙስ፣ ግንቦት 20

## ሀ. የዘንዶው ቁጣ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ፣ ታማኞቹ እንዴት ይሆናሉ? ራእይ 12:17

ባለ ራዕዩ እስከ መጨረሻውን ዘመን እየተመለከተ እንዲህ ብሏል "ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ" ራእይ 12:17። ዛሬ በምድር ላይ የሚኖሩ አንዳንዶች እነዚህ ቃላት ሲፈጸሙ ያያሉ። ባለፉት ዘመናት ሰዎች እውነተኛውን ቤተክርስቲያን እንዲያሳድዱ ያደረገው ያው መንፈስ፤ ወደፊትም ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ለሚጠብቁ ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ እንዲሁ ያደርጋል። ለዚህ የመጨረሻ ታላቅ ተጋድሎ ከአሁኑ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው።"—Prophets and Kings, p. 605.

## ለ. የቅሬታዎቹ ባህሪያት በመጨረሻው ዘመን ያለችን ቤተክርስቲያንን እንዴት ይገልጻሉ? ራእይ 14:12፤ 19:10

"የቅሬታዋ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በሕጉ ታከብረዋለች እናም የትንቢት ስጦታ ይኖራታል። ለእግዚአብሔር ሕግና ለትንቢት መንፈስ መታዘዝ ሁልጊዜ እውነተኛ የሆኑትን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ይለያል፤ ፈተናም ብዙውን ጊዜ የሚሰጠው ልዩነትን ለመግለጥ ነው።"—Loma Linda Messages, p. 33.

"የቅሬታዋ ቤተ ክርስቲያን ወደ ታላቅ ፈተናና ጭንቀት ትገባለች። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እና የየሱስን እምነት የሚጠብቁ የዘንዶውን እና የሰራዊቱን ቁጣ ይቀበላሉ። ሰይጣን ዓለምን የእርሱ ተገዢ እንደሆነች ይቆጥራል፤ ከሃዲዎችን አብያተ ክርስቲያናትም በቁጥጥሩ ስር አድርጓል፤ ነገር ግን የእርሱን የበላይነት የሚቃወሙ ጥቂት የቅሬታዎች አሉ።"—Testimonies for the Church, vol. 9, p. 231.

"የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለማክበር ፈቃደኛ አለመሆን እና እነዚህን ትእዛዛት ለሚያውጁ ሰዎች ከፍ ያለ ጥላቻን መያዝ፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁትን ሰዎች ለመቋቋም ሙሉ ኃይሉን የሚጠቀመውን ዘንዶ ወደ ከባድ ጦርነት ይመራዋል።"—Ibid., vol. 8, p. 117.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች　　　　　　　　　　አርብ፣ ግንቦት 21

1. ቤተክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሴት የተመሰለችው ለምንድን ነው?
2. የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሰው ወደ ምድር ለመምጣት የወሰደውን ሀላፊነት አብራራ።
3. ሰይጣን ከሰማይ መባረሩ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀው መቼ ነው?
4. በቤተክርስቲያን ላይ የዘንዶውን ቁጣ ምክንያት ግለጽ።
5. ቅሬታቹን በምንመለከትበት ጊዜ ምን አይነት ባህሪያትን እንጠብቃለን?

# ግንቦት 29፣ 2018

# የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ



## ከፕራግ፣ ቼክ ሪፐብሊክ የጸሎት ቤት

ቼክ ሪፐብሊክ በአውሮፓ እምብርት ውስጥ የምትገኝ ሀገር ስትሆን ከጀርመን፣ ከፖላንድ፣ ከኦስትሪያ እና ከስሎቫኪያ ጋር የምትዋሰን ሀገር ናት። በዚህች ጆን ሃስ (1369) ታላላቅ ተሃድሶዎቹን በጀመረባት ሀገር ውስጥ የቦሂሚያ ውብ መንደሮች፣ ግርማ ሞገስ ያላቸው ቤተ መንግሥቶች እና የበለፀገ የባህል እና መንፈሳዊ ቅርስ ያለው ታሪካዊ ክልሎች ይገኛሉ። በዛሬው ጊዜ ወደ 10.9 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች የሚኖሩባት ዘመናዊ ከተማ ስትሆን ከእነዚህም ውስጥ ከ1.4 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በዋና ከተማዋ ፕራግ ይኖራሉ።

ፕራግ የታሪካዊ እና የባህል ማዕከል ብቻ ሳይሆን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በልባቸው ውስጥ የሕይወትን ትርጉም፣ ተስፋ እና ሰላም የሚፈልጉ ሰዎች ያሉበት መንፈሳዊ ፍላጎት ያለባት ቦታ ናት። ከነዋሪዎቹ መካከል 47.8% የሚሆኑት ሃይማኖት የለሽ እንደሆኑ ይቆጠራሉ፤ 11.7% የሚሆኑት ደግሞ ክርስቲያን ሲሆኑ (ከእነዚህም ውስጥ 9.3% የሚሆኑት ካቶሊክ እንደሆኑ እና 2.4% የሚሆኑት ሌላ የክርስትና እምነት ቡድኖችእንደሆኑ ይነገል) ፣ እናም 10.8% የሚሆኑት ከሌሎች ሃይማኖቶች ይመደባሉ።

በዚህች ከተማ የአድቬንቲስት የተሃድሶ እንቅስቃሴ ሥራ የተጀመረው በግንቦት 2014 ሲሆን ለመጀመሪያው ስብሰባ ተሰብስበው የነበሩት ሦስት ሰዎች ብቻ ነበሩ። በኋላም በነሐሴ 2020 አንድ መጋቢ እና ቤተሰቡ ለጠፉ ነፍሳት የመዳንን የእውነት መልእክት ለማወጅ ወደዚህ ተልከዋል።

ዛሬ የፕራግ ጉባኤ 30 የቤተክርስቲያን አባላት ያሉ ሲሆን፤ ፍላጎት ካላቸው እና ለጥምቀት ከሚዘጋጁት ጋር 70 ያህል ሰዎች አሉ። የአምልኮ ሥርዓቶች በአሁኑ ጊዜ ኪራይ ቦታ ውስጥ እየተካሄዱ ነው።ግን ምዕመናኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሰበሰብበትን፣ በእምነት የሚጠናከርበትን እና በዙሪያቸው ካሉት ሰዎች ጋር የእውነትን ብርሃን የሚያካፍልበትን የራሳቸውን የጸሎት ቤት የመግዛት ወይም የመገንባት እድል ለማግኘት ከልብ እየጸለዩ ነው።

“እግዚአብሔር የሚመለክበት ቤት ባህሪውንና ክብሩን የሚመን መሆን አለበት።”—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 268.

ውድ ወንድሞችና እህቶች፣ ዛሬ በዚህ ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ ላይ የመሳተፍ የተባረከ እድል አለን። ስጦታችሁ ለዘላለም እና በመሃል አውሮፓ ላይ ያለችውን ቤተክርስቲያን ለነፍሶች መዳን እና ማጠናከር የሚያስችል ኢንቨስትመንት ነው። እባካችሁ የእግዚአብሔርን መመሪያ ለማግኘት ጸልዩ፣ ይህንን ፕሮጀክት በደግነት ደግፉ እና ይህንን ጥሪ ለሌሎች አካፍሉ። ጌታ በዚህ ሥራ በፍቅር የሚሳተፉትን ሁሉ ይባርክ!

“እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን” (1ኛ ተሰሎንቄ 1:2)

በፕራግ ያሉ ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ

## ሰንበት፣ ግንቦት 29፣ 2018

## 10ኛ ትምህርት

# አውሬው እና ምልክቱ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ።” (ራዕይ 13፡16)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 439–450.

*“እንደበግ ቀንድ ያሉ ቀንዶች ያሉት ግን እንደ ዘንዶ የሚናገረው አውሬ ምሳሌ፤ በምልክቱ በተወከለው ህዝብ እውነተኛ ተግባር እና ሀላፊነት መካከል ያለውን አስገራሚ ተቃርኖ የሚያመለክት ነው።”*—The Great Controversy, p. 442.

## 1. የተቀናጀው አውሬ — እሁድ፣ ግንቦት 23

**ሀ. ዮሐንስ በራዕይ 13፡1 (የመጀመሪያው ክፍል) ምን አየ፣ እና ይህንን በዳንኤል 7፡3 ጥናታችን ብርሃን እንዴት እንረዳዋለን?**

**ለ. የአውሬው አንዳንድ አካላዊ ባህሪያት ከዚህ በፊት ካጠናናቸው አራት እንስሳት ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ ከማወቅ ምን እንማራለን? ራዕይ 13:2፤ ዳንኤል 7:4–6።**

*“በምዕራፍ 13 [ከቁጥር 1-10] ሌላ አውሬ ተጠቅሷል። “ነብር ይመስል ነበር።” ዘንዶውም “ሃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ስልጣን” የሰጠው ነው። ይህ ተምሳሌት አብዛኛዎቹ ፕሮቴስታንቶች እንደሚያምኑት በጥንታዊው የሮም ግዛት ተይዞ የነበረውን ኃይል ዙፋንና ስልጣን የተካውን የጳጳሳዊውን ሥርዓት የሚወክል ነው። ነብር ስለሚመስለው አውሬ እንዲህ ተብሏል፣ “ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው.... እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውን በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ። ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው። በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ስልጣን ተሰጠው።” ይህ በዳንኤል 7 ላይ ከተጠቀሰው ትንሽ ቀንድ መግለጫ ጋር ሙሉ ለሙሉ አንድ አይነት ሊሆን ምንም የማይቀረው ትንቢት ያለምንም ጥርጥር የሚጠቁመው ወደ ጳጳሳዊው ሥርዓት ነው።”*—The Great Controversy, p. 439.

*“በብዙ የአውሮፓ አገሮች በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት ደረጃ የሚገዙት መሪዎች ለዘመናት በጳጳሳዊው ሥርዓት አማካኝነት በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ውለዋል።”*—Ibid., pp. 268, 269.

2. አሳዳጅ ኃይል ሰኞ፣ ግንቦት 24

*ሀ. በሥልጣኑ ዘመን በመመስረት የአውሬው ማንነት የሚረጋገጠው እንዴት ነው? ራእይ 13:5፤ ዳንኤል 7:25*

""አርባ ሁለት ወርም እንዲሰራ ስልጣን ተሰጠው።" ነቢዩ ሲናገር፣ "ከራሶቹም ለሞት እንደታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ" [I saw one of his heads as it was wounded to death) [ራእይ 13÷3]። እንደገናም "ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገደል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል።" አርባ ሁለቱ መለወጥ የማይችለው የእግዚአብሔር ሕግ 281 ወራት በዳንኤል 7 ላይ ካሉት ሶስት ዓመት ተኩል ወይም 1260 ቀናት "እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም" ከተባሉት ጋራ እኩል ናቸው። ይህም ጊዜ የጳጳሳዊው ስልጣን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጨቁንበት ዘመን ነበር። ይህ ጊዜ በቀደሙት ምዕራፎች እንደተገለጸው፣ ጳጳሳዊው ሥርዓት በ538 ዓ .ም ሲቋቋም የጀመረ ሲሆን በ1798 ዓ .ም አብቅቷል። በዚያን ጊዜ ጳጳሳዊው ስርዓቱ ተገርስሶ ሊቀ ጳጳሱም በፈረንሳይ ጦር እስረኛ ሲሆን ጳጳሳዊው ኃይል የሞቱ ቁስል ደረሰበት፤ እናም ሊማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል የሚለው ትንቢት ተፈፀመበት።"—The Great Controversy, p. 439

## ለ. የነብር መሰል አውሬ የበላይነት እንዴት ይመነምናል? ራዕይ 13:3 (የመጀመሪያ ክፍል)፣ 10

## ሐ. አውሬው ምን እርምጃዎችን ይወስዳል? ራዕይ 13:6–8

"ሮም በአንድ ወቅት ለስልጣንዋ አውቅና ይሰጡ በነበሩ አገራት ዘንድ የነበራት ተጽዕኖ፣ አሁንም ፈጽሞ አልጠፋም። ወደፊትም ኃይልዋ እንደሚታደስ ትንቢት ይናገራል። "ከራሶቹም ለሞት እንደታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፤ ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ። ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ አደነቀ" [ራእይ 13÷]። የደረሰበት ለሞቱ የሆነው ቁስል በ1798 ዓ.ም የጳጳሳዊ ሥርዓት የተገረሰሰበትን ያመለክታል። ከዚህ በኋላ፣ ነብዩ ሲናገር፦ "ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ፤ ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ አደነቀ።" የኃጢአቱ ሰው እስከ ዳግም ምፅዓት ድረስ እንደሚቀጥል ጳውሎስ በግልጽ ይናገራል [2ኛ ተሰሎ 2÷8]። እስከ ፍፃሜው ቀን ድረስ የማታለል ሥራውን ይቀጥልበታል። ባለ ራዕዩ ስለ ጳጳሳዊው ሥርዓት ጭምር ሲናገር፦ "በሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተፃፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል" ይላል [ራዕይ 13÷8]። በአሮጌው እና በአዲሱ ዓለም፣ በሮም ቤተ ክርስቲያን ስልጣን አማካኝነት ብቻ ለተቋቋመው የእሁድ ተቋም የሚሰጠው ክብር ለጳጳሳዊው ሥርዓት የሚሰጥ የክብር እውቅና ይሆናል።"—Ibid., p. 579.

## ሀ. የጳጳሱ ኃይል ለሞት የሚያደርስ ቁስሉን ሲቀበል ምን አዲስ የፖለቲካ ኃይል ብቅ አለ? ራዕይ 13:11

*"የበግ የሚመስሉ ቀንዶች የነበሩት አውሬ ግን የታየው "ከምድር ሲወጣ" ነበር። ራሱን ያቋቁም ዘንድ ሌሎች ኃይላትን ገልብጦ በመውጣት ፈንታ በዚህ የተወከለው መንግሥት፣ በፊት ተይዞ ባልነበረ ምድር መነሳት ያለበት ሲሆን፣ ቀስ በቀስ በሰላማዊ መንገድ የሚያድግ ይሆናል። "ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም ቋንቋዎችም" ያሉበት፣ በሚናወጥ ባህር፣ ከተጨናነቀውና ከሚታገለው የአሮጌው ዓለም ሕዝብ መካከል የሚነሳ አይሆንም ማለት ነው። በምዕራባዊው አሕጉር መታሰስ አለበት።*

*በ1798 ዓ.ም እያደገ የነበረ ኃይል፣ የጥንካሬና የታላቅነት ተስፋ ሰንቆ የዓለምን ትኩረት እየሳበ የነበረ የአዲሱ ዓለም መንግሥት ማን ነበር? የተምሳሌቱ ፍቺ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም። የዚህን ትንቢት ዝርዝር የሚያሟላ አገር አንድና አንድ ብቻ ነው። ያለምንም ጥርጥር የሚያመለክተው ወደ ተባበሩት አሜሪካ (United States of America) ነው። ከቅዱሱ ፀሐፊ ቃላት ጋር ሙሉ ለሙሉ አንድ ሊሆኑ ምንም ባልቀራቸው የሚደጋገሙ ሐሳቦች፣ ስለዚህች አገር መነሳትና ማደግ፣ ተናጋሪውና የታሪክ አዋቂው በውል ሳያስተውል በተመሳሳይ ቋንቋ ገልጾታል። አውሬው የታየው "ከምድር ሲወጣ" ነበር፤ እንደ ተርጓሚዎች ከሆነ እዚህ ላይ የተጠቀመው "ሲወጣ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ሲያድግ ወይም እንደ ቡቃያ ሲያቆጠቁጥ" ማለት ነው። እንደተመለከትነውም ይህች አገር ቀደም ብሎ ባልተያዘ ምድር መነሳት አለባት። . . .*

*"የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት።" የበግ ቀንድ የሚመስሉት ቀንዶች ወጣትነትን፣ የዋህነትንና ገርነትን የሚያመለክቱ ሲሆን፣ ለነብዩ "ሲወጣ" ተብሎ የተነገረውን በ1798 ዓ.ም የአሜሪካ የነበራትን ባህርይ በትክክል የሚገልጽ ነው። መጀመሪያ ወደ አሜሪካ ኮብልለው የሄዱት ክርስቲያኖች ከንጉሣዊ ጭቆናና ከኃይማኖት መሪዎች ተቀባይነት ማጣት ለመራቅ ፍላጎታቸው ነበረ። በግለሰባዊና በሐይማኖታዊ ነፃነት ሰፊ መሰረት ላይ የቆመ መንግሥት ለማቋቋም ቁርጥ ሃሳብ ነበራቸው። የነፃነት አዋጁ፣ "ሰዎች ሁሉ የተፈጠሩት እኩል ነው" የሚለውን ታላቅ እውነት የያዘ "ለሕይወት፣ ለነፃነትና ለደስታ መሻት" ያለውን ሊጣስ የማይችል መብት የተጎናፀፉ ናቸው ሲል ያስቀምጠዋል። በሕዝቡ የተመረጡ ወኪሎች ሕግ እንዲያወጡና ያንን ሕግም እንዲያስተዳድሩ የሚያደርግ፣ ህገ መንግሥቱ ለሕዝቡ በራሳቸው የመተዳደርን መብት የሚያረጋግጥ ነው። እያንዳንዱ ሰው ህሊናው በመራው መንገድ እግዚአብሔርን ማምለክ ይችል ዘንድ የኃይማኖት ነፃነትም ተሰጥቶ ነበር። ሪፐብሊካዊነትና ፕሮቴስታንታዊነት የሃገሪቱ አብይ መርሆዎች ሆኑ። የኃይልዋና የብልጽግናዋ ምስጢራት እነዚህ መርሆዎች ናቸው። በክርስቲያኑ ዓለም ሁሉ የተጨቆኑና የተረገጡ በፍላጎትና በተስፋ ወደዚህች አገር ፊታቸውን አዙረዋል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ እርስዋ መግባት ይሻሉ፤ በምድር ካሉ ኃያላን መንግሥታት አንዷ የመሆንን ስፍራ በመያዝ አሜሪካ ተመንድጋለች።"*
—The Great Controversy, pp. 440, 441.

## ሀ. በግ መሰሉ አውሬ የሚፈፀም ምን አስደንጋጭ ለውጥ ይከሰታል? ራዕይ 13:12፣ 16

"ተምሳሌቱ የበግ የሚመስሉ ቀንዶችና የዘንዶ ድምጽ፣ በተወከለችዋ አገር ንግግርና ድርጊት መካከል ያለውን አስደናቂ መጣረስ የሚጠቁም ነው። "ይናገራል" የሚለው የሃገሪቱ የሕግ አውጪና ተርጓሚ ባለስልጣናትን ድርጊት የሚያሳይ ነው።ይህን በመተግበርም የመርህ-ግብሩ መሰረት እንደሆኑ አድርጎ ላስቀመጣቸው ለነዚያ ነፃ አስተሳሰብ እና ሰላማዊ መርሆዎች የማስመሰል መልክ ይሰጣቸዋል። "እንደ ዘንዶ" ይናገራል "በፊተኛውም አውሬ ስልጣን ሁሉን ያደርጋል" የሚለው ትንቢት በግልጽ የሚተነብየው በዘንዶውና በነብር መሰል አውሬ የተወከሉት መንግሥታት ሲያንፀባርቁት የነበረውን ያለመቻቻልና፣ የማሳደድ መንፈስ እንደሚያጎለብት ነው። ሁለት ቀንዶች ያሉት አውሬ "ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል" ሲል የሚያመለክተው ለጳጳሳዊ ስርዓቱ ክብር ሲባል መጠበቅ ያለባቸው የተወሰኑ ትዕዛዞች የዚህችን አገር ስልጣን በመጠቀም ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ ይሰራል ማለት ነው።

እንደዚህ ዓይነቱ ድርጊት፣ ለዚህ መንግሥት መርሆዎች፣ ጠንካራ ተጽዕኖ ማሳረፍ ለሚችሉት ነፃ ተቋሞችዋ፣ ለነፃነት አዋጁ ቀጥተኛና ክቡር መኃላዎች እንዲሁም ለህገ መንግሥቱ በቀጥታ ተፃራሪ ይሆናል። መንግሥታዊ ኃይል በቤተ ክርስቲያን ላይ ጥቅም ላይ እንዳይውል የማይቀረውም ያለመቻቻልና የስደት ውጤቱ እንዳይከሰት የሃገሪቱ መሥራቾች በጥንቃቄ እንዲጠበቅ ለማድረግ ጥረዋል። ህገ መንግሥቱ፣ "የተወካዮች ምክር ቤቱ የአንድ ኃይማኖታዊ ተቋምን በተመለከተ እንዲከበር የማድረግ ወይም [ያንን ኃይማኖት] በነፃነት የመከተል መብትን የሚከለክል ሕግ ማውጣት አይችልም።" በተጨማሪም "በአሜሪካ ውስጥ እንደ የሙያ መመዘኛ ሆኖ የሚቀርብ፣ መንግሥታዊ የሥራ ክፍልን ለመያዝ (ሥራ ለመቀጠር) የሚረዳ፣ ኃይማኖታዊ ፈተና፣ መስፈርት ሆኖ መቅረብ ፈጽሞ አይችልም" ይላል። አንድ ኃይማኖት እንዲመለክ የሚያደርግ መንግሥታዊ ትዕዛዝ ሊወጣ የሚችለው የአገሪቱን ነፃነት ለመጠበቅ የተቀመጡትን እነዚህን ቅጥሮች በአይነ-ደረቅነት ከጣሰ ብቻ ነው።—The Great Controversy, p. 442.

## ለ. ይህ የአውሬው ምልክት ተግባራዊ መደረግ እንዴት የዩናይትድ ስቴትስ (የአሜርካ) ውድቀት ይሆናል? ምሳሌ 14:34፤ መዝሙር 119:126።

"በየምዕተ ዓመቱ የተፈጸመው ስድ ተግባር ለፍርድ ቀን ቁጣን አስቀምጧል፤ ያ ቀን ሲመጣና የበደል ጽዋ ሲሞላ እግዚአብሔር እንግዳ (ያልተለመደ) ሥራውን ይሰራል። የእግዚአብሔር ትዕግሥት ማለቅ አሰቃቂ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ ከምህረት ጋር ያልተቀላቀለ ተብሎ የተገለጸበት ምክንያት በአስደናቂ ሁኔታና በኃይል ስለሚወርድ እና ምድር ባድማ ስለምትሆን ነው። የበደል ስፍር የሚሞላው ብሔራዊ ክህደት ሲፈጸም፣ የአገሪቱ መሪዎች የሰይጣንን መርህ በመተግበር ራሳቸውን ከኃጢአት ሰው ጋር ሲያሰልፉ ነው፤ ብሔራዊ ክህደት የብሔራዊ ውድቀት ምልክት ነው።"—Selected Messages, bk. 2, p. 373.

## 5. የአውሬው ምልክት ሐሙስ፣ ግንቦት 27

## ሀ. የሮም ሥልጣን ምልክት ምንድን ነው? ዳንኤል 7:25

"የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስልጣን ምልክት እንደሆነ አድርገው ጳጳሳዊ ፀሃፊዎች ሲጠቅሱ "ሰንበትን ወደ እሁድ የመለወጡ ያው ድርጊት፣ ፕሮቴስታንቶችም ፈቃድ የሰጡበት ድርጊት ነው.... ምክንያቱም እሁድን ውልፍት ሳይሉ በማክበራቸው ቤተ ክርስቲያን በዓላትን የማቋቋምና የማጽደቅ እንዲሁም አለማክበር ኃጢአት እንደሆነ ትዕዛዝ የማስተላለፍ ስልጣን እንዳላት እውቅና ይሰጣሉ።" ["Abridgment of Christian Doctrine"]። ታዲያ የሰንበት መለወጥ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ስልጣን ምስል ወይም ምልክት፣ "የአውሬው ምልክት" ከመሆን ውጪ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? . . .

"የእሁድ መከበር ግን በሕግ አስገዳጅ በሚሆንበት ጊዜ፣ መላው ዓለም ለእውነተኛው ሰንበት ያለበትን ኃላፊነት በሚረዳበት ጊዜ፣ ሮም ካላት ስልጣን የበለጠ ስልጣን የሌለውን መመሪያ በመታዘዝ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጥስ ማንኛውም ሰው፣ ጳጳሳዊ ሥርዓትን ከእግዚአብሔር በላይ ከፍ ከፍ ያደርጋል።"—The Great Controversy, pp. 448, 449.

## ለ. አንዱ እውነትን ለነፍሳት ለማብራራት እና ሌላኛው የአውሬውን ምልክት ተግባራዊ ለማድረግ በሚያደርጉት ተቃራኒ እንቅስቃሴ መካከል ያለውን ጡዘት ግለፅ። ራዕይ 13:13–15፤ 16:13፣ 14፤ ማቴዎስ 24:14፣ 24።

"ቤተ ክርስቲያን የመንግሥታዊ ኃይልን ጽኑ ክንድ [እርዳታ] ትጠይቃለች፤ በዚህም ተግባር ላይ ጳጳሳዊያኑና ፕሮቴስታንቶች ያብራሉ። እሁድን አስገዳጅ የሚያደርገው ንቅናቄ እየተባና የበለጠ ቀራጥ እየሆነ ሲመጣ [የእግዚአብሔርን] ትዕዛዛት በሚጠብቁ ላይ ሕጉ እንዲሰለጥን ይደረጋል። 392 ታላቁ ተጋድሎ በቅጣትና በእስር ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል። አንዳንዶቹም እምነታቸውን እንዲክዱ ማባበያ ይሆን ዘንድ ተጽዕኖ ፈጣሪ እርከኖች፣ ሽልማቶችና ጥቅማ ጥቅሞች ይበረከቱላቸዋል። ነገር ግን የማያወላውለው መልሳቸው፣ ልክ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሳለ፣ ሉተር ያቀረበው ጥያቄ (አቤቱታ) ይሆናል፦ "ስህተታችንን ከእግዚአብሔር ቃል ዘንድ አሳዩን።" በፍርድ ሸንጎዎች እንዲቀርቡ የሚደረጉ እነርሱ እውነትን ነፃ የሚያወጣ ጠንካራ መከራከሪያ ያደርጋሉ። ከሚሰሟቸው መካከል አንዳንዶቹም ሁሉንም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ጠብቀው እንደ እነርሱ ለመቆም ይመራሉ። በዚህ ሁኔታ እነዚህ እውነቶች በሌላ በምንም አይነት መንገድ ሊደርሳቸው የማይችሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ብርሐን ይደርሳቸዋል።"—Ibid., p. 607.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ግንቦት 28

1. በዳንኤል 7 ላይ ያለው አውሬ አንዳንድ ባህሪያት ወደ ሮም እንዴት ተሸጋገሩ?
2. የ1260 ዓመታት የጳጳሱ ስርዓት የበላይነት የተዘረዘሩባቸውን የተለያዩ መንገዶች ገምግም።
3. የአውሬው ለሞት የሚያደርስ ቁስል ሞትን ያላስከተለው ለምንድን ነው?
4. በበጉ ቀንዶች የተገለጹት የዩናይትድ ስቴትስ ልዩ ገጽታዎች ምንድን ናቸው?
5. ዛሬ በእሁድ የሚያመልኩ ሰዎች የአውሬው ምልክት አላቸውን?

# ሦስቱ መላእክት

## የመታሰቢያ ጥቅስ፡ "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት የሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው።" (ራዕይ 14፡12)

## ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡ Early Writings, pp. 232–261.

"ቅደም ተከተሉቻቸውን ጠብቀው የተቀመጡ ሦስት መልእክቶችን ተመልክቼ የነበረ ሲሆን እነርሱም የመጀመሪያው፣ የሁለተኛውና የሦስተኛው መልአክ መልእክቶች ነበሩ። አብሮኝ የነበረው መልአክ «እነዚህን መልእክቶች የሚጋርድ ወይም የሚገታ ወዮለት። የእነዚህ መልእክቶች እውነተኛ አስተውሎ አስፈላጊነቱ ከፍ ያለ በመሆኑ የነፍሳት የመጨረሻው መዳረሻ መልእክቶቹን በመቀበላቸው ላይ ይወሰናል" አለኝ።"—Early Writings, p. 258.

## 1. መላዕክት በራዕይ ውስጥ እሁድ፣ ግንቦት 30

### ሀ. በመላእክት የተወከሉትን የተለያዩ የመልእክተኞች ዓይነቶች አነፃፅር። ራዕይ 1፡20 ፤ 10፡1፣ 5 ፤ 11፡1 ፤ 22፡8

### ለ. እግዚአብሔር በምድር ላይ ላሉ ሁሉ መልእክት እንዴት ይልካል? ሮሜ 10:13–15

"እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ተወካዩ እነዲሆኑ ሊያድናቸው ከሚፈልጓቸው ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ስሜት ያላቸውን ሰዎችን እንጂ፤ ያልወደቁትን መላእክት ፈጽሞ አልመረጠም። "የማይመረመረውን የክርስቶስን ባለጠግነት" የማሳወቅ የተቀደሰ አደራ የተሰጠው ለወንዶች እና ለሴቶች ነው። ኤፌሶን 3:8"—The Acts of the Apostles, p. 134.

"የሱስን ለዓለም ለማቅረብ ከሰማያዊ መላእክት ጋር አብረን ሠራተኞች መሆን አለብን።… ከሰው ጋር የመገናኛ መንገድ መሆን ያለበት ሰው ነውና። እናም በሙሉ ልብ ለክርስቶስ ራሳችንን ስንሰጥ፤ መላእክት የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጽ በእኛ አንደበት መናገር ስለሚችሉ ይደሰታሉ።"—The Desire of Ages, p. 297.

### ሐ. በራዕይ 14:6–12 ላይ ባሉት መላእክት እና በተልእኮአቸው የተመሰለው ማን ነው? ማቴዎስ 28:19፣ 20፤ የሐዋርያት ሥራ 1:8

"መላእክቶቹ በምድር ታሪክ መጨረሻ ላይ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያለውን የማስጠንቀቂያ መልእክት በማወጅ በሰማይ መካከል እንደሚበሩ ሆነው ተገልጸዋል። እነዚህ መላእክት ከሰማይ ዩኒቨርስ ጋር በመስማማት እየሰሩ ያሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚወክል ምልክት ስለሆነ ማንም ሰው የእነዚህን መላእክት ድምፅ አይሰማም።"—Selected Messages, bk. 2, p. 387.

## 2. የመጀመሪያው መልአክ ሰኞ፣ ሰኔ 01

## ሀ. የመጀመሪያው መልአክ መልእክቱን የወሰደው ለማን ነበር? ራእይ 14:6

*"የክርስቶስ በቅርብ መምጣት በሚታወጅበት ጊዜ ታላቅ ኃይማኖታዊ መነቃቃት እንደሚኖር በመጀመሪያው መልአክ መልእክት በራዕይ 14 ትንቢት ተነግሯል። . . . የመልአኩ "በሰማይ መካከል" መብረር፣ ማስጠንቀቂያው የተነገረበት "ታላቅ ድምጽ" "በምድር ለሚኖሩ" ሁሉ መታወጁ፣ "ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም" መነገሩ፣ እንቅስቃሴው በፍጥነት የሚከናወንና ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዳለው ማስረጃ የሚሰጥ ነው።"*—The Great Controversy, p. 355.

## ለ. የመጀመሪያው መልአክ እንዴት ትኩረትን ወደ እግዚአብሔር ወደ ፈጣሪነቱ ሳበ? ራእይ 14:7፤ ዘፍጥረት 1:1፤ ኤፌሶን 3:9

## ሐ. የአድቬንቲስት እንቅስቃሴ፤ የመጀመሪያው መልአከ መልእክት እና ፍርድ እንዴት ክርስቶስ በቅርቡ ይመጣል ለሚለው ስብከታቸው እንደተጠቀሙበት አሰላስል። ዳንኤል 7:26፣ 27፤ 8:14፤ የሐዋርያት ሥራ 17:30፣ 31

*"ማስጠንቀቂያው በአሜሪካ ይነገር ዘንድ ኃላፊነቱ ለዊሊያም ሚለርና ለግብረ አበሮቹ ተሰጠ። ይህች አገር የታላቁ የአድቬንት (የምፅዓቱ መልእክት) እንቅስቃሴ እምብርት ሆነች። የመጀመሪያው መልአክ መልእክት ትንቢት እጅግ ቀጥተኛ የሆነ ፍፃሜ ያገኘው እዚህ ነው። የሚለርና ጓደኞቹ ጽሁፎች ወደ ሩቅ ስፍራዎች ተሰራጩ። ሚስዮናዊያን መድረስ የቻሉበት የዓለም ክፍል ሁሉ የክርስቶስ በቶሎ መመለስ መልካም ዜናዎች ተበተኑ። "የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት" የሚለው የዘላለሙ ወንጌል መልእክት በስፋትና በርቀት ተሰራጨ።*

*ክርስቶስ በ1844 ዓ.ም ፀደይ ወቅት እንደሚመጣ የሚያመለክቱ የሚመስሉት የትንቢታቱ ምስክርነቶች በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ሰርገው ገብተው ነበር። መልእክቱ ከክፍለ ሀገር ወደ ክፍለ ሀገር* (state to state) *ሲሰራጭ በሁሉም ስፍራ መነቃቃትና መጠነ ሰፊ ፍላጎት ይንፀባረቅ ነበር። በትንቢት ዘመናት የቀረቡት መከራከሪያዎች እውነት እንደሆኑ በማመን፣ የአመለካከታቸውን ኩራት በመሰዋት እውነትን በደስታ ተቀበሉ። አንዳንድ አገልጋዮች የተለየ አመለካከታቸውንና ስሜታቸውን ወደ ጎን በመተው፣ ደመወዛቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን በመተው የየሱስን መምጣት ለማወጅ ወጉ። ሆኖም በአንፃሩ ይህንን መልእክት የሚቀበሉ አገልጋዮች ብዙ አልነበሩም። እናም ሥራው በአብዛኛው ያረፈው በምስኪን ምዕመናን ነበር። . . . እግዚአብሔርን መሰልነት ያጣች ቤተ ክርስቲያን ሁኔታና በኃጢአት የተዘፈቀው ዓለም የእውነተኛ ጠባቂዎችን ልቦች በሸክም አቅመደመዱት፤ እናም ሰዎችን ወደ ንስሐ ብሎም ወደ ድነት ለመጥራት ሲሉ በፈቃደኛነት ፍጋትን፣ ችጋርንና መከራን ቻሉ። በሰይጣን ተቃውሞ ቢገጥመውም ሥራው በቀጣይነት ወደፊት ተራምዶ የምፅዓቱ እውነትም በበርካታ ሺዎች ተቀባይነትን አገኘ።"*—Ibid., p. 368.

## ሀ. ሁለተኛው መልአክ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነኝ ስለምትለው ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሁኔታ ምን ይላል? ራዕይ 14:8

*"ወይን ምንድን ነው? የሀሰት አስተምህሮዋ ነው። በአራተኛው ትዕዛዝ ሰንበት ፋንታ ለዓለም የውሸት ሰንበት ሰጥታለች፤ ሰይጣን በመጀመሪያ ለሄዋን በኤደን ገነት ውስጥ የነገረውን ውሸት፣ ነፍስ በተፈጥሮ የማትሞት መሆንዋን ደግማለች። «የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማረች" (ማቴ. 15፥ 9) ብዙ አይነት ስህተቶችን በስፋት አሰራጭታለች።*—Selected Messages, bk. 2, p. 118.

*"ባቢሎን መርዛማ ትምህርቶችን፣ የስህተትን ወይን እያስፋፋች ነው። ይህ የስህተት ወይን እንደ የነፍስ አትሞትም፣ የክፉዎች ዘላለማዊ ስቃይ፣ ክርስቶስ በቤተልሔም ከመወለዱ በፊት የነበረውን ህልውና መካድ እና የሳምንቱን የመጀመሪያ ቀን ከእግዚአብሔር ልዩ እና ከተቀደሰ ቀን በላይ ከፍ ማድረግን የመሳሰሉ የሐሰት ትምህርቶችን ያቀፈ ነው። እነዚህ እና ተመሳሳይ ስህተቶች በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለዓለም ቀርበዋል፣ በዚህም ምክንያት "አሕዛብ ሁሉ የዝሙትዋን ቁጣ ወይን ጠጅ ጠጥተዋልና" የሚሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ተፈጽመዋል።"*—Testimonies to Ministers, pp. 61, 62.

## ለ. በአድቬንቲስት እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ አማኞች የመጀመሪያውን ተስፋ መቁረጥ፣ የ2300 ቀናት እውነተኛ ፍጻሜ መገኘቱን እና መልእክቱን ከካዱት ሰዎች እንዲለዩ የተሰጣቸውን ጥሪ እንዴት እንደተረዱ ግለጽ። ዕንባቆም 2:3፤ ማቴዎስ 25:6

*"የ2300 ቀናቶቹ መጨረሻ ነው ተብሎ በታመነበት በ1844 በጋ እና በኋላ እንደታወቀውም ጊዜውን እስከ አራዘሙበት፣ የዛው ዓመት መከር ወቅት መካከል እኩሌታ አካባቢ ድረስ፣ "እነሆ ሙሽራው ደረሰ" የሚለው ራሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መልእክት እየታወጀ ነበር።*

*"ለዚህ እንቅስቃሴ ማለትም ጊዜው ከበጋ 1844 ወደ መከር የተራዘመበት ምክንያት የሆነው የ2300 ቀናት መነሻ (መጀመሪያ) የነበረው የሩሳሌምን እንደገና ለመገንባት የወጣው የአርጤክስስ አዋጅ ተግባራዊ የሆነው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ457 የመከር ወቅት እንጂ በፊት ይታመን እንደነበረው የአመቱ መጀመሪያ እንዳልሆነ ስለተደረሰበት ነበር። ከክ. ል. በፊት 457 ዓ.ዓ ጀምሮ 2300 ቀናቱ ሲቆጠሩ በ1844 ዓ.ም መከር ወቅት ያበቃሉ።"*—The Great Controversy, pp. 398, 399.

*"አብያተክርስቲያናቱ የመጀመሪያውን መልአክ መልእክት ለመቀበል እምቢተኝነታቸውን በገለጹ ጊዜ ሰማያዊውን ብርሃን በመቃወም እራሳቸውን ከአምላካዊው ድጋፍና ምሪት አገለሉ። እነዚህ ሕዝቦች በገዛ ብርታታቸው በመታመን የመጀመሪያውን መልእክት በመቃወማቸው የሁለተኛውን መልአክ መልክት መመልከት በማይችሉበት ሁናቴ ውስጥ እራሳቸውን ዘፈቁ። ነገር ግን «ባቢሎን ወደቀች» የተሰኘውን መልእክት የተቀበሉና ጭቀና የደረሰባቸው የእግዚአብሔር ተወዳጆች ቤተክርስቲያንን ትተው ወጡ።"*—Early Writings, p. 237.

## ሀ. ከሦስተኛው መልአክ ምን አስገራሚ ማስጠንቀቂያ መጣ? ራእይ 14:9–11

"ለፍጡር ከተሰጡ እጅግ አሰፈሪ ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ የሚበልጠው በሶስተኛው መልአክ መልክት የተካተተው ነው። ከምሕረት ጋር ያልተቀላቀለውን የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያወርድ እጅግ አሰቃቂ ኃጢአት መሆን አለበት። ይህንን አስፈላጊ ጉዳይ በተመለከተ ሰዎች በጨለማ የሚተው አይሆኑም፤ ሊቀጡ ያላቸው ለምን እንደሆነ ሁሉም ያውቁ ዘንድ፣ ያመልጧቸውም ዘንድ ዕድል እንዲያገኙ የእግዚአብሔር ፍርድ ከመውረዱ በፊት ይህንን ኃጢአት የሚያወግዘው ማስጠንቀቂያው የሚሰጥ ይሆናል። . . . የተመሳሳዩ ሶስት እጥፍ መልእክት አካል የሆነው የሶስተኛው መልአክ ማስጠንቀቂያም ያነሰ ስርጭት አይኖረውም [እንደ መጀመሪያዎቹ መልእክቶች ለሁሉም የሚደርስ ይሆናል]። በትንቢት የተገለጸው በታላቅ ድምጽ በሚናገር በሰማይ መካከል በሚበር መልአክ እንደታወጀ ነው፤ የዓለምንም ትኩረት ያገኛል።"—The Great Controversy, pp. 449, 450.

## ለ. የሦስተኛው መልአክ መልእክት በተላለፈበት ዘመን፤ ቅዱሳን የሆኑት እንዴት ነው የሚለዩት? ራዕይ 14:12

"የእግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች በተለይ ለአራተኛው ትእዛዝ ባላቸው አክብሮት ተለይተው ይታወቃሉ፤ ምክንያቱም ይህ የእግዚአብሔር የመፍጠር ኃይል ምልክት እና በሰው ልጅ መፈራትና እና መከበር እንደሚገባው የሚመሰክር ነው። . . . በተጋድሎው ጉዳይ ላይ ክርስትና፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እና የየሱስን እምነት በሚጠብቁ፣ እንዲሁም አውሬውንና ምስሉን የሚያመልኩ እና ምልክቱን በሚቀበሉ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። ቤተክርስቲያን እና መንግስትም ሁሉንም "ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም" የአውሬውን ምልክት እንዲቀበሉ ለማስገደድ ኃይላቸውን አንድ ያደርጋሉ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ግን አይቀበሉትም። ራዕይ 13:16"—Testimonies for the Church, vol. 9, pp. 16, 17.

## ሐ. የሦስተኛው መልአክ መልእክት መነሳት እንዴት ይገለጻል? ራዕይ 7:2፣ 3.

"በኖቬምበር 1848 በዶርቸስተር፣ ማሳቹሴት በተካሄደው ስብሰባ ላይ፤ የታተመውን መልእክት ስለማወጅ እና በመንገዳችን ላይ እየበራ የነበረውን ብርሃን ማሳተምና ማሰራጨት የወንድሞች ግዴታ እንደሆነ በራዕይ ተረድቼ ነበር።

"ከራዕዩ ከወጣሁ በኋላ ባለቤቴን እንዲህ አልኩት 'ላንተ መልእክት አለኝ። ትንንሽ ወረቀቶችን አትመህ ለሕዝቡ መላክ መጀመር አለብህ። መጀመሪያ ላይ ትንሽ ይሁን፤ ነገር ግን ሕዝቡ እያነበቡት ሲሄዱ ህትመቱን በገንዘብ ይደግፉሃል፤ ከመጀመሪያውም ጀምሮ ስኬታማ ይሆናል። ከዚህ ትንሽ ጅምር ተነስቶ በዓለም ዙሪያ ግልጽ የሆነ የብርሃን ጅረቶች ወደመሆን እነደሚያድግ አየሁ።"—Life Sketches, p. 125.

## 5. የመልእክቱ ዋና ሀሳብ ሐሙስ፣ ሰኔ 04

### ሀ. የሦስተኛው መልአክ መልእክት በሚታወጅበት ወቅት በእምነት ለሞቱት ሰዎች የተነገረው በረከት እንዴት ይፈጸማል? ራዕይ 14:13፤ ዳንኤል 12:2

"እግዚአብሔር ህዝቦቹን ለማዳን የመረጠው ጊዜ አኩለ ሌሊት ነው። ጎጥአን በቅዱሳኑ ላይ እየተሳለቁባቸው እያለ ሳይታሰብ ጸሐይ ትፈነጥቅና በሙሉ ኃይሏ ታበራለች።: ጨረቃም በነበረችበት ላይ መታየቷን ትቀጥላለች። ቅዱሳን ይህን የመዳናቸውን ምልክት በታላቅ ደስታ ሲመለከቱ ኃጥአን ግን ትዕይንቱን በመደነቅ ያዩ ነበር። ምልክቶችና አስደናቂ ነገሮች በፍጥነት ተከታተሉ አሁን ሁለም ነገር ከተፈጥሮአዊ ሂደቱ ውጪ ያለ ይመስላል። ወንዞች መፍሰሳቸውን አቆሙ። በጽልመት የተሞሉ ከባባድ ደመናዎች መጥተው እርስ በርሳቸው ተጋጩ በዚህን ወቅት በተረጋጋ ክብር ውስጥ መሆኑ በግልጽ የሚታይበት አንድ ብቻ ስፍራ የነበረ ሲሆን ይኸውም እንደ ብዙ ውሖች ይፈስ የነበረውና ሰማይንና ምድርን ያናውጥ የነበረው የእግዚአብሔር ድምጽ ነበር ታላቅ የመሬት መናወጥ ሆነ: መቃብሮች ተከፈቱና የሦስተኛውን መልአክ መልእክት በእምነት ተቀብለው ሰንበትን የጠበቁ፤ እግዚአብሔር ሐጉን ከጠበቁት ጋር የሚገባውን የሰላም ኪዳን ለመስማት ካንቀላፉበት የትቢያ መኝታ በመንቃት ከበሩ።"—Early Writings, p. 285.

### ለ. የሦስቱ መላእክት መልእክቶች ሲጠናቀቁ ምን ይሆናል? ራዕይ 14:14–16፤ ማርቆስ 4:26–29

"መላእክት በፍጥነት ወደ ሰማይ ሲወጡና ሲወርዱ ተመለከትኩ። አነስተኛ የቀለም ማስቀመጫ በጎኑ የያዘ አንድ መልአክ ከምድር ወደ የሱስ ተመልሶ በመምጣት ቅዱሳን ተቆጥረውና ታትመው ማብቃቱንና ሥራው ፍጻሜ ማግኘቱን ሪፖርት አደረገ። ከዚያም አስርቱን ትእዛዛት ከያዘው ከታቦቱ ፊት ያገለግል የነበረው የሱስ ጥናውን ወደታች ሲወረውር ተመለከትኩ። የሱስ እጆቹን ወደ ላይ ብድግ ካደረገ በኋላ ድምጹን ከፍ አድርጎ «ተፈጸመ" በማለት ጮኸ።"—Ibid., p. 279.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሰኔ 05

1. እግዚአብሔር የወንጌልን ስብከት በሰው ልጆች ውክልና ላይ የመሰረተው ለምንድን ነው?
2. የመጀመሪያው መልአክ መልእክት በዓለም ዙሪያ እንዴት ተዳረሰ?
3. የሁለተኛው መልአክ መልእክት የተሰጠበትን ምክንያት ግለጽ።
4. የሦስተኛው መልአክ መልእክት ምን ልዩነት ያጎላል?
5. የሦስቱ መላእክት መልእክት ከተጠናቀቀ በኋላ ምን ዓይነት ክስተት ይከናወናል?

## ሰንበት፣ ሰኔ 13፣ 2018

## 12ኛ ትምህርት

# የመጨረሻው ጥሪ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡ “ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች።” (ራዕይ 18፡1)**

**ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡** The Great Controversy, pp. 603–612.

*“የመጨረሻው ታላቅ የወንጌል ሥራ የሚዘጋው፣ ሥራው ሲጀመር ከነበረው ባነሰ የእግዚአብሔር ኃይል መገለጥ አይደለም።”*—The Great Controversy, p. 611.

## 1. ታላቂቱ ባቢሎን እሁድ፣ ሰኔ 07

**ሀ. ዮሐንስ ታላቂቱ ባቢሎን በመባል ስለምትታወቀው ቤተክርስቲያን የተመለከተውን አስደናቂ እይታ ግለጽ። ራዕይ 17፡1–6።**

*“ሴቲቱ፣ የራዕይ 17 ባቢሎን ስትገለጽ “በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጎናጽፋ” በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁዎችም ተሸልማ ነበር። በእጅዋም የሚያፀይፍ ነገር፣ የዝሙትዋም ርኩሰት የሞላበትን የወርቅ ጽዋ ያዘች። ... በግንባርዋም ምስጢር የሆነ ስም ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞቶችና የምድር ርኩሰት እናት ተብሎ ተፃፈ” ይላል ነብዩ። . . . ለብዙ መቶ ዓመታት በክርስቲያን ነገሥታት ላይ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ አገዛዝ መስርቶ ቀፍድዶ ያኖራቸው ሮም ነው። ቀይና ሐምራዊ ቀለም፣ ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች እንዲሁም ዕንቁዎች በግልጽ የሚያመለክተው አንፀባራቂውን፣ ከነገሥታት በላይ የሆነውን፣ በእብሪተኛው ሮም መንበረ-መንግሥት የተደገፈውን ልታይ ልታይ ባይነትን ነው። “በቅዱሳን ደም ሰክራ” ተብላ በትክክል የተነገረባት፣ የክርስቶስን ተከታዮች በጭካኔ ካሳደደችው ቤተ ክርስቲያን በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም። ባቢሎን “ከምድር ነገሥታት” ጋር ህገ-ወጥ ቁርኝት በማድረግ ኃጢአትም ትከሰሳለች። ከጌታ ተለይታ ከአሕዛብ ጋር ህብረት በመፍጠርዋ ነበር የአይሁድ ቤተ ክርስቲያን ጋለሞታ የሆነችው፤ ሮምም የምድራዊ ኃይላትን እገዛ በመሻት በተመሳሳይ ሁኔታ ራስዋን ስላበላሸች፣ ተመሳሳይ ኩነኔ ትቀበላለች።”*—The Great Controversy, p. 382. [Author’s italics.]

**ለ. ይህ ኃይል እንዴት ወደ ፍጻሜው ይመጣል? ራዕይ 17:15–18.**

## 2. ሌላኛው መልአክ          ሰኞ፣ ሰኔ 08

## ሀ. በራዕይ 18:1 ላይ የታየውን መልአክ አመጣጥ ግለጽ።

*“የሦስቱ መላእክት መልእክቶች በአንድነት ለዓለም ሦስት እጥፍ ብርሃናቸውን ይሰጣሉ። ዮሐንስ በራዕዩ እንዲህ ይላል፡ “ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች።” (ራዕይ 18:1) ይህ የመጨረሻውን እና ሦስት እጥፍ የሆነውን የማስጠንቀቂያ መልእክት ለዓለም መስጠትን ያመለክታል።”*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7 p. 985.

*“ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ የጸጋ ባለጠግነት ማከማቻ ናት፤ በቤተ ክርስቲያንም በኩል የመጨረሻውና ሙሉ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር “በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት” እንኳን ይገለጣል።”*—The Acts of the Apostles, p. 9.

## ለ. የመልአኩ ክብር ምንን ያመለክታል? እንዴትስ ታይቷል? መዝሙር 29:1፣ 2፤ ዮሐንስ 17:22፣ 23

*“የባህሪ መገንባት ችላ ሲባል፣ የነፍስ ውበት ሲጎድል፣ እግዚአብሔርን መምሰል ሲናቅ፤ የኩራትና የታይታ ፍቅር አሰደናቂ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎችን ወደ መስራትና ወደ ማስጌጥ እንዲሁም ትላልቅ ክበረ በዓላትን ወደማክበር ይመራል። ነገር ግን በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር አይከብርም። እርሱ ቤተክርስቲያንን የሚያከብራት በውጫዊ እይታዋ ሳይሆን ከዓለም በሚለያት ቅን አምልኮዋ ነው። እርሱ የሚመዝነው አባላቱ በክርስቶስ እውቀትና በመንፈሳዊ ልምምዳቸው ባላቸው እድገት መሠረት ነው።”*—Prophets and Kings, pp. 565, 566.

## ሐ. ሙሴ ለማየት ሲጠይቀው እግዚአብሔር የራሱን ክብር እንዴት ገለጸ? ዘጸአት 33:18፣ 19፤ 34:5–7።

*“የእግዚአብሔር ባህሪያት ክብር በባሕርይው ይገለጻሉ። እያንዳንዱ  የቅዱሳት መጻሕፍት ገጽ በእርሱ ብርሃን ያበራል። የክርስቶስ ጽድቅ እንደ ንፁህና ነጭ ዕንቁ ምንም ጉድለት ወይም እድፍ የለውም። ምንም ጉድለት ስለሌለው የትኛውም የሰው ሥራ የእግዚአብሔርን ታላቅና ውድ ስጦታ ሊያሻሽል አይችልም። እንከን አልባ ነውና።”*—Christ’s Object Lessons, p. 115.

*“ይህ ባሕርይ በክርስቶስ ሕይወት ተገልጧል። ኃጢአትን በሥጋ  እንዲኮንን፤ ኃጢአተኛ ሥጋን ለበሰ። እርሱ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያለማቋረጥ አሳይቷል፤ ይህንንም ባሕርይ ያለማቋረጥ ለዓለም ይገልጥ ነበር።*

*“የክርስቶስ ተከታዮችም በሕይወታቸው ውስጥ ይህንኑ ባሕርይ እንዲገልጡ ይፈለጋል።”*—God’s Amazing Grace, p. 322.

## 3. የማስጠንቀቂያ መልዕክት                    ማክሰኞ፣ ሰኔ 09

## ሀ. መልአኩ በባቢሎን ለሚኖሩ ሰዎች እንዴት ተናገረ? ራዕይ 18:2

"*አንድ ሌላ ታላቅ ሥልጣን የተሰጠው ኃያል መልአክ ድምጹን ከሦስተኛው መልአክ ጋር በማቀናጀት ለመልእክቱ ኃይልና ጉልበት ለመስጠት ወደ ምድር ሲወርድ አየሁ። ለመልአኩ ከተሰጠው ታላቅ ኃይልና ክብር የተነሳ ምድር አበራች:: መልአኩ በብርቱ ድምጽ ሲጮኽ በእርሱ ላይ ያንጸባረቀው ብርሃን ስፍራውን ሁሉ በብርሃን ሞላው። . . . የባቢሎን ውድቀት መልእክት ቀደም ብሎ በሁለተኛው መልአክ በመሰጠቱ አሁን ከ*1844 *አንስቶ በቤተክርስቲያን የተከሰተውን ብልሹ አሠራር በማከል በድጋሚ ቀርቦአል።*"—Early Writings, p. 277.

## ለ. የሁለተኛው መልአክ መልእክት ለመጀመሪያ ጊዜ ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ በባቢሎን ምን የተለወጠ ነገር አለ? ራዕይ 18:3

"*የራዕይ* 14 *የሁለተኛው መልአክ መልዕት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰበከው በ*1844 *ዓ .ም በጋ ወቅት ነበር፤ የበለጠ ቀጥተኛ ተፈፃሚነቱም የፍርዱ ማስጠንቀቂያ በስፋት በታወጀበት፣ በአብዛኛው ተቀባይነት ባጣበትና የአብያተ ክርስቲያናት ማሽቀልቀል እጅግ ፈጣን በነበረበት በአሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ነበር። ነገር ግን የሁለተኛው መልአክ መልዕት በ*1844 *ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ፍፃሜ ላይ አልደረሰም ነበር። የአድቬንትን መልእክት በአለመቀበላቸው ምክንያት በዚያን ጊዜ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በግብረ ገብነት ውድቀት ውስጥ ነበሩ፤ ውድቀቱ ግን ገና አልተጠናቀቀም ነበር። ለዚህ ጊዜ የሚያስፈልጉትን የተለዩ እውነቶችን እምቢ ማለታቸውን ሲቀጥሉበት ወደ ታች እየወደቁ፣ እየወረዱ መጡ።*

"*ነገር ግን "ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቁጣ ወይን ጠጅ የተነሳ ወድቀዋልና" ማለት የሚቻልበት ጊዜ ገና ነው። አሕዛብ ሁሉ ይህን እንዲያደርጉ ገና አላደረገቻቸውም። ከዓለም ጋር የመመሳሰልና ለፈታኞቹ የዘመናችን እውነቶች ግድ የለሽ መሆን ያለ ሲሆን፣ በክርስትናው ዓለም ባሉ ሁሉም አገራት በሚገኙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ስር እየሰደደ መጥቷል። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናትም ጠንካራና ከባድ በሆነው የሁለተኛው መልአክ ውግዘት ውስጥ ተካትተዋል። የክህደት ሥራ ግን ገና መደምደሚያው ላይ አልደረሰም።*

"*መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ከጌታ መምጣት በፊት "በኃይል ሁሉ በምልክትም በሐሰትም ተዓምራት" ሰይጣን እንደሚሰራ ሰዎችም "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ" "ሐሰትን ያምኑ ዘንድ የስህተት መንፈስ" ይቀበሉ ዘንድ ይተዋሉ። ይህ ቅድመ ሁኔታ ሳይደርስ፣ በክርስትናው ዓለም ሁሉ የቤተ ክርስቲያናት የዓለም ህብረት ሙሉ ለሙሉ ሳይሳካ የባቢሎን ውድቀት ሙሉ አይሆንም (ፍፃሜ አያገኝም)። ለውጡ ተራማጅነት ያለው ነው፤ የራዕይ* 14÷8 *ሙሉ የሆነ መፈፀሚያ ገና ወደፊት ነው።*"—The Great Controversy, pp. 389, 390. [Author's italics]

## 4. የመጨረሻው ጥሪ ረቡዕ፣ ሰኔ 10

## ሀ. እስከ አሁን በባቢሎን ውስጥ ላሉት ምን አስቸኳይ ጥሪ ይሰማል? ራእይ 18:4

"በራዕይ 14÷6-12 ያለውን ሶስት እጥፍ ማስጠንቀቂያ ካለመቀበልዋ የተነሳ ቤተ ክርስቲያንዋ በሁለተኛው መልአክ የተነገረው ቅድመ ሁኔታ ላይ ሙሉ በሙሉ የምትደርስበት፣ አሁንም በባቢሎን ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከህብረትዋ እንዲነጠሉ የሚጠሩበት ጊዜ መቼ እንደሆነ ራዕይ 18 ይጠቁማል። ይህ ለዓለም የሚሰጥ የመጨረሻው መልእክት ነው፤ ሥራውንም ይፈጽማል። "በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በአመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ" [2ኛ ተሰ 2÷12] የስህተትን አሰራር እንዲቀበሉና ሐሰትን እንዲያምኑ በሚተውበት ጊዜ እውነትን ይቀበሉ ዘንድ ልባቸውን ክፍት በሚያደርጉ ሁሉ ላይ የእውነት ብርሐን ያንፀባርቃል፤ በባቢሎን የቀሩት የእግዚአብሔር ልጆች "ሕዝቤ ሆይ ከእርስዋ ዘንድ ውጡ" [ራዕይ 18÷4] የሚለውን ድምጽ ይሰማሉ።" —The Great Controversy, p. 390.

## ለ. "ሕዝቤ" ተብለው እና ከባቢሎን እንዲወጡ የተጠሩት እነማን ናቸው? ዮሐንስ 10:16።

"ባቢሎን በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የመንፈሳዊ ጽልመትና ከእግዚአብሔር ጋር ፀብ ቢኖርም ብዙ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በአባልነት የሚገኙ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ለዚህ ጊዜ የተሰጡትን የተለዩ እውነቶች በጭራሽ አይተው የማያውቁ ብዙዎች አሉ። አሁን ባሉበት ወቅታዊ ሁኔታቸው ያልረኩ፣ የተሻለ፣ ግልጽ ያለ ብርሐን በመናፈቅ ላይ ያሉ ጥቂቶች አይደሉም። በተቀራኙባቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የክርስቶስን መልክ ለማየት በከንቱ ያማትራሉ። እነዚህ አካላት[አብያተ ክርስቲያናት] ከእውነት የበለጠ እየራቁ፣ እየራቁ ሲሄዱና ቁርኝታቸውን ከዓለም ጋር የበለጠ እያጠናከሩ ሲሄዱ፣ በሁለቱ መደቦች መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ሄዶ በመጨረሻም በመለያየት ይደመደማል። እግዚአብሔርን ከሁሉም በላይ አስበልጠው የሚወዱ፣ "ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፣ የአምልኮ መልክ አላቸው ሃይሉን ግን ክደዋል" [2ኛ ጢሞ 3÷4፣5] ከተባሉት ጋር ተቀራኝተው መቆየት የማይችሉበት ጊዜ ይመጣል።"—Ibid., p. 390.

## ሐ. ከባቢሎን ስለመውጣት የተጠራው ጥሪ ለምን አጣዳፊ ሆነ? ራእይ 18:5–8

"በዳግም ምጽአቱ ተጠባባቂዎች ላይ አብርቶ የነበረው ብርሃን በየስፍራው በመሰራጨቱ በየአብያተክርስቲያናቱ ብርሃን ያገኙ፤ የሦስተኛውን መልአክ መልእክት ያልሰሙና ያልተቃወሙ የወደቀችውን ቤተክርስቲያን እየተዉ ወጡ።"—Early Writings, p. 278.

## 5. ጥሪውን ለማሰማት መዘጋጀት ሐሙስ፣ ሰኔ 11

## ሀ. ግልጽ የሆነ የማስጠንቀቂያ መልእክት አስፈላጊነትን ይግለጹ። ኢሳይያስ 58:1፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 14:7፣ 8

“የራዕይ አስራ ስምንተኛው ምዕራፍ እውነትን ያለምንም ገደብ በድፍረትና በኃይል ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። . . . በሦስተኛው መልአክ መልእክት አዋጅ ውስጥ ከመጠን በላይ ዙርያ ጥምጥም መሄድ አለ።”—Evangelism, p. 230..

“እግዚአብሔር እረኞቹ ተነስተው ሕዝቡ ሁሉ ስራቸውን አውቀው በታላቁ ሥራ ውስጥ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ፤ በአንድ ድምፅ ግልፅ የሆነን መልዕክት እንዲያስተላልፉ አስቧል። ከዚያም ከሰማይ የወረደው የሌላኛው መልአክ ኃይለኛና ግልጽ ብርሃን ምድርን በክብሩ ይሞላል። ብዙ ዓመታት ወደኋላ ቀርተናል፤ እግዚአብሔር ከሚኒያፖሊስ ስብሰባ ተነስቶ እያበራ እንዲወጣ የፈለገውን መልእክት በጨለምተኝነታቸው እድገቱን ያዘገዩት ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ልባቸውን ዝቅ ማድረግና ሥራው በእነርሱ አእምሮ መታወርና በልባቸው ድንዳኔ ምክንያት እንዴት እንደተደናቀፈ ማየትና መረዳት አለባቸው።”—The Ellen G. White 1888 Materials, p. 1070.

## ለ. ሁላችንም በግለሰብ ደረጃ በልባችን ልንይዘው የምንችለው የየሱስ ልባዊ ተማጽኖ ምንድን ነው? ዮሐንስ 12:35፣ 36.

“ሌላኛው መልአክ ድምፁን ከሦስተኛው መልአክ ጋር አንድ አደረገ፤ ምድርም በክብሩ በራች። ብርሃኑ እየጨመረ በመሄድ ለምድር አሕዛብ ሁሉ ያበራል፤ በሙሉ ኀይሉ እንደሚበራ ደማቅ ብርሃን ይወጣል። ወርቃማ ጨረሮቹ በምድር ሁሉ ፊት ላይ ባሉ ሰዎች፣ ሕዝቦችና ቋንቋዎች እስኪያርፉ ድረስ በታላቅ ኃይል ይታጀባል። እንዲህ ብዬ ልጠይቃቹ፥ ለዚህ ሥራ ለመዘጋጀት ምን እያደረጋችሁ ነው? ለዘላለም እየገነባችሁ ነው? ይህ መልአክ ለዓለም ይሰጡ ዘንድ ይህን መልእክት የያዙትን ሰዎች እንደሚወክል ማስታወስ አለብህ። ከእነዚያ ሰዎች መካከል ነህን?”—The Review and Herald, August 18, 1885.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሰኔ 12

1. ሮም የጋለሞቶች እናት ከሆነችው ከባቢሎን መገለጫዎች ጋር እንዴት እንደምትስማማ አብራራ።
2. በሌላኛው መልአክ የሚገለጠው የእግዚአብሔር እውነተኛ ክብር ምንድን ነው?
3. የሁለተኛው መልአክ መልእክት መደገም ያለበት ለምንድን ነው?
4. ዛሬ አብዛኞቹ የየሱስ እውነተኛ ተከታዮች የት ናቸው?
5. ዛሬ ለእግዚአብሔር ሥራ እንቅፋት ከመሆን ይልቅ እንዴት አዎንታዊ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን እችላለሁ?

# የመጨረሻው አስቀድሞ ተነግሮአል

## የመታሰቢያ ጥቅስ፡ "በዙፋኑም የተቀመጠው፡- እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፡- እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ።"(ራዕይ 21፡5)

## ለንባብ የተመረጠው መጽሐፍ፡ Early Writings, pp. 279–295.

"በኃጢአት እርግማን ስር ያለችው፤ በክቡር ፍጥረታቱ ውስጥ እንደ አንድ የጨለማ ምልክት የሆነችው ትንሿ ዓለማችን፤ በእግዚአብሔር አጽናፈ ዓለም ውስጥ ካሉ ሌሎች ዓለማት ሁሉ በላይ ትከብራለች።"—The Desire of Ages, p. 26.

## 1. ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች እሁድ፣ ሰኔ 14

### ሀ. በምድር ላይ ስለሚፈሱት የእግዚአብሔር ፍርዶች ምን ተገለጠ? ራዕይ15፡1፤ ምዕራፍ 16

"መጠለያ በሌላቸው ላይ ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች በቅርቡ እንደሚወርዱባቸው ብመለከትም ዓለም እነዚህን መቅሰፍቶች ሊዘንቡ ካሉ ታላላቅ የዝናብ ጠብታዎች አግዝፎ አልተመለከታቸውም ነበር። የእግዚአብሔር ቁጣ የሆነውን አስፈሪውን የሰባቱን መቅሰፍቶች ትዕይንት በጽናት የምመለከትበት ድፍረት ተሰጠኝ። የእግዚአብሔር ቁጣ በእጅጉ አስፈሪ መሆኑን በመመልከት እርሱ በቁጣ እጁን ወደፊት ወይም ወደ ላይ ቢዘረጋ መላው የምድር ሕዝቦች ከዚህ ቀደም እንዳልነበሩ ይሆናሉ ወይም በማይድኑ ቁስሎችና መቅሰፍቶች ይመታሉ። በዚህም በእነዚህ አሰቃቂ ነገሮች ከመጥፋት ውጪ አንዳችም መዳኛ አያገኙም።"—Early Writings, p. 64.

### ለ. ተመሳሳይ ትዕይንት በምን አይነት የተለየ መንገድ ተገለፀ? ኤርምያስ 25:30–33፤ ራዕይ 19:17–21

"ኃጥአን የምሕረት ጊዜ ወሰናቸውን (ገደባቸውን) አልፈዋል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ባላሰለሰ ተቃውሞ ምክንያት በመጨረሻ ተወስዶአል። በመለኮት ፀጋ ስላልተከለሉ ከክፉው [ከሰይጣን የሚከልላቸው] ጥበቃ የላቸውም። ከዚያም ሰይጣን የምድርን ነዋሪዎች ወደ አንድ የመጨረሻ ታላቅ መከራ ይዘፍቃቸዋል። የእግዚአብሔር መላእክት የሰውን ጥልቅ የስሜት ሞገድ ከማገድ ሲያቆሙ የጥላቻ ባህርያት ሁሉ ልቅ ይሆናሉ። በጥንታዊት የሩሳሌም ላይ ከመጣው ጥፋት እጅግ በከፋ ሁኔታ መላው ዓለም ውድመት ውስጥ ይገባል።"—The Great Controversy, p. 614.

## ሀ. የራዕይ መጽሐፍ የክርስቶስን ዳግም ምጻት እንዴት ይገልጸዋል? ራዕይ 1:7፤ 6:15-17

"ብዙም ሳይቆይ ዐይኖቻችን ወደ ምሥራቅ በማቅናት ትንሽና ጥቁር ደመና ብቅ ሲል ተመለከትን። ይህ የሰውን እጅ ግማሽ ያህል መጠን ያለው ደመና የሰው ልጅ መምጣት ምልክት መሆኑን ሁላችንም አውቀናል። ደመናው እየቀረበ ሲመጣ ሁላችንም ግርማ ባለው ጸጥታ ደመናውን አፍጥጠን ተመለከትነው። ትንሹ ደመና ግዙፍና ነጭ እስኪሆን ድረስ ክብሩ እየጨመረ ይሄድ ጀመር ከወደ ስሩ ላይ እንደሚንበለበል እሳት ሆኖ ሲታይ፤ ደመናው ላይ ቀስተደመና አርፎበት ነበር። አሥር ሺህ መላእክት ዙሪያውን ከበውት በእጅጉ ተወዳጅ መዝሙር ይዘምሩ የነበረ ሲሆን በላዩ ላይ ደግሞ የሰው ልጅ ተቀምጦአል። ነጭ የተጠቀለለ ጸጉሩ በትከሻዎቹ ላይ ዘንፈል ብሎአል። በዐናቱ ላይ ደግሞ ብዙ ዘውዶች ነበሩ እግሮቹ የሚንበለበል እሳት ይመስሉ ነበር፤ በቀኝ እጁ ስለታማ ማጭድ በግራ እጁ ደግሞ ብርማ ቀለም ያለው መለከት ይዞአል። ልጆቹን ከዳር እስከ ዳር የሚመለከቱት ዐይኖቹ የአሳት ነበልባል ይመስሉ የነበር። ከዚያም የሁሉም ፊት ብሩህ ገጽታ ይዞ በአንድ ሲሰበሰቡ በእግዚአብሔር ነቀፌታ የደረሰባቸው ግን ጥቀርሻ መስለው በአንድ ተከማቹ። ከዚያም ሁላችንም «በፊቱ መቆም የሚችለው ማን ነው? የለበስኩት መጎናጸፊያ እንከን ዐልባ ነውን?" በማለት ጬኸታችንን አሰማን። ወዲያውም መላእክት ዝማሬአቸውን በማቆም አስፈሪ ጸጥታ የነገሠበት ጊዜ ተስተዋለ። ነገር ግን የሱስ «ንጹህ እጆችና ልቦች ያሏቸው መቆም ይችላሉ--ጸጋዬ ይበቃችኋል» ብሎ ሲናገር ፊታችን አበራ፥ ልባችንም በደስታ ተሞላ። ደመናው ከበፊቱ ይበልጥ ወደ ምድር እየተቃረበ በመጣበት በዚያን ወቅት መላእክት አቁመውት የነበረውን ዝማሬ ከበፊቱ ከፍ ባለ ድምፅ እንደገና ማሰማታቸውን ቀጠሉ።"—Early Writings, pp. 15, 16.

## ለ. መላእክት ከዚያ በኋላ ምን ያደርጋሉ? ማቴዎስ 24:31፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 4:16፣ 17

"ኃጢአት የመለኮትን መልክ አበላሽቶ ሙሉ ለሙሉ ሊያጠፋው ተቃርቦ ነበር፤ ነገር ግን የጠፋውን ያድስ ዘንድ ክርስቶስ መጣ። የተዋረደውን (ግሙን) ሰውነታቸውን ይለውጠዋል፤ ውብ በሆነው አካሉ አምሳያም ያበጃቸዋል። ደም ግባቱ የጠፋበት፣ በአንድ ወቅት በኃጢአት ተበክሎ የነበረው ሟቹና ተበላሹ አካል ፍፁም፣ ውብና ዘላለማዊ (immortal) ይሆናል። . . .

"መላእክት "ከአራቱ ነፋሳት ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ የተመረጡትን" ሰበሰቡ። ህፃናት በመላእክት ወደ እናቶቻቸው እቅፍ ተወሰዱ። ከአሁን ወዲያ ፈጽሞ ላይነጣጠሉ ለረጅም ጊዜ በሞት ተለይተው የነበሩ ወዳጆች ተገናኙ፤ በተድላ (በሐሴት) መዝሙርም አንድ ላይ ወደ እግዚአብሔር ከተማ ወጡ።"—The Great Controversy, p. 645.

## ሐ. ሰይጣን የት ይሆናል? ራዕይ 20:1፣ 2

"ለሺህ ዓመታት ከክፉ መላእክቱ ጋር ሰይጣን በምድር ይሆናል።" በምድር ብቻ የተወሰነ በመሆኑ፣ ያልወደቁትን ለመፈተንና ለማስቀጣት ወደ ሌሎች ዓለማት መግባት ፈጽሞ አይችልም።"—Ibid., p. 659.

## ሀ. ሰይጣን በሚታሰርበት 1,000 ዓመታት ውስጥ ቅዱሳን ምን ያደርጋሉ? ራዕይ 20:4–6፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 6:2፣ 3

“በሺህ አመት ጊዜ፣ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ትንሳኤ መካከል፣ የኃጥአን ፍርድ ይከናወናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ፍርድ ሲያመለክት ዳግም ምፅዓቱን ተከትሎ የሚመጣ ክስተት እንደሆነ ይጠቁማል። “ስለዚህ በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሐን የሚያመጣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ” [1ኛ ቆሮ 4÷5]። ዳንኤልም ሲናገር በዘመናት የሸመገለው በመጣ ጊዜ “ፍርድ ለልዑል ቅዱሳን ተሰጣቸው” [ዳንኤል 7÷22]። በዚህ ጊዜ ፃድቃን ለእግዚአብሔር እንደ ነገሥታትና ካህናት ሆነው ይነግሳሉ (ይገዛሉ)። ዮሐንስ በራዕይ እንዲህ ይላል፦ “ዙፋኖችንም አየሁ፣ በርሳቸውም ተቀመጡባቸው፣ ፍርድም ተሰጣቸው።” “የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፤ ከእርሱም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሳሉ” [ራዕይ 20÷4፣6፤ 1ኛ ቆሮ 6÷2፣3]። በጳውሎስ አስቀድሞ እንደተነገረው “ፃድቃን በዓለም ላይ የሚፈርዱት” በዚህ ጊዜ ነው [ራዕይ 20÷4፣6፤ 1ኛ ቆሮ 6÷2፣3]። ሥራቸውን ከሕጉ መጽሐፍ (ከመጽሐፍ ቅዱስ) ጋር እያወዳደሩ በአካል ላይ እንደተሰራው መጠን እያንዳንዱን ጉዳይ እየወሰኑ፣ ከክርስቶስ ጋር በአንድነት በኃጥአን ላይ ይፈርዳሉ። ከዚያም ኃጥአን ሊገጥማቸው ያለው የስቃይ ፈተና እንደሥራቸው ተለክቶ ይቀመጣል። በየስማቸውም አንጻር በሞት መጽሐፍ ይሰፍራል።

ሰይጣንና ርኩስ መላእክቱም በክርስቶስና በሕዝቦቹ ይዳኛሉ። ጳውሎስ ይላል፦ “በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?” [ራዕይ 20÷4፣6፤ 1ኛ ቆሮ 6÷2፣3]። ይሁዳም ሲናገር፣ “መኖሪያቸውን የተውትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እሥራት ከጨለማ በታች እስከታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቋቸዋል።” [ይሁዳ 6]።” —The Great Controversy, pp. 660, 661.

## ለ. በ1,000 ዓመት ፍርድ መጨረሻ ምን ይሆናል? ራዕይ 21:2፤ 20:7፣ 8

“በሺው አመት መጨረሻ ሁለተኛው ትንሣኤ ይሆናል። “የተጻፈው ፍርድ” ይተገበር ዘንድ በእግዚአብሔርም ፊት ይቀርቡ ዘንድ ኃጥአን ከሞት ይነሳሉ። እዚያም ገላጩ[የሉስ] የጻድቃንን ትንሣኤ ካብራራ በኋላ እንዲህ ይላል፣ “የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ አመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አይኖሩም” [ራዕይ 20÷5]። ኢሳይያስም ኃጥአንን በተመለከተ ሲናገር፣ “ግዞተኞች በጉድጓድ እንደሚከማቹ በአንድነት ይከማቻሉ በግዞት ቤትም ውስጥ ተዘግተው ይኖራሉ፣ ከብዙ ቀንም በኋላ ይጎበኛሉ።” [ኢሳ 24÷22]።”—Ibid., p. 661. [Author’s italics.]

## ሐ. የክፉዎች የመጨረሻ ፍጻሜ ምን ይሆናል? ራእይ 20:9፤ ሚልክያስ 4:1

“በስተመጨረሻ፣ ኃጥአን፣ ሥርና ቅርንጫፍ፣ በሚያፀዳው ነበልባል ጠፉ - ስሩ ሰይጣን፣ ቅርንጫፎቹ ተከታዮቹ። የሕጉ ሙሉ ቅጣት ተጎብኝቷል፤ የፍርድ መጠይቁም ተማልቷል፤ ሰማይና ምድርም፣ እያዩ፣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አወጁ።”—Ibid., p. 673.

## 4. አዲሲቱ ምድር ረቡዕ፣ ሰኔ 17

## ሀ. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደገና አዲስ እንደሚያደርግ የሰጠውን ተስፋ ግለጽ። ራዕይ 21:1፣ 5፤ 22:1፣ 2፤ ኢሳይያስ 65:17

*"የቤዛነት ሥራ ሙሉ ይሆናል። ኃጢአት በበዛበት ቦታ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ እጅግ ይበዛል። ሰይጣን የእሱ እንደሆነች ያስብ የነበረው ምድር ራሷ መቤዠት ብቻ ሳይሆን ከፍ ከፍ ብላ ትከብራለች። በኃጢአት እርግማን ስር ያለችው፤ በክቡር ፍጥረታቱ ውስጥ እንደ አንድ የጨለማ ምልክት የሆነችው ትንሿ ዓለማችን፤ በእግዚአብሔር አጽናፈ ዓለም ውስጥ ካሉ ሌሎች ዓለማት ሁሉ በላይ ትከብራለች። የእግዚአብሔር ልጅ በሰበአዊነት በመጣበት፣ የክብር ንጉሥ በኖረበት፣ በተሠቃየበትና በሞተበት በእዚህ ሁሉንም ነገር አዲስ ሲያደርግ የእግዚአብሔር ድንኳን ከሰዎች ጋር ይሆናል፣ ከእነርሱም ጋር ይኖራል፣ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፣ እግዚአብሔርም ራሱ ከእነርሱ ጋር ይሆናል፣ አምላካቸውም ይሆናል። የተዋጁት ለዘለዓለም በእግዚአብሔር ብርሃን ሲመላለሱ ሳለ፤ ስለማይነገር ስጦታው "አማኑኤል፣ 'እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው' እያሉ ያመሰግኑታል።"—*
The Desire of Ages, p. 26.

## ለ. በአዲሱ ምድር ምን የተለየ ነገር ይኖራል? ኢሳይያስ 65:21–25፤ ራዕይ 21:4

*"በሰማይ ከባቢ አየር ህማም ይኖር ዘንድ አይችልም። እንባ፣ የቀብር ስደራ* [የቀብር መኪኖች ሰልፍ] *ወይም የመርዶ አርማ እዚያ አይኖርም።* . . .
*"በእግዚአብሔር ከተማ "ሌሊት አይኖርም"፤ እረፍት የሚሻ፣ የሚያስፈልገውም የለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግም ሆነ ለስሙ ምስጋና በመስጠት መድከም አይኖርም። ሁልጊዜም የጧት ትኩስነት* (አዲስነት) *ይሰማናል፤ ከማብቂያውም ፈጽሞ የራቅን እንሆናለን። "አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራባቸዋልና የመብራት* [የኩራዝ/ሻማ] *ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም"* [ራዕይ 22÷5]። *የፀሐይ ብርሃን በደማቅ ጨረር፣ ሆኖም በማያሳምም ፀዳል፣ ከእኛ የቀትር ብርሃን በሚበልጥ፣ መለካት በማይችል ነፀብራቅ ይተካል።—*The Great Controversy, p. 676.
*"የዳኑት ውርስ በመጽሐፍ ቅዱስ አገር ተብሎ ይጠራል* [ዕብ 11÷14-16]። *በዚያ ቦታ ሰማያዊው እረኛ መንጋውን ወደ ሕያው ምንጮች ይመራቸዋል። የሕይወት ዛፍ በየወሩ ፍሬ ትሰጣለች፤ ቅጠሎችዋም ለአሕዛብ አገልግሎት ይውላሉ። ሳያቋርጡ የሚፈሱ እንደ መስታወት ድንጋይ የነጹ ጅረቶች፣ ባጠገባቸው ቅጠላቸውን የሚያውለበልቡ ጥላቸውን ለዳኑት ባዘጋጀው መንገድ ላይ የሚያሳርፉ ዛፎችም አሉ። ወደ ውብ ኮረብታማ ስፍራዎች የሚለወጡ የተንጣለሉ ሜዳዎች አሉበት፤ የእግዚአብሔር ተራራዎችም ግዙፍ ቁንደዶአቸውን አምጥቀው ገዝፈው ይታያሉ። በነዚያ ፀጥታ በሰፈነባቸው ሜዳዎች በሕያው ምንጮች አፋፍ ለረዥም ጊዜ ተጓዥና ተቅበዝባዥ የነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ቤታቸውን ያገኛሉ።"—*
Ibid., p. 675.

## 5. ግብዣ እና በረከት ሐሙስ፣ ሰኔ 18

## ሀ. የሱስ የራዕይ መጽሐፍ ትንቢትን የሚያነቡትን ለማበረታታት የፈለገው በምን ቃላት ነው? ራዕይ 22:7፣ 12–14

*“ጌታ ራሱ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ምስጢሮች ለአገልጋዩ ገልጦለታል፣ እናም ሁሉም ያጠኑት ዘንድ ክፍት እንደሚሆኑም አድርጎታል። በውስጡ ያሉት እውነቶች በዚህች ምድር ታሪክ የመጨረሻ ቀናት ውስጥ ለሚኖሩ እንዲሁም በዮሐንስ ዘመን ይኖሩ ለነበሩት የተነገሩ ናቸው። በዚህ ትንቢት ውስጥ የተገለጹት አንዳንድ ትዕይንቶች ያለፉ ናቸው፣ አንዳንዶቹ አሁን እየተከናወኑ ነው፤ አንዳንዶቹ በጨለማ ኃይሎች እና በሰማዩ ልዑል መካከል ያለውን ታላቅ ግጭት መጨረሻ የሚያሳዩ ናቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በአዲሲቱ ምድር ላይ የተዋጁትን ድል እና ደስታ ይገልጣሉ።*

*“በራዕይ መጸዕሐፍ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ምልክት ትርጉም ማስረዳት ስለማይችሉ መጸዕሐፉ የያዘውን እውነት ትርጉም ለማወቅ ጥረት በማድረግ ይህንን መጽሐፍ መመርመር ከንቱ ነው ብሎ ማንም እንዳያስብ። እነዚህን ምስጢሮች ለዮሐንስ የገለጠለት እውነትን በትጋት ለሚፈልግ ሰው የሰማያዊ ነገር ቅምሻን ይሰጠዋል። ልባቸው እውነትን ለመቀበል ክፍት የሆኑ ሰዎች ትምህርቶቹን መረዳት እንዲችሉ ይደረጋሉ፤ እናም ‘የዚህን ትንቢት ቃል ለሚሰሙና በውስጡ የተጻፉትን ለሚጠብቁ’ የተሰጠውን የተስፋውን በረከት ያገኛሉ።”*—The Acts of the Apostles, pp. 584, 585.

## ለ. ክርስቶስ በእርሱ አማካኝነት የዘላለም ሕይወትንና ሰላምን እንድናገኝ እንዴት ይጋብዘናል? ራዕይ 22:17፤ ኢሳይያስ 55:1፤ ዮሐንስ 7:37፣ 38

*“ለተጠማች ነፍስ የሚደረገው የክርስቶስ ጥሪ አሁንም ደረሰ እየወጣ ነው። በበዓሉ የመጨረሻ ቀን በቤተ መቅደስ ከተሰማው ይልቅ በታላቅ ኃይል ወደ እኛ ይጮሓል። ምንጩ ለሁሉም ክፍት ነው። ለደከሙና ለዛሉት የሚያረሰርስ የዘላለም ሕይወት ውሀ ምንጭ ተዘጋጅቶላቸዋል።*

*የሱስ አሁንም ‘ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ’ እያለ ይጣራል።”*—The Desire of Ages, p. 454.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሰኔ 19

1. *መቅሰፍቶቹ የዓለምን ታሪክ ፍጻሜ እንዴት ያመጣሉ?*
2. *ክርስቶስ ሲመለስ በፊቱ ሊቆም የሚችለው ማን ነው?*
3. *በ1,000ው ዓመታት ውስጥ የሚደረገውን የፍርዱን ዓላማ ግለጽ።*
4. *የተቤዣቸው ሰዎች የመጨረሻ መኖሪያ ምን ይሆናል?*
5. *የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት አካል ለመሆን በሙሉ ልቤ እፈልጋለሁን?*

# የመጀመሪያ የሰንበት ሥጦታዎች



## መጋቢት 26፣ 2018

### የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ የጣሊያን ዋና መሥሪያ ቤት

ለእግዜብሔር ክብር ይሆን ዘንድ የዚህን ቦታ ጠቀሜታ ከፍ የምናደርግበት ጊዜ ላይ ነን። (ገጽ 4ን ተመልከቱ)



## ሚያዝያ 24፣ 2018

### የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ ለዓለም ሚሲዮናች

በጨለማ ውስጥ ያሉ ውድ ነፍሳት የወቅቱን እውነት ይሻሉና እኛም ተባብረን እናድርስ።



## ግንቦት 29፣ 2018

### የመጀመሪያው የሰንበት ስጦታ ከፕራግ፣ ቼክ ሪፐብሊክ የጸሎት ቤት

በተሐድሶ ውስጥ ታሪካዊ በሆነው በዚህ ከተማ ለአምላክ ክብር የብርሃን ማማ እንገንባ። (ገጽ 51 ተመልከቱ)